# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

## የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር


**የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስው የመማር ብልሀቶች ፍተሻ በወላይታ ዞን በባይራ ኮይሻ ወረዳ በቅሎ ሰኞ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት**


በ

ኢያሱ ኦንዶሼ



ሰኔ 2015 ዓ.ም

አዲስ አበባ ኢትዮጵያ

# የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስው የመማር ብልሀቶች ፍተሻ በወላይታ ዞን በባይራ ኮይሻ ወረዳ በቅሎ ሰኞ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት


## አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

### የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

### የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር


### በተግባራዊ ሥነ ልሳን አማርኛን ለማስተማር ኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት


**በ**

**ኢያሱ ኦንዶሼ**



ሰኔ 2015 ዓ.ም

አዲስ አበባ ኢትዮጵያ

# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

## የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

## የአማርኛ ቋንቋ  ሰዋስው የመማር ብልሀቶች ፍተሻ በምላይታ ዞን በባይራ ኮይሻ ወረዳ በቅሎ ሰኞ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት

በ

ኢያሱ አንዶሼ

የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

| | ስም | ፊርማ | ቀን |
|---|---|---|---|
| አማካሪ | ___________________ | __________ | ________ |
| ፈታኝ | ___________________ | __________ | ________ |
| ፈታኝ | ___________________ | __________ | ________ |

# ምስጋና

በቅድሚያ ውድ ጊዜያቸውን ሰውተው ይህን ጥናታዊ ፅሁፍ ከርዕስ ጀምሮ እያንዳንዷን ስህተቴን በጥልቀት በመመርመር ጠቃሚ አስተያየት ለሰጡኝ፣ ፅሁፉን በወቅቱ በማረም ትክክለኛ ቅርፅ በማስያዝ ከፍፃሜ እንድደርስ አስተዋፆ ላደረጉልኝ ውድ አማካሪዬ ፐ/ር ጌታሁን አማረ ምስጋናዬ የላቀ ነው፡፡

በጋውን በስራ ክረምቱን በትምህርት ከጎኗ ስለያት ናፍቆቴን ችላ ጅምሬን ላስፈፀመችልኝ ለውድ ባለቤቴ ለተስፋነሽ ገብሬ ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነው፡፡

ለጥናቱ መረጃ ለማሰባሰብ በሄድኩበት ትምህርት ቤት ሁሉ ትብብር ላደረጉልኝ የትምህርት ቤት አስተዳደሮችና ተማሪዎች እንዲሁም የሃሳብ የቁሳቁስ ድጋፍ በማድረግ ለጥናቴ የሚያገለግሉ መረጃዎችን በመስጠትና ስራዬን በመከታተል ልዩ ሙያዊ ድጋፍ ላደረገልኝ ለአቶ ፍቃዱ ዳና ምስጋናዬ ከልብ ነው፡፡

በመጨረሻም ይህንን የትምህርት እድል ለሰጠኝ ለሶዶ ዙሪያ ወረዳ አስተዳደርና አውቀታቸውን ለቸሩኝ ውድ መምህሮቼና የጥናቱን በጀት ለፈቀደልኝ ለአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

## ማውጫ

**ርዕስ** **ገፅ**


ምስጋና......I
ማውጫ......II
የሰንጠረዥ ማውጫ......IV
አጠቃሎ......V
ምዕራፍ አንድ......1
መግቢያ......1
1.1. የጥናቱ ዳራ......1
1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት......2
1.3. የጥናቱ ዓላማ......4
1.4. የጥናቱ ጠቀሜታ......4
1.5. ጥናቱ ገደብ (ወስን)......5
1.6. የጥናቱ ዉስንነት......5
ምዕራፍ ሁለት......6
የተዛማጅ ፅሁፎች ቅኝት......6
2.1. የሰዋሰዉ ምንነት......6
2.2. ቋንቋ የመማር ብልሀቶች ምንነት......6
2.3. ሰዋስው የመማር ብልሀቶች ምንነት......8
2.4. ቋንቋ በመማር ብልሀቶች አጠቃቀም ላይ ተፅዕኖ የሚያስከትሉ ሁኔታዎች......9
2.5. ሰዋስው የመማር ብልሀቶች በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ያለው ሚና......10
2.6. ሰዋስው የመማር ብልሀቶች አከፋፈል......11
2.6.1. ቀጥተኛ ሰዋስው የመማር ብልሀቶች......13
2.6.1.1. የማስታወስ ብልሀቶች......13
2.6.1.2 አእምሮታዊ (ግንዛቤያዊ) ብልሀቶች......15
2.6.1.3. የማካካሻ ብልሀቶች......16
2.6.2. ኢቀጥተኛ ሰዋስው የመማር ብልሀቶች......17
2.6.2.1. ልዕለ አእምሮታዊ ብልሀቶች......17
2.6.2.2. ስሜታዊ ብልሀቶች......18
2.6.2.3. ማህበራዊ ብልሀቶች......19
2.7 የቀደምት ጥናቶች ውጤት......20

ምዕራፍ ሶስት ........ 23
የጥናቱ ዘዴ ........ 23
3.1. የጥናቱ ንድፍ ........ 23
3.2. የመረጃ ምንጭ ........ 23
3.3. የናሙና አመራረጥ ዘዴ ........ 24
3.3.1. የክልልና የወረዳ የናሙና አመራረጥ ........ 24
3.3.2. የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ ........ 24
3.3.3 የክፍል ደረጃ ናሙና አመራረጥ ........ 24
3.3.4. የተማሪዎች የናሙና አመራረጥ ........ 24
3.4. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ........ 26
3.4.1 የፅሁፍ መጠይቅ ........ 26
3.5. የመረጃ አተናተን ዘዴ ........ 28
ምዕራፍ አራት ........ 29
የመረጃ ትንተናና ማብራሪያ ........ 29
4.1. ቀጥተኛ የመማር ብልሀቶች መረጃ ትንተና ማብራሪያ ........ 29
4.1.1. የማስታወስ ብልሀቶች መረጃ ትንተናና ማብራሪያ ........ 31
4.1.2 አእምሮታዊ ብልሀቶች መረጃ ትንተናና ማብራሬያ ........ 37
4.1.3 የማካካሻ ብልሀቶች መረጃ ትንተናና ማብራሪያ ........ 42
4.2. ኢቀጥተኛ የመማር ብልሀቶች ትንተና ማብራሪያ ........ 44
4.2.1 የልዕለ አእምሮታዊ ብልሀቶች መረጃ ትንተናና ማብራሪያ ........ 45
4.2.2. የስሜታዊ ብልሀቶች መረጃ ትንተናና ማብራሪያ ........ 48
4.2.3. የማህበራዊ ብልሀቶች መረጃ ትንተናና ማብራሪያ ........ 51
ምዕራፍ አምስት ........ 55
ማጠቃለያና የመፍትሄ ሀሳቦች ........ 55
5.1 ማጠቃለያ ........ 55
5.2. የመፍትሄ ሀሳቦች ........ 57
ዋቢ ፅሁፎች ........ 59
አባሪ 1 ........ 65

# የሰንጠረዥ ማውጫ

**ርዕስ** **ገፅ**

ሰንጠረዥ 1 በጥናቱ የተሳተፉ ተማሪዎች ስብጥር ........................................................25
ሰንጠረዥ 2. የማስታወስ ብልሀቶች መረጃ ...................................................................30
ሰንጠረዥ 3. የአእምሮታዊ ብልሀቶች መረጃ.................................................................36
ሰንጠረዥ 4. የማካካሻ ብልሀቶች መረጃ.........................................................................42
ሰንጠረዥ 5. የልዕለ አእምሮታዊ ብልሀቶች መረጃ........................................................45
ሰንጠረዥ 6. የስሜታዊ ብልሀቶች መረጃ .....................................................................48
ሰንጠረዥ 7. የማህበራዊ ብልሀቶች መረጃ....................................................................51

# አጠቃሎ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በደቡብ ክልል በወላይታ ዞን በባይራ ኮይሻ ወረዳ በቅሎ ሰኞ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስው የመማር ብልሀቶችን መመርመር ነው፡፡ ለዚህም ዘጠነኛ ክፍል ካሉት ከ440 ተማሪዎች መካከል በማሰባጠር 40 ተማሪዎች በዓላማ ናሙና ዘዴ ተመርጣዋል ፡፡ ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ለመሰብሰብ የፅሁፍ መጠይቅ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ የተሰበሰቡ መረጃዎችንም በሁለት ዋና ዋና ብልሀቶች በመክፈል ቀጥተኛ የመማር ብልሀቶች (የማስታወስ፤ አእምሮታዊና የማካካሻ) እና ኢቀጥተኛ የመማር ብልሀቶች (ልዕለ አእምሮታዊ፣ ስሜታዊና ማህበራዊ) መሰረት ዝርዝር ብልሀቶችን በምን ያህል መጠን እንደሚገለገሉባቸው በሰንጠረዥ ተደራጅተው በቁጥርና በመቶኛ ተጠቃልለው እንዲታዩ በማድረግ በገላጭ ዘዴ ተተንትነዋል፡፡ በፅሁፍ መጠይቅ በተሰበሰቡ መረጃዎች ትንተና ውጤት መሰረት የተማሪዎች ቀጥተኛ የመማር ብልሀቶች አጠቃቀም ዝቅተኛ ሲሆን ኢቀጥተኛ ብልሀቶች አጠቃቀም የተሻለ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ተማሪዎች ከቀጥተኛ መማር ብልሀቶች ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ከዚህ በፊት ከሚያውቀት ነገር ጋር ማያያዝን፣ በአእምሯቸው ውስጥ ምስል በመፍጠር ማስታወስን፣ የተለያዩ አካላዊ እንቅስቃሴዎች መጠቀምን፣ ሀጎችን ደጋግሞ መፃፍና መናገርን፣ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር መማርን፣ ጠቃሚ ሀሳቦችን አጠር አድርጎ ማስታውሻ መያዝን፣ ከአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ጋር ማነፃፀርን፣ ወደ አፍ መፍቻ ቋንቋ መተርጎምንና በፅሁፍ ውስጥ ጠቃሚ የሆኑ ሰዋስዋዊ መረጃዎችን የተለያዩ ምልክቶችን በማድረግ የመጠቀም ብልሀቶችን፤ ከኢቀጥተኛ መማር ብልሀቶች ውስጥ ደግሞ ዓላማ ማዘጋጀትን፣ ትኩረት መስጠትን፣ ማቀድን፣ጭንቀት መቀነስን፣ ራስን ማበረታታትን፣ አዎንታዊ ገለፃ መስጠትን፣ ሀላፊነት መውሰድን፣ ከክፍል ተማሪዎች ጋር መተባበርን፣ መምህሩን መጠየቅንና ማህበራዊ ግንዛቤ ማዳበርን አዘውትረው እንደሚጠቀሙ ለመረዳት ተችሏል፡፡ አብዘኞቹ ተማሪዎች ሌሎችን ዝርዝር ብልሀቶችን አልፎ አልፎ እንደሚገለገሉባቸው የተገኘው ትንተና ውጤት ያመለክታል፡፡ ይህም ብዙ ተማሪዎች ለበርካታ ቀጥተኛም ሆነ ኢቀጥተኛ ብልሀቶች ዕውቀትና ልምድ የሌላቸው መሆኑን ያሳያል፡፡ በመሆኑም መምህራን የተማሪዎቹን የመማር ብልሀት ምርጫ ተረድተው መረጃ በመስጠት ተማሪዎች የተለያዩ ሰዋስው የመማር ብልሀቶች ዕውቀትና ልምድ እንዲያዳብሩ ግንዛቤ ቢያስጨብጡ፤ ተማሪዎች ቀጥተኛ ሰዋስው የመማር ብልሀቶችን በተለይ የማስታወስና የማካካሻ ብልሀቶችን የመጠቀም ፍላጎታቸው አነስተኛ ስለሆነ የቋንቋ መምህራን ተማሪዎች እነዚህን ብልሀቶች በክፍል ውስጥም ሆነ ከክፍል ውጭ እንዲጠቀሙ ሁኔታዎችን ቢያመቻቹ፤ አንዳንድ ተማሪዎች ለመምህሩ ጥያቄ ማቅረብን፣እንቅስቃሴ መጠቀምን፣ ማድመቅ ማክበብን ብልሀቶችን ፈፅሞ ስለማይጠቀሙ መምህራን ተማሪዎቻቸው እነዚህን ብልሀቶች አልፎ አልፎ ቢሆንም እንዲጠቀሙ ቢያበረታቱ፤ እንዲሁም ተማሪዎች አዘውትረው የሚጠቀሙባቸውን ብልሀቶች ተከትለው የሚመጡ ችግሮች እንዳይፈጠሩ ቢጠብቁ የሚሉ የመፍትሄ ሀሳቦችን በማስቀመጥ ጥናቱ ተጠናቅቋል፡፡

# ምዕራፍ አንድ

# መግቢያ

## 1.1. የጥናቱ ዳራ

ቋንቋ የመማር ብልሀቶችን አስመልክቶ Oxford (1990፤8) ሲያብራሩ “ተማሪው የቋንቋ ትምህርት ሂደት ቀላል፣ ፈጣን፣ ማራኪና ምቹ ለማድረግ እንዲሁም ይበልጥ ራስ መርና ግልፅ ለማድረግ የሚወስዳቸው ዝርዝር ተግባሮች ወይም ሃሳቦች ናቸው”ይላሉ። እንደ Wharton (2000፤204) አገላለፅ የመማር ብልሀቶች “በተማሪዎች የሚተገበሩ መልመድን፣ ዕውቀት ማካበትን፣ ሀሳብን አስታውሶ መጠቀምን የሚያፋጥኑ የአሰራር ቴክኒኮች ሲሆኑ ተማሪው የቋንቋ ትምህርቱን ሂደት ምቹ፣ ራስ መርና አስደሳች በሆነ መንገድ ለመወጣት የሚያስችሉ መሳሪያዎች ናቸው”። O’malley and Chamot (1990፤1) በበኩላቸው ቋንቋ የመማር ብልሀቶች የታላሚው ቋንቋ ተማሪዎች ቋንቋ በመማር ሂደት መረጃን ለማጠራቀም የሚገለገሉባቸው ተግባራት ወይም ባህሪያት እንደሆኑ ያስረዳሉ። በተጨማሪም Chamot (2004፤14) የመማር ብልሀቶች “ተማሪዎች የቋንቋ ትምህርት ዓላማ ለማሳካት ሲባል ሆን ብለው የሚወስዷቸው ሀሳቦችና ተግባራት ናቸው” በማለት ይገልፃሉ። በመሆኑም ቋንቋ የመማር ብልሀቶች የቋንቋ ተማሪዎች በቋንቋ ትምህርት ሂደት የሚያጋጥሙ ቋንቋ በተለይም ሰዋስው የመማር እንቅፋቶችን ለማስወገድና መረዳትን ለማቀላጠፍ የሚገለገሉባቸው ስልቶች ናቸው።

ቋንቋ የመማር ብልሀቶች ቀጥተኛና ኢቀጥተኛ ተብለው በሁለት የሚከፈሉ ሲሆን፤ በያንዳንዳቸው ስር ደግሞ ሶስት ሶስት ንዑሳን ብልሀቶች ይገኛሉ። ቀጥተኛ የመማር ብልሀቶች ከቋንቋ ትምህርት ጋር ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት ያላቸው ብልሀቶች ናቸው። እነሱም የማስታወስ ብልሀቶች (አዳዲስ መረጃዎችን ለማግኘት፣ ለማከማቸትና መልሶ ለመጠቀም) ፣ አእምሮታዊ ብልሀቶች (አዳዲስ መረጃዎችን ለማገናዘብና ለመጠቀም)፣ የማካካሻ ብልሀቶች (የታላሚው ቋንቋ ዕውቀት እጥረት ለመተካት) የሚያገለግሉ ብልሀቶች ናቸው (Oxford 1990)።

ኢቀጥተኛ የመማር ብልሀቶች ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ ተማሪዎች በቋንቋ ትምህርት ውጤታማ እንዲሆኑ የሚያግዟቸው ብልሀቶች ናቸው።

እነሱም ልዕለ አእምሮታዊ ብልሀቶች (ግንዛቤያዊ ሂደትን ለመቆጣጠር)፣ ስሜታዊ ብልሀቶች (በቋንቋ ትምህርት ሂደት የሚያድርባቸውን ስሜት ለመቆጣጠር)፣ ማህበራዊ ብልሀቶች (ከሌሎች አካላት ጋር ግንኙነትን ወይም ተራክቦ ለመፍጠር) የሚያገለግሉ ብልሀቶች ናቸው (Oxford፣1990)፡፡ አያይዘውም Oxford (1990) ባጠቃላይ እነዚህ ብልሀቶች ተማሪዎች ከመምህሩ ጥገኝነት ነፃ እንዲሆኑ፣ የራሳቸውን ጠንካራና ደካማ ጎን ለይተው እንዲያውቁና የራሳቸውን የቋንቋ ትምህርት ሂደት በራሳቸው እንዲመሩ የሚረዷቸው ብልሀቶች እንደሆኑ ይገልፃሉ፡፡ በመሆኑም እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩ የመማር ብልሀቶች ተማሪዎች በቋንቋ ትምህርታቸው በተለይ በሰዋስው ትምህርታቸው ውጤታማ እንዲሆኑ የሚረዷቸው ብልሀቶች ናቸው፡፡

በመማር ብልሀቶች አጠቃቀም ላይ ተፅዕኖ የሚያስከትሉ በርካታ ሁኔታዎች እንዳሉ Rubin (1987)፣ Oxford (1989፤1990)፣ Griffths (2003)፣ Chamot (2004) ገልፀዋል፡፡ ከነዚህም ጥቂቶቹ ዕድሜ፣ የፆታ ልዩነት፣ የትምህርት ችሎታ፣ የመማር ብልሀት፣ ተነሳሽነት፣ አመለካከት፣ የመማር ስልት ናቸው፡፡

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ሰዋሰዉ የመማር ብልሀቶች ተማሪው በትምህርቱ ሂደት ራሱን እየመራ በንቃት ለመሳተፍና የቋንቋ ችሎታውን ለማዳበር የሚያገለግሉ ቁልፍ መሳሪያዎች እንደሆኑ Oxford (1990) ያብራራሉ፡፡ Hutimen (1996) በበኩላቸው ሰዋስው የመማር ብልሀቶች ጠቀሜታ ሲገልፁ ተማሪው በተግባቦት ሂደት በሰዋስው ችሎታ ማነስ ምክንያት ተግባቦቱ እንዳይቋረጥ፤ የቋንቋ ብቃት እንዲዳብር እንደሚረዷቸው ይገልፃሉ፡፡ ስለሆነም ሰዋስው የመማር ብልሀቶች ተማሪው በሰዋስው ትምህርት ሂደት ራስን በራስ በመደገፍ በትምህርት ቤትም ሆነ ከትምህርት ቤት ውጭ መምህሩን ማግኘት በማይችልበት ሁኔታ ሁሉ በራሱ ጥረት ሰዋስው የመማር ችሎታውን ለማሻሻል አስፈላጊዎች ናቸው፡፡

ተማሪዎች ከዝቅተኛ ክፍል ትምህርት ደረጃ ጀምሮ እስከ ተቋማት ድረስ ለታላሚው ቋንቋ ሰዋስው ያላቸው እውቀት ደካማና ሰዋስውን በተገቢው ሁኔታ የመጠቀም ችሎታቸው አነስተኛ እንደሆነ (Haregewain 2008) ይገልፃሉ፡፡

በአንድ ክፍል ውስጥ በተመሳሳይ ሁኔታ በአንድ ዓይነት ማስተማሪያ ዘዴ ከተማሩ ተማሪዎች መካከል አንዳንዶቹ ውጤታማ ሲሆኑ አንዳንዶቹ ግን ውጤታማ አይሆኑም፡፡

ለዚህም አንዱ ምክንያት ምናልባትም የተማሪዎች የመማር ብልሀቶች መለያየት ሊሆን ይችላል፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች በቋንቋ ትምህርታቸው ውጤታማ እንዲሆኑ ሰዋስው

የመማር ብልሀቶችን በብቃት መጠቀም ይገባቸዋል፡፡ በተጨማሪም Griffiths እና Judy (2001) ሲያብራሩ በቋንቋ ተማሪዎች መካከል ለሚታየው ልዩነት መነሻው የሚገለገሉባቸው ሰዋስው የመማር ብልሀቶች ልዩነት ነው፡፡

ሰዋሰዉ በመማር ብልሀቶች ዙሪያ የተወሰኑ ጥናታዊ ፅሁፎች ተሰርተዋል፡፡ ከነዚህም ጥቂቶቹ ሰለሞን (1991) የተማሪዎች የአማርኛ ድርሰት የመጻፍ ስትራቴጅና የመምህራን የማስተማር ዘዴ ተጣጥሞ መመርመር ሲሆን በመምህሩ ድርሰት በማስተማር ዘዴውና በተማሪዎች የመጻፍ ስትራቴጅ መካከል ክፍተት መኖሩን ወይም የማይጣጣሙ መሆኑን ጠቁመዋሉ፡፡ ሠፋ (1995) ተማሪዎች የሚጠቀሙባቸው ተግባቦታዊ ብልሀቶች ትንተና ሲሆን የተግባቦታዊ ብልሀት ዓይነቶችና ብዛት በተግባሩ ዓይነት እንደሚወሰኑ ገልፀዋሉ፡፡ ይርጋ (1997) ጥሩ የቋንቋ ተማሪዎች አማርኛ ሲማሩ የሚገለገሉባቸው ቋንቋ የመማር ብልሀቶች እና የመምህራን ግንዛቤ አሰሳ ሲሆን በተማሪዎቹ ቋንቋ የመማር ብልሀት እና በመምህራኑ የማስተማር ሂደት መካከል መጣጣም የሌለ መሆኑን አመለክተዋሉ፡፡ ከበደ (1999) የሰዋስው ትምህርት በክፍል ውስጥ ማስተማሪያ ብልሀቶች አጠቃቀምና አተገባበር መፈተሽ ሲሆን ብልሀቶቹ ለተማሪዎች የማይቀርቡ፣ ተማሪዎቹ የማይጠቀሙና የማይተገበር መሆኑን አመልክተዋሉ፡፡ ተክላይ (2000) የንባብ ብልሀት አጠቃቀምና የመምህራን ግንዛቤ ተጣጥሞ ፍተሻ ሲሆን በዝቅተኛ የክፍል ደረጃ የሚገኙ ተማሪዎች በከፍተኛ ክፍል ደረጃ ከሚገኙ ተማሪዎች ይልቅ የንባብ ብልሀት አጠቃቀም የተሻለና የመምህራን ግንዛቤ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ መሆኑን አመልክተዋሉ፡፡ በላይነሽ (2002) የአማርኛ ቋንቋ ቃላትን ለመማር የሚገለገሉባቸውን የመማር ብልሀቶች ፍተሻ፣ ንጋቱ (2005) ቃላት የመማር ብልሀት መፈተሽ ሲሆን ተማሪዎች ቃላትን የሚማሩበት መንገድ የመማር ብልሀቶችን መሰረት ያላደረገ መሆኑን አሳይተዋሉ፡፡ አብዘኞቹ የታላሚው ቋንቋ ጥናታዊ ፅሁፎች በክሂሎችና ቃላት በመማር ብልሀት ላይ የተሰሩ ናቸው፡፡ በያንዳንዱ ቋንቋ ትምህርት ዘርፍ መሰራቱ በተለይ በያንዳንዱ ቋንቋ ትምህርት ዘርፍ ለትምህትርትነት በሚሰጥበት ጊዜ የሚዘወተሩትንና የበለጠ ውጤታማ የሆኑትን ነጥሎ ለመለየት ስለሚያስችል በሰዋስው መሰራቱ ደግሞ ተጨማሪ ዕውቀት ይሰጣል፡፡

ስለዚህ እኔም ተማሪዎች ሰዋስው ሲማሩ የትኞቹን ብልሀቶች አዘውትረው እንደሚጠቀሙባቸው የሚያሳይ ጥናት ባለመኖሩ ጥናቱን ለማካሄድ ችያለሁ፡፡

በተጨማሪም አንዳንድ ተማሪዎች በሰዋስው ትምህርታቸው ውጤታማ ሲሆኑ አንዳንዶቹ ደግሞ ውጤታማ አይሆኑም፡፡ ለዚህ አንዱ ምክንያት ምናልባትም ሰዋስው የመማር ብልሀቶች አጠቃቀም መለያየት ሊሆን ይችላል፡፡ ከዚህ አንፃር በዚህ ጥናት በቅሎ ሰኞ

ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስው የመማር ብልሀቶችን የሚፈትሽ ነው፡፡

በመሆኑም ይህ ጥናት ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስው የመማር ብልሀት አጠቃቀማቸው ምን ይመስላል? ከብልሀቶቹ መካከል በተደጋጋሚ የሚገለገሉት የትኞቹን ነው? የሚለዉን ይመልሳል፡፡

## 1.3. የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በደቡብ ክልል በዎላይታ ዞን በባይራ ኮይሻ ወረዳ በበቅሎ ሰኞ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስው የመማር ብልሀቶችን መፈተሽ ነው፡፡ በዚህ ዋና ዓላማ ላይ በመመርኮዝ ጥናቱ የሚከተሉትን ዝርዝር ዓላማዎችን ይኖሩታል፡፡

1. በቅሎ ሰኞ 2ተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ9ኛ  ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስው ለመማር አዘውትረው የሚጠቀሙባቸው ቀጥተኛ ሰዋስው የመማር ብልሀቶች የትኞቹ እንደሆኑ መለየት፡፡
2. የክፍሉ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ  ሰዋሰውለመማር የሚገለገሉት ኢቀጥኛ የመማር ብላሃቶች የትኞቹ እንደሆኑ መፈተሽ
3. በሰዋሰው ትምህርት አቀራረብ ላይ በመምህራን ተጽኖ የሚያሳድሩ ተላዉጦችን መፈተሽ

## 1.4. የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት በበቅሎ ሰኞ 2ተኛደረጃ ትምህርት ቤት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስው የመማር ብልሀቶችን የሚፈትሽ ሲሆን ጥናቱ የሚከተሉትን ጠቀሜታዎች ይኖሩታል፡፡

1. ለመምህራን ተማሪዎቻቸው የሚጠቀሙባቸውን ብልሀቶች ተከትለው የሚመጡ ችግሮች እንዳይፈጠሩ ከወዲሁ ተዘጋጅተዉ  መጠበቅ እንዳለባቸው መረጃ ምንጭ ይሆናል፡፡
2. ለመጽሀፍ አዘጋጆች ተማሪዎች አዘውትረው በሚጠቀሙባቸው ብልሀቶች ምክንያት ችግር የሚከሰትበትን መልመጃ እንዲቀንሱና መልመጃ እንዲያዘጋጁ እንደመረጃ ምንጭ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል፡፡

3. ለመርሃ ትምህርት አዘጋጆች ተማሪዎች አዘውትረው የሚጠቀሙባቸውን ብልሀቶች ለይተው በማመልከት ከየብልሀቶቹ የሚመነጩ ችግሮች ማስተማሪያ መሳሪያዎች ላይ የጎላ ችግር እንዳይፈጥሩ ለማድረግ መረጃ ያገኙበታል፡፡

4. ወደፊት ስዋሰዉ በመማር ብልሃት ዙሪያ ተዛማጅ ጥናታዊ ጽሑፍ ለሚያደርጉ እንደማጣቀሻ ወይም ዋቢ በመሆን ያገለግላል፡፡

5. መምህራን የማስተማሪያ ብልሃቶችን ጠንካራና ደካማ ጎኖች በመለየት ቀጣይ ዝግጅቶችን በተሻለ መንገድ እንዲያከናዉኑ ያስችላችዋል፡፡

6. ወደፊት ሰዋስው በመማር ብልሀት ላይ ተጨማሪ ጥናት ለሚያካሂድ ሰው እንደመረጃ ምንጭነት ሊያገለግል ይችላል፡፡

## 1.5. ጥናቱ ገደብ (ወሰን)

ይህ ጥናት በደቡብ ክልል በወላይታ ዞን በባይራ ኮይሻ ወረዳ በበቅሎ ሰኞ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስው የመማር ብልሀት መፈተሽ ነው፡፡ በወረዳው ሁለት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችያሉ ሲሆን በሁለቱም ትምህርት ቤቶች ስዋሰውን የመማር ብላሀት ፍተሻ ማጥናት ካለኝ የጊዜ፣ የጉልበትና የገንዘብ አቅም አንፃር በቅሎ ሰኞ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በዘጠነኛ ክፍልተማሪዎች ብቻ እንዲወሰን ተደርጓል፡፡

የጥናቱ ትኩረት በቅሎ ሰኞ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ2015 ዓ.ም የሚማሩ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስው ሲማሩ የሚጠቀሙባቸው ብልሀቶች ምን ምን እንደሆኑና አዘውትረው የሚጠቀሙባቸው ብልሀቶች የትኞቹ እንደሆኑ ተተንትነዋል፡፡ በተጨማሪም የቋንቋ ክሂሎችና ሌሎች የዕውቀት ዘርፎች በዚህ ጥናት አይካተቱም፡፡

## 1.6. የጥናቱ ዉስንነት

ይህ ጥናት የአማርኛ ቋንቋ ሰዋሰው የመማር ብልሃቶ ፍተሻ ተማሪዎች ሰዋሰው የመማር ብልሃት ፍተሻ ችሎታ የማጎልበት ተግባራዊነትን ለማየት የታቀደ ነው፡፡ በዚህም የወላይታ ዞን በባይራ ኮይሻ ወረዳ በበቅሎ ሰኞ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ በ2015 ዓ.ም የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎችን ሰዋሰው የመማር ብልሃቶች ለመፈተሽ የተወሰነ ነው፡፡

# ምዕራፍ ሁለት
# የተዛማጅ ፅሁፎች ቅኝት

## 2.1. የሰዋሰዉ ምንነት

የሰዋሰዉን ምነንት አስመልክቶ የሚሰጡ ቢያነዎች የተለያዩ ከመሆናቸዉ ባሻገር ጽንሰ ሀሳቡን በተመለከተ ቁርጥ አድርጎ ይህ ለማለት አይቻልም፡፡ በተለያዩ አዉዶች ዉስጥ የተለያየ ቢያነ ያለዉ በመሆኑ እንደ ሁነታዉ ይቀያየራል፡፡ ከዚህ በማስተካከል ስለ ሰዋሰዉ የተሰጡት ቢያነዎች እንደሚከተለዉ ቀርቧል፡፡

> ሰዋሰዉ የሚለዉን ዋል/Green Baum (1988) ሲፈታዉ እንደ ምከተለዉ ያስቀምጣል፡፡
>
> ሰዋሰዉ የስነ-ልሳን ጥናት አንዱ ክፍል ሲሆን የሚያጠናዉ የቃላት ክፍሎችን፣ የድምጽ አፈጣጠር ሁነታን፣ ቃላቱ በዓ/ነገር ዉስጥ ያላቸዉን ግንኙትና፣ አግባብነት ካለዉ አጠቃቀም፣ አንጽር ሲሆን አንዳንደም ጥናቱ በስፋት ከጉዳዩ ጋር ግንኙነት ያለቸወዉን ስነ- ድምጸግን የቋንቋዎች ጥናትን፣ ከአጻጻፍ ስርዐትን ስነ- ፍችን ያካትታል፡፡

## 2.2. ቋንቋ የመማር ብልሀቶች ምንነት

ስለብልሀቶች ጥናት የተጀመረው እ.ኤ.አ በ1966 ዓ.ም አሮን ካርቶን በተባሉ ምሁር ሲሆን "በውጭ ቋንቋ ጥናት ሀሳብ ፈልቅቆ የማውጣት ዘዴ /the method of inference foreign language study/" በሚል ርዕሰ ጉዳይ የሰሩትን ጥናት ካሳተሙ በኂላ እንደሆነ Rubin (1987) ገልፀዋሉ፡፡ አያይዘውም Rubin ተማሪዎች ምክንያታዊ በሆነ መልኩ ሀሳብን ፈልቅቆ በማውጣት በኩል ባላቸው ተስጥኦ ችሎታቸው የሚለያዩ መሆናቸውን በጥናታቸው አብራርተዋሉ፡፡

ለብልሀቶች የሚሰጡ መጠሪያዎች የተለያዩ መሆናቸውን አንዳንድ ምሁራን ይገልፃሉ፡፡ ብልሀት የሚለውን አንዳንዶች "ስልት" ወይም "ሂደት" ብለው ሲጠሩ አንዳንዶቹ ደግሞ "ቴክኒክ"፣ "ታክቲክ"፣ "የመማር ክሂል" ወዘተ. እየተባለ እንደሚጠራ ይገልፃሉ፡፡ ይህን በተመለከተ Brown (1994) ስልት፣ ሂደትና ብልሀት በፅንሰ ሀሳብ ደረጃ የሚወራረሱ መሆናቸውን አብራርተዋሉ፡፡ ስልት በአንድ ግለሰብ ውስጥ በተደጋጋሚ ዘላቂ በሆነ መልኩ የሚስተዋል ባህርይ ሲሆን፣ ሂደት ደግሞ ማንኛውም ሰው በተወሰኑ የመማር ዓይነቶች ላይ

አሊያም በተወሰኑ የመማር ደረጃዎች ላይ እንደሚያልፍ የሚያመለክት ፅንሰ ሀሳብ ነው፡፡ ብልሀቶች ደግሞ አንድን ድርጊት ለመፈፀም ወይም አንድን ችግር ለመፍታት የሚገለገሉባቸው ዝርዝር ዘዴዎች መሆናቸውን ያመለክታሉ፡፡ Wenden (1987) በበኩላቸው ብልሀቶች "ቴክኒክ"፣ "ታክቲክ"፣ "ግንዛቤያዊ ብቃት"፣ "የመማር ክሂል"፣ "መሰረታዊ ክሂል" ወዘተ. እየተባሉ እንደሚጠሩ ገልፀዋሉ፡፡

ስለቋንቋ መማር ብልሀቶች ምንነት የተለያዩ የቋንቋ ጥናት ባለሙያዎች የተለያዩ ብያኔዎችን ሰጥተዋል፡፡ Rubin (1987)፣ O'malley እና ሌሎች(1985)፣ Williams and Burden (1997)፣ Oxford (1989) ቋንቋ የመማር ብልሀቶች ለቋንቋ ትምህርት የሚሆነውን ዕውቀት ለማግኘት፣ ለማጠራቀምና መልሶ ለመጠቀም እንዲሁም ለትምህርቱ ሂደት አመቺ ሁኔታዎችን ለመፍጠር ብለው ተማሪዎች የሚተገብሩት ማናቸውም ቅደም ተከተላዊ ክንውኖችና እቅዶች መሆናቸውን ያብራራሉ፡፡

እንደ Oxford (1990፣8) አገላለፅ ቋንቋ የመማር ብልሀቶች "ተማሪዎች የቋንቋ ትምህርት ሂደት ቀላል፣ ግልፅ፣ ፈጣን፣ ይበልጥ ውጤታማ፣ ቀልጣፋ፣ ማራኪ፣ ምቹና አስደሳች ለማድረግ የሚወስዷቸው የተወሰኑ ተግባሮች ናቸው"፡፡ Cohen (1996) በበኩላቸው የመማር ብልሀቶች ተማሪዎች የቋንቋ ችሎታቸውን ለማሻሻልና በታላሚው ቋንቋ ለመጠቀም የሚመርጧቸው ቅደም ተከተሎች ወይም ተግባሮች እንደሆኑ ይገልፃሉ፡፡ በመሆኑም ቋንቋ የመማር ብልሀቶች ተማሪዎች የቋንቋ ትምህርት በቀላሉ ለመረዳትና በቋንቋ ትምህርታቸው ውጤታማ እንዲሆኑ የሚያስችሏቸው ዘዴዎች ናቸው፡፡ በሌላ በኩል Rubin (1975) ስለብልሀቶች ምንነት ሲያቀርቡ ብልሀቶች ተማሪው በትምህርቱ ሂደት ዕውቀት ለማግኘት ሲባል የሚገለገልባቸው ማንኛውም ቴክኒኮች ወይም መሳሪያዎች እንደሆኑ ይገልፃሉ፡፡ እንደ Oxford (1990) አገላለፅ ደግሞ ብልሀቶች ተማሪዎች የቋንቋ ችሎታቸውን ለማሻሻል ወይም ቋንቋውን ለመረዳት አልመው የሚገለገሉባቸው ዝርዝር ተግባራት ወይም ቴክኒኮች መሆናቸውን ያስረዳሉ፡፡

ከነዚህ ምሁራን ሀሳብ መረዳት የሚቻለው ስለብልሀቶች ጥናት ከተጀመረ ከአራት አስርት ዓመታት በላይ መሆኑን፣ በተለያየ ምሁራን ዘንድ የተለያየ ስያሜ ያላቸው መሆኑንና ተማሪዎች በትምህርቱ ሂደት የሚያጋጥሙ ቋንቋ የመማር እንቅፋቶችን ለማስወገድ ወይም የመማር ሁኔታን ለማቀላጠፍና ዕውቀት ለማግኘት ሲባል የሚጠቀሙባቸው ዘዴዎች መሆናቸውን ነው፡፡

በተጨማሪም Stern (1983) ፣ Wenden and Rubin (1987) ቋንቋ የመማር ብልሀቶችን አስመልክተው በሰጡት ማብራሪያ ተማሪዎች ሁለተኛ ቋንቋቸውን ሲማሩ የሚተገብሯቸውንና የሚያሳዩዋቸውን ባህሪዎችን በሙሉ የሚያጠቃልል የአሰራር ቴክኒኮች መሆናቸውን ይገልፃሉ፡፡

Chamot (1987) ቋንቋ የመማር ብልሀቶችን ሲገልፁ ተማሪዎች የትምህርቱን ሂደት ለማመቻቸት፣ ስነ ልሳናዊ የሆኑ መረጃዎችን ለማስታወስ ብሎ የሚወስዳቸው ቅደም ተከተላዊ አቀራረቦችና ቴክኒኮች መሆናቸውን ነው፡፡

ባጠቃላይ ከላይ ከተለያዩ ምሁራን ከተነሳው ሀሳብ እንደምንረዳው ቋንቋ የመማር ብልሀቶች የቋንቋ ተማሪዎች የቋንቋ ትምህርት በመማር ሂደት አዲስ መረጃ ማግኘትን፣ ያገኙትን መረጃ ማከማቸትንና ያከማቹትን መረጃ በአስፈላጊው ጊዜ መልሶ መጠቀምን ለማፋጠን ወይም ለማቀላጠፍ ዓላማ ሲሉ የሚወስዷቸው ርምጃዎች፣ ቴክኒኮችና ቅደም ተከተላዊ ክንውኖች ሲሆኑ እነዚህም ብልሀቶች ተማሪው የቋንቋ ትምህርቱን ሂደት ምቹ ለማድረግና ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመወጣት የሚያስችሉ መሳሪያዎች መሆናቸውን ነው፡፡

## 2.3. ሰዋስው የመማር ብልሀቶች ምንነት

ሰዋስው የመማር ብልሀቶች ተማሪዎች በሰዋስው ትምህርት ሂደት የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለማለፍና በሰዋስው ትምህርት ውጤታማ ለመሆን የሚከተሏቸው ዘዴዎች ናቸው፡፡ ሰዋስው የመማር ብልሀቶች ምንነትን በተመለከተ Oxford (1990) አጠቃላይ ቋንቋ የመማር ብልሀቶች ምንነት በገለፁበት መንገድ Oxford፣ Rang Lee and Park (2007፣17) ሰዋስው የመማር ብልሀቶች "ተማሪዎች የሰዋስው ትምህርት ሂደት ቀላል፣ ፈጣን፤ ይበልጥ ውጤታማ፣ ይበልጥ ቀልጣፋ፣ ይበልጥ ማራኪ ምቹና አስደሳች ለማድረግ የሚወስዷቸው የተወሰኑ ተግባሮችና ሀሳቦች ናቸው" በማለት ገልፀዋሉ፡፡

ሰዋስው የመማር ብልሀቶች ተማሪዎች አንድን የሰዋስው ትምህርት ይዘት ለመማር ግልፅ፣ ቀላልና ምቹ የሆነው መንገድ የትኛው እንደሆነ፤ እንዲሁም ሰዋስው ነክ ተግባራትን በምን ዓይነት ዘዴ ማከናወን ወይም መተግበር እንደሚችሉ፤ ባጠቃላይ በሰዋስው ትምህርት ሂደት የሚያጋጥሙ እንቅፋቶችን እንዴት መፍታት እንዳለባቸው ወዘተ. የሚሉትን ነገሮች የሚወስኑበት መንገድ ነው፡፡ በተለይም ተማሪዎች በመማሪያ ክፍል ውስጥም ሆነ ውጪ መምህሩን ማግኘት በማይችሉበት አጋጣሚ ሁሉ ተግባራትን በራሳቸው ምርጫና በሚያሻቸው መንገድ እየሰሩ እንዲማሩ የሚያግዟቸው መንገዶች ናቸው፡፡

## 2.4. ቋንቋ በመማር ብልሀቶች አጠቃቀም ላይ ተፅዕኖ የሚያስከትሉ ሁኔታዎች

በመማር ብልሀቶች አጠቃቀም ላይ ተፅዕኖ የሚያስከትሉ በርካታ ሁኔታዎች እንዳሉ Ellis (1994)፣ Chamot (2004)፣ Oxford (1989፤1990)፣ Wenden (1991)፣ Wallace (1992)፣ Chamot (1987)፣ Rubin (1987) ይገልፃሉ። ከነዚህም ጥቂቶቹ ዕድሜ፣ ፆታ፣ የትምህርት ችሎታ፣ የመማር ብልሀት፣ ተነሳሽነት፣ አመለካከት፣ የመማር ስልት፣ ናቸው። የተማሪው ዕድሜ በመማር ብልሀት ላይ ተፅዕኖ ከሚያስከትሉ ሁኔታዎች አንዱ ነው።

ህፃናትና አዋቂ ተማሪዎች የብልሀት አጠቃቀማቸው የተለያየ ነው፤ በተለይም ከአእምሮ ዕድገት ደረጃ አንፃር ሲታይ የተማሪው ዕድሜ በብልሀቶች አጠቃቀም ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ እንዳለው Ellis (1994) ያብራራሉ። አያይዘውም Ellis (1994) ህፃናት ብዙውን ጊዜ ቀለል ያሉ ብልሀቶችን የሚጠቀሙ ሲሆን አዋቂዎች ግን ከበድ ያሉ ብልሀቶችን ሊተገብሩ እንደሚችሉ፤ እንዲሁም ከህፃናት ይልቅ አዋቂዎች ቋንቋ በመማር ብልሀት የተሻሉና ፈጣን መሆናቸውን ይገልፃሉ።

ሌላው በመማር ብልሀት ላይ ተፅዕኖ ከሚያስከትሉ ሁኔታዎች አንዱ ፆታ ነው። እንደ Green and Oxford (1995) አባባል ከወንዶች ይልቅ ሴቶች በብልሀቶች አጠቃቀም የተሻሉ በተለይም ደግሞ ማህበራዊና ስነ ልቦናዊ ብልሀቶችን በይበልጥ እንደሚጠቀሙ ያብራራሉ።

Andersen (2005)፣ እና Wharten (2000) በቋንቋ ችሎታቸው የተሻሉ ተማሪዎች የተለያዩ የመማር ብልሀቶችን የሚጠቀሙ መሆናቸውን ይገልፃሉ። በሌላ በኩል Ellis (1994) በቋንቋ ችሎታቸው ውጤታማ የሆኑ ተማሪዎች ውጤታማ ካልሆኑ ተማሪዎች በተሻለ ደረጃ የመማር ብልሀቶችን እንደሚጠቀሙ፣ በተለይም በቋንቋ ችሎታቸው የተሻሉ ተማሪዎች በኢቀጥተኛ ብልሀቶች አጠቃቀም የተሻሉ እንደሆኑ ያብራራሉ።

የመማር ብልሀቶች ቋንቋ በመማር ብልሀቶች ላይ ተፅዕኖ ከሚያስከትሉ ሁኔታዎች አንዱ ነው። ቀጥተኛ ብልሀቶች ብዙውን ጊዜ ከተወሰኑ የመማር ተግባራት ዓላማዎች ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ሲኖራቸው ኢቀጥተኛ ብልሀቶች ግን በሁሉም የመማር ተግባራት ላይ አንድ ናቸው (Chamot፣1987)::

ሌላው በመማር ብልሀት ላይ ተፅዕኖ አድራጊ ተነሳሽነት ሲሆን ለቋንቋ ትምህርት የበለጠ መነሳሳት ያላቸው ተማሪዎች ዝቅተኛ መነሳሳት ካላቸው ተማሪዎች ይልቅ የበለጠ የመማር ብልሀቶችን እንደሚጠቀሙ (Oxford፣1989) ይገልፃሉ፡፡

ተማሪዎች ለቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት በመማር ብልሀት ላይ ተፅዕኖ ከሚያስከትሉ ሁኔታዎች አንዱ ነው፡፡ ይህን አስመልክተው Oxford (1990) ሲያብራሩ ለቋንቋ ትምህርት አሉታዊ አመለካከት ያላቸው ተማሪዎች የመማር ብልሀት አጠቃቀማቸው ዝቅተኛ እንደሆነ ይገልፃሉ፡፡

በሌላ በኩል Oxford (1990) የተለያየ የመማር ስልት ያላቸው ተማሪዎች የተለያየ የመማር ብልሀቶችን እንደሚጠቀሙ ይገልፃሉ፡፡ የተለያየ የመማር ብልሀት የሚጠቀሙ ተማሪዎች ደግሞ በቋንቋ ትምህርት ውጤታማ ናቸው፡፡ እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩና ሌሎችም ቋንቋ በመማር ብልሀቶች አጠቃቀም ላይ ተፅዕኖ የሚያስከትሉ ሁኔታዎች አሉ፡፡ በመሆኑም ከላይ የተዘረዘሩ ቋንቋ በመማር ብልሀቶች አጠቃቀም ላይ ተፅዕኖ የሚያስከትሉ ሁኔታዎች በሰዋስው ትምህርት መማር ብልሀቶች አጠቃቀም ላይም ተፅዕኖ የሚያስከትሉ ሁኔታዎች ናቸው፡፡

## 2.5. ሰዋስው የመማር ብልሀቶች በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ያለው ሚና

ሰዋስው የመማር ብልሀቶችን ሚና ለማመልከት ሌሎች ቋንቋ የመማር ብልሀቶች ሚና ማየቱ ተመራጭነት አለው፡፡ ምክንያቱም ሰዋስው የመማር ብልሀቶች ሚና ከቋንቋ መማር ብልሀቶች ሚና የሚመነጩ በመሆናቸው ነው፡፡ Oxford (1990) ቋንቋ የመማር ብልሀቶች ተማሪዎች የታላሚውን ቋንቋ ተግባቦታዊ ብቃት ለማዳበር እንደሚያግዟቸው ያስረዳሉ፡፡ እንደ Canale and Swain (1980) እና Halliday (1994) አገላለፅ አንድ ተማሪ ተግባቦታዊ ችሎታ አዳብሯል የሚባለው አራቱን ተግባቦታዊ ችሎታ ሲያዳብር ነው፡፡ እነሱም የሰዋስው፣ የማህበረ ስነልሳናዊ፣ የዲስኩርና የብልሀት ብቃት ናቸው፡፡ ሰዋስው የመማር ብልሀቶች ተማሪዎች ተግባቦታዊ ብቃት ደረጃ ላይ እንዲደርሱ ከሚያስችሏቸው መንገዶች አንዱ ነው፡፡ በተለይ የማካካሻ ብልሀቶች ተማሪዎች ሰዋስው ብቃት እንዲያዳብሩ ሲያግዟቸው፤ ማህበራዊ ብልሀቶች ደግሞ ማህበረ ስነ ልሳናዊ ብቃት እንዲያዳብሩ ያግዟቸዋል፡፡

ቋንቋ የመማር ብልሀቶች ተማሪዎች ቋንቋ በመማር ሂደት ከመምህሩ ጥገኝነት ተላቅቀው ራሳቸውን ችለው ቋንቋ የመማር ችሎታቸውን እንዲያዳብሩና በራስ የመተማመን ስሜት እንዲኖራቸው ለማድረግ ይረዷቸዋል (Oxford 1990)፡፡

Hutimen (1996) በበኩላቸው የመማር ብልሀቶች ሚና ሲገልፁ ተማሪው በተግባቦት ሂደት በሰዋስው ችሎታ ማነስ ተግባቦቱ እንዳይቋረጥ፤ የቋንቋ ችሎታና የአጠቃቀም ብቃት እንዲዳብር እንደሚረዷቸው ገልፀዋሉ፡፡

በተጨማሪም Oxford (1994) ቋንቋ የመማር ብልሀቶች ሚና በተመለከተ ሲያብራሩ ተማሪዎች የተማሩትን የቋንቋ ትምህርት ይዘት በአእምሮአቸው አከማችተው ለረዥም ጊዜ ማስታወስ እንዲችሉና በፈለጉት ጊዜ መልሰው እንዲጠቀሙ ያስችላሉ፤ ታላሚውን ቋንቋ በመማሪያ ክፍል ውስጥም ሆነ ውጪ በራሳቸው ጥረት እንዲማሩ እና ራስ መር ተማሪ እንዲሆኑ እንደሚረዷቸው ይገልፃሉ፡፡ በመሆኑም ሰዋስው የመማር ብልሀቶች ሚናም ከቋንቋ መማር ብልሀቶች ሚና የሚመነጩ ሲሆን ተማሪዎች በሰዋስው ትምህርት ራሳቸውን በራሳቸው በመደገፍ ከመምህሩ ጥገኝነት ተላቅቀው በራሳቸው ጥረት ሰዋስው የመማር ዕውቀት እንዲያዳብሩ ይረዷቸዋል፡፡

## 2.6. ሰዋስው የመማር ብልሀቶች አከፋፈል

ሰዋስው የመማር ብልሀቶች አከፋፈል ቋንቋ ከመማር ብልሀቶች አከፋፈል የሚመነጩ በመሆናቸው አስቀድመን ቋንቋ የመማር ብልሀቶች አከፋፈልን ማየቱ የተሻለ ነው፡፡ ቋንቋ የመማር ብልሀቶችን የተለያዩ የቋንቋ ባለሙያዎች በተለያየ መንገድ ከፍሏቸዋል፡፡ አከፋፈላቸውን ስንመለከት ግን በቃላት ደረጃ ይለያዩ እንጂ በሃሳብ ደረጃ አንድ ናቸው፡፡ Rubin (1981) ተማሪዎች የሚገለገሉባቸውን ቋንቋ የመማር ብልሀቶችን ቀጥተኛ እና ኢቀጥተኛ ብለው በሁለት ሰይሟቸዋል፡፡ ቀጥተኛ የመማር ብልሀቶች ተማሪዎች የቋንቋ ተግባራትን እያከናወኑ እንዲማሩ በቀጥታ እገዛ የሚያደርጉ ብልሀቶች ሲሆኑ እነሱም፡- ማብራራት፣ መቆጣጠር፣ ማስታወስ፣ መገመት፣ መተንተን(ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር) እና መለማመድ ናቸው፡፡ ኢቀጥተኛ የመማር ብልሀቶች ደግሞ ተማሪዎች የትምህርታቸውን ሂደት ለማመቻቸት ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ የሚገለገሉባቸው ብልሀቶች ሲሆኑ እነሱም ለታላሚው ቋንቋ የመጋለጥ ዕድል መፍጠርና ለልምምድ መነሳሳት ናቸው፡፡ አያይዘውም Rubin (1981) ለልምምድ መነሳሳት ተግባቦታዊ ብልሀትንም የሚያካትት መሆኑን ገልፀዋሉ፡፡

በተጨማሪም Rubin (1987) ተማሪዎች ቋንቋን ለመማር የሚገለገሉባቸውን ብልሀቶች የመማር ብልሀቶች፣ ተግባቦታዊ ብልሀቶችና ማህበራዊ ብልሀቶች ብለው በሶስት መድቧቸዋል፡፡ የመማር ብልሀቶች የቋንቋ ተማሪዎች የታላሚውን ቋንቋ ችሎታቸውን ለማዳበር በቀጥታ የሚተገብሩት ሲሆን አእምሮታዊና ልዕለ አእምሮታዊ ብልሀቶች ተብለው በሁለት ዋና ዋና ምድቦች እንደሚከፈሉም ገልፀዋሉ፡፡

አእምሮታዊ ብልሀቶች ተማሪዎች በቋንቋ ትምህርት ሂደት ተግባራዊ የሚያደርጓቸው ቅደም ተከተሎች ወይም የችግር ማቃለያ ዘዴዎች ሲሆኑ ልዕለ አእምሮታዊ ብልሀቶች ደግሞ ተማሪዎች የቋንቋ ትምህርት ሂደት ለማቀድ፣ ለማደራጀትና ለመቆጣጠር የሚገለገሉባቸው ብልሀቶች መሆናቸውን አመልክተዋሉ፡፡ ተግባቦታዊ ብልሀቶች ተማሪዎች ኢቀጥተኛ በሆነ መንገድ ከታላሚው ቋንቋ ተማሪዎች ጋር ግንኙነት ወይም ተራክቦ በማድረግ ቋንቋን የሚማሩበት ብልሀት ነው፡፡ ማህበራዊ ብልሀቶች ተማሪዎች ኢቀጥተኛ በሆነ መንገድ ከማህበረሰቡ ጋር ተሳትፎ በማድረግ ለታላሚው ቋንቋ በመጋለጥ ቋንቋን የሚለምዱበት ብልሀት ነው፡፡

O'malley (1985) ተማሪዎች የሚገለገሉባቸውን ቋንቋ የመማር ብልሀቶችን አእምሮታዊ፣ ልዕለ አእምሮታዊና ማህበራዊ/ስሜታዊ ብልሀቶች ብለው በሶስት መድቧቸዋል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ O'malley and Chamot (1990) ጥሩ የቋንቋ ተማሪዎች የሚገለገሉባቸውን የመማር ብልሀቶችን አእምሮታዊ፣ ልዕለ አእምሮታዊና ማህበራዊ /ስሜታዊ/ ብልሀቶች ብለው በሶስት ሰይሟቸዋል፡፡ አእምሮታዊ ብልሀቶች ተማሪዎች በቀጥታ የታላሚውን ቋንቋ ተግባራት ሲያከናውኑና ሲተገብሩ የሚጠቀሙባቸው ብልሀቶች ናቸው፡፡ ልዕለ አእምሮታዊ ብልሀቶች ደግሞ ተማሪዎች የሚማሩትን የቋንቋ ትምህርት ክንውን ማቀድ፣ መቆጣጠርና ራሳቸውን መገምገም እንዲችሉ እገዛ የሚያደርጉ ብልሀቶች ናቸው፡፡ ማህበራዊ/ስሜታዊ ብልሀቶች ተማሪዎች ከሌሎች ጋር ግንኙነት በመፍጠር ወይም የተለያዩ ስሜቶችን በመቆጣጠር ቋንቋን የሚማሩበት ብልሀት መሆናቸውን ገልፀዋሉ፡፡

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ Oxford (1990) የRubin (1981)ን ሞዴል በመጠቀም አጠቃላይ ቋንቋ የመማር ብልሀቶችን ቀጥተኛና ኢቀጥተኛ የመማር ብልሀቶች ብለው በሁለት ዐበይት ክፍሎች መድበዋሉ፡፡

ባጠቃላይ ሲናያቸው ግን O'malley እና ሌሎች (1985)፣ O'malley and Chamot (1990) ቋንቋ የመማር ብልሀቶች አከፋፈል አእምሮታዊ፣ ልዕለ አእምሮታዊና ማህበራዊ ወይም ስሜታዊ ብልሀቶችን ያጠቃልላሉ፡፡ ልዩነታቸው O'malley እና ሌሎች (1985)፣ O'malley

and Chamot (1990) ማህበራዊ ወይም ስሜታዊ ብልሀቶች ብሎ እንደአማራጭ የወሰዳቸውን Oxford (1990) ስሜታዊ እና ማህበራዊ ብሎ ለሁለት ከከፈላቸው በሁዋላ በያንዳንዳቸው ስር ሌሎች ዝርዝር ብልሀቶችን አካትተዋሉ።

Rubin ደግሞ በሁለቱም ጥናታቸው ተግባቦታዊ ብልሀት አካትተዋሉ፤ ይሁን እንጂ ተግባቦታዊ ብልሀቶች በአንዳንድ ምሁራን ዘንድ የማካካሻ ብልሀቶች በመባል እንደሚታወቁ Littlemore (2001) ይገልፃሉ። Rubin (1981) and Oxford (1990) ቋንቋ የመማር ብልሀቶችን ቀጥተኛ እና ኢቀጥተኛ ብለው በሁለት በመክፈል ሌሎች ዝርዝር ብልሀቶችን ያጠቃልላሉ። ባጠቃላይ የሁሉንም ምሁራን አከፋፈል ሲናያቸው በቃላት ደረጃ እንጂ በሀሳብ ደረጃ አንድ ናቸው። ሰዋስው የመማር ብልሀቶች አከፋፈልም ከዚሁ ቋንቋ ከመማር ብልሀቶች አከፋፈል የመነጨና ቋንቋ የመማር ብልሀቶች አካላት ናቸው።

በመሆኑም ለዚህ ጥናት አጥኚው የሚከተለው የOxfordን ቋንቋ የመማር ብልሀቶች አከፋፈልን ነው። ምክንያቱም የመማር ብልሀቶችን ዘርዘር አድርገው በማቅረባቸው፣ የቃላት አጠቃቀማቸው ቀላል በመሆኑ፤ የቅርብ ጊዜ ጥናት በመሆኑ፣ እንዲሁም በሌሎች ጥናቶች የቀረቡ የመማር ብልሀቶችን አካትቶ የያዘ በመሆኑ ነው። ከዚህ ቀጥሎ ለሰዋስው ትምህርት የሚሆኑ ከOxford (1990) ቋንቋ ከመማር ብልሀቶች አከፋፈል የመነጨ ሰዋስው የመማር ብልሀቶች በዝርዝር ቀርበዋሉ።

### 2.6.1. ቀጥተኛ ሰዋስው የመማር ብልሀቶች

እንደ Oxford (1990) አገላለፅ ቀጥተኛ የመማር ብልሀቶች ተማሪው በቀጥታ የታላሚውን ቋንቋ ተግባራት እየሰራና በትምህርቱ ሂደት እየተሳተፈ እንዲማር በቀጥታ እገዛ የሚያደርጉ ናቸው። አያይዘውም Oxford ሁሉም ቀጥተኛ የመማር ብልሀቶች የአዕምሮ ስራ ሂደትን የሚፈልጉ መሆናቸውን ይገልፃሉ። ሰዋስው ለመማር ተገቢ የሆኑ ቀጥተኛ የመማር ብልሀቶችም የማስታወስ፣ አእምሮታዊና ማካካሻ ብልሀቶች በሚባሉ ሶስት ንዑሳን ምድቦች ይካተታሉ።

#### 2.6.1.1. የማስታወስ ብልሀቶች

Oxford (1990) የማስታወስ ብልሀቶች ተማሪዎች በቋንቋ ትምህርት ሂደት የሚያገኟቸውን አዳዲስ ሀሳቦች በአእምሯቸው መዝግበው የረዥም ጊዜ ትውስታ በመፍጠር በአስፈላጊው ጊዜ ሁሉ መልሰው መገልገል እንዲችሉ የሚያግዙ ብልሀቶች እንደሆኑ ይገልፃሉ።

የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ችግሮች አንዱ ከዚህ ቀደም ሲል በአንድ ወቅት የተማሯቸውን መዋቅሮችን በሌላ ጊዜ ወይም አዲሱን የሰዋስው ትምህርት በመማር ሂደት አስታውሰውና መልሰው መጠቀም አለመቻል ነው፡፡ የማስታወስ ብልሀቶች የቋንቋ ተማሪዎች ይህንና የመሳሰሉ ችግሮችን መፍታት እንዲችሉ ይረዷቸዋል፡፡ በመሆኑም የማስታወስ ብልሀቶች ተማሪዎች የሰዋስው ትምህርት ተግባራትን በአእምሯቸው አከማችተው እንዲይዙና ለረዥም ጊዜ አስታውሰው እንዲጠቀሙ የሚያገለግሉ ብልሀቶች ናቸው፡፡ ሰዋስውን ለመማር የሚያገለግሉ ዝርዝር ብልሀቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ማቧደን - የማስታወስ ችግርን ለመቅረፍ ሰዋስውን ለማጥናት በሚቀል መንገድ እንደየርዕሳቸው በቡድን በቡድን ማደራጀት ነው፡፡ ለምሳሌ፡- በምዕላድ ክፍላቸው፣ በቃል ክፍላቸው፣ በሀረግ ዓይነታቸው፣ በዐረፍተ ነገር ዓይነታቸው፣ በዓረፍተ ነገር ክፍላቸው ወዘተ. እየቦደኑ ማስታወስ ነው፡፡ ተመሳሳይነት ያላቸውን የሰዋስው መዋቅሮችን አንድ ላይ በመመደብ ለትውስታ የማመቻቸት ብልሀት ነው፡፡

- ማያያዝ - አዲሱን የሰዋስው ትምህርት ከዚህ በፊት ከሚያውቁት ከሌላ ነገር ጋር በማገናኘት አእምሯዊ ትስስር መፍጠር፡፡ ለምሳሌ፡- መምህሩ ክፍል ውስጥ ሲያስተምር ከነበረበት ሁኔታ አንፃር፣ በመፅሀፉ ውስጥ የሰዋስው

- ምስል መፍጠር - የታላሚውን ቋንቋ ሰዋስው ትምህርት በዓይን ከሚታዩና በእጅ ከሚዳሰሱ ነገሮች ጋር በማገናኘት አእምሮአዊ ምስል በመፍጠር ለትውስታ ማመቻቸት፡፡ ለምሳሌ፡- ከቁሳቁሶች፣ ከስዕሎች፣ ከቦታዎች፣ ከድምፆች፣ ከፎቶዎች ወዘተ…

- መከለስ - የተማሩት የሰዋስው ትምህርት የረዥም ጊዜ ትውስታ እንዲኖረው ዘውትር ክለሳ ማድረግ፡፡ ለምሳሌ፡- የአንድ ምዕራፍ ትምህርት ሰብስብ አድርጎ በአንድ ገፅ ማጠቃለል፣ በአስተዋፆ መልክ ማስፈር

- የሰውነት እንቅስቃሴን መጠቀም - የተለያዩ የሰዋስው ትምህርት ተግባራትን አካላዊ ምላሽ በመጠቀም ትውስታ የመፍጠር ብልሀት ነው፡፡ ለምሳሌ፡- መነሳትን በመቆም ማስታወስ ፣ መራመድን በመሄድ ማስታወስ

### 2.6.1.2 አእምሮታዊ (ግንዛቤያዊ) ብልሀቶች

አእምሮታዊ ብልሀቶች ተማሪዎች በሰዋስው ትምህርት ተግባራት ላይ በቀጥታ በሚሳተፉበት ጊዜ የሚገለገሉባቸው ብልሀቶች ሆነው የመገንዘብ ሁኔታን ለማዳበር የሚደረጉ ብልሀቶች ናቸው፡፡ አእምሮታዊ ብልሀቶች በቋንቋ ተማሪዎች በስፋት በተግባር ላይ የሚውል ሆነው ተማሪዎች የቋንቋ ትምህርት ተግባራትን መረዳትና መገንዘብ እንዲችሉ እገዛ የሚያደርጉ ብልሀቶች ናቸው (Oxford 1990፣ O'malley and Chamot 1990 እና Cohen 1998):: በመሆኑም አእምሮታዊ ብልሀቶች ተማሪዎች በሰዋስው ትምህርት ተግባራት ላይ በቀጥታ በሚሳተፉበት ጊዜ የሚገለገሉባቸው ብልሀቶች ሆነው ሰዋስውን የመገንዘብ ወይም የመረዳት ሁኔታን ለማዳበር የሚደረጉ ብልሀቶች ናቸው፡፡ ለአእምሮታዊ ብልሀት የሚሆኑ ዝርዝር ብልሀቶቹም፡-

- መደጋገም/መለማመድ/ - የታላሚውን ቋንቋ ሰዋስው ህጎችን በማውጣት፤ በአእምሮ ውስጥ በማመላለስ፤ ተግባራትን ደጋግሞ በመፃፍ ወይም በማለት ልምምድ ማድረግ ነው፡፡ በልምምድ ወቅት ለምሣሌ፡- ሰፊ የሆነውን የሰዋስው መዋቅር ቀመር በማበጀት አሳጥሮ ማቅረብ

- ምንጭ መጠቀም - ለታላሚው ቋንቋ ሰዋስው ትምህርት የሚሆኑ ሌሎች የመረጃ ምንጮችን መጠቀም፡፡ ለምሳሌ፡- ሰዋስው መፅሀፍ፣ መማሪያ መፅሀፍ፣ ወዘተ.

- ሚድያዎችን መከታተል - የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስው ዕውቀት ለማገናዘብ የተለያዩ ሚዲያዎችን የመጠቀም ብልሀት ነው፡፡ ለምሳሌ፡- ሬዲዮ፣ ቴሌቭዥን፣ ኢንተርኔት፣ ወዘተ. የመከታተል ብልሀት ነው፡፡

- መተርጐም - የታላሚውን ቋንቋ ሰዋስው አጠቃቀም ወደአፍ መፍቻ ቋንቋ ሰዋስው አጠቃቀም ተርጉሞ የመጠቀም ብልሀት ነው፡፡ ለምሳሌ፡- ከአማርኛ ወደ ወላይትኛ

- ማሸጋገር- ቀደም ሲል የተማሩትን የሌላ ቋንቋ የሰዋስው ዕውቀት የታላሚውን ቋንቋ ሰዋስው ለመረዳት መጠቀም፡፡ ለምሳሌ፡- የእንግልዘኛውን ወይም የዎላይተኛዉን ለአማርኛ ቋንቋ መጠቀም፣

- መተንተን - የሰዋስው ትምህርትን ከአጠቃላይ ወደዝርዝር ወይም ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ በሆነ መንገድ የመማር ብልሀት ነው፡፡
- ማስታውሻ መያዝ - የታላሚውን ቋንቋ የሰዋስው ፅንሰ ሀሳቦችን እና አጠቃቀሞችን አጠር አድርጎ ማስታውሻ ደብተር ላይ የማስፈር ብልሀት ነው፡፡
- ማነፃፀር - የአፍ መፍቻ ቋንቋ ሰዋስው ከታላሚው ቋንቋ ሰዋስው ጋር እያነፃፀሩ የመጠቀም ብልሀት ነው፡፡
- ማድመቅ - ከአንድ ፅሁፍ ውስጥ ጠቃሚ ለሆኑ ሰዋስዋዊ መረጃዎች ትኩረት ወይም አፅንኦት የመስጠት ብልሀት ነው፡፡ ለምሳሌ፡- ከስሩ በማስመር፣ ኮከብ ምልክት በማድረግ፣ ተቃራኒ ቀለም ያለውን ብዕር በመጠቀም መማር(Oxford 1990)::

### 2.6.1.3. የማካካሻ ብልሀቶች

የማካካሻ ብልሀቶች ተማሪዎች በቋንቋ አጠቃቀም ሂደት በሰዋስው ዕውቀት ማነስ የተነሳ በሰዋስው ትምህርት ላይ የሚያጋጥሟቸውን ችግሮችን ለማለፍ ወይም ጉድለቱን ለመሙላት የሚገለገሉባቸው ብልሀቶች ናቸው፡፡ ይህን ብልሀት አንዳንድ ምሁራን እንደየአመለካከታቸው ከሌሎች ብልሀቶች ጋር ያጠቃልላሉ፡፡ አንዳንዶቹ በሌላ ብልሀት ይተካሉ፡፡ ለምሳለሌ፡- O'malley and Chamot (1990) በአእምሮታዊ ብልሀት ስር ይመድቡታል፡፡ Cohen (1998) ቋንቋ የመጠቀም ብልሀቶች ከሚለው ጋር ይመድቡታል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ Bialystk (1978) ተግባቦታዊ ብልሀቶች በሚለው ይተካሉ፡፡ ዝርዝር ብልሀቶች የሚከተሉት ናቸው፤

- መገመት - እንግዳ የሆኑ ሰዋስዋዊ ተግባራት ሲያጋጥሙ በብልሀት ላይ የተመሰረተ ግምት መስጠት፡፡ ለምሳሌ፣- ተማሪዎች በክፍል ውስጥም ሆነ ውጭ ጭውውት ወይም ቃለ ምልልስ በሚያደርጉበት ጊዜ ለሚፈጠረው ሰዋስው ችግር የሚጠቀሙበት ብልሀት ነው፡፡
- አካላዊ እንቅስቃሴ መጠቀም - ምልክታዊ የሆኑ ፍንጮችን በመጠቀም አካላዊ ምላሽ የመስጠት ብልሀት፡፡ ለምሳሌ፡- የእጅ እንቅስቃሴ፣ የአንገት እንቅስቃሴ፣ የግንባር መኮሳተር፣ የዓይን ጥቅሻ ወዘተ.

- መለማመድ - በንግግር ወይም በፅሁፍ ጊዜ ሀሳብን መግለፅ ሲያቅት ወይም ሲያስቸግር ተመሳሳይ ይዘት ባለው በሌላ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ልምምድ የማድረግ ብልሀት ነው (Oxford 1990)፡፡

### 2.6.2. ኢቀጥተኛ ሰዋስው የመማር ብልሀቶች

ኢቀጥተኛ ብልሀቶች ተማሪዎች በትምህርቱ ሂደት በቀጥታ እየተሳተፉ ሳይሆን ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ ለሰዋስው ዕውቀት መዳበር እገዛ የሚያደርጉ ናቸው፡፡ እነዚህ ብልሀቶች ተማሪዎች የትምህርታቸውን ሂደት ለማመቻቸት የሚገለገሉባቸው ብልሀቶች ናቸው፡፡

በኢቀጥተኛ ብልሀቶች ስር ሶስት ንዑሳን ብልሀቶች ይካተታሉ፡፡ እነሱም፡- ልዕለ አእምሮታዊ፣ ስሜታዊና ማህበራዊ ብልሀቶች ናቸው፡፡

#### 2.6.2.1. ልዕለ አእምሮታዊ ብልሀቶች

ልዕለ አእምሮታዊ ብልሀቶች ተማሪዎች የሰዋስውን ትምህርት በማቀድ፣ የሰዋስው ትምህርት ተግባራትን በመቆጣጠር፣ የራሳቸውን በንግግርም ይሁን በፅሁፍ ወቅት የሚከሰቱ የሰዋስው ስህተቶችን በራሳቸው በመገምገም ትምህርቱን እንዲማሩ የሚያግዙ ብልሀቶች ናቸው፡፡ ይህ ብልሀትም በቋንቋ ተማሪዎች በስፋት ተግባር ላይ የሚውል መሆኑን O'malley and Chamot (1990) ገልፀዋሉ፡፡ ለአእምሮታዊ ብልሀት የሚሆኑ ዝርዝር ተግባራት የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ማቀድ - ተማሪው ለሰዋስው ትምህርት ግብ የማስቀመጥ፣ ከትምህርቱ በኋላ ምን እንደሚጠበቅባቸው አስቀድሞ የመወሰን ብልሀት ነው፡፡ የመምህሩ ብቻ ሳይሆን ተማሪው ለራሱ ከዚህ ሰዋስው ትምህርት በኋላ "እንዲህ" አደርጋለሁ ብሎ ግብ የማዘጋጀት ብልሀት ነው፡፡ አጠቃላይና ዝርዝር ዓላማ የመንደፍ ሂደት ነው፡፡

- መርጦ ማተኮር - ለሰዋስው ትምህርት ትኩረት ሰጥቶ ለመማር መወሰን፤ ቅድሚያ ለሚፈልጉ ይዘቶች ቅድሚያ የመስጠት ብልሀት ነው፡፡

- ማደራጀት - የሰዋስው ትምህርት ለመማር ምቹ ሁኔታ መፍጠር፣ ፕሮግራም ማዘጋጀትና ቅደም ተከተል ማስያዝ፣ የተማሯቸውን በሙሉ ሰብሰብ አድርጎ መልክ ማስያዝ፡፡

- ራስን መቆጣጠር - ተማሪው የራሱን ስህተት በራሱ የሚለይበት ብልሀት ነው፡፡ የሌላው አካል ጣልቃ ገብነት ሳይኖር ተማሪው የራሱን የሰዋስው አጠቃቀም ስህተት ራሱ የሚያርምበት፣ ሰዋስውን በትክክለኛው መንገድ መጠቀም አለመጠቀሙን ራሱን የሚቆጣጠርበት ዘዴ ነው፡፡

- ራስን መገምገም - የሰዋስው ትምህርት ውጤት በመመርመር ካለፈው የበለጠ ለውጥ ማሳየት አለማሳየቱን፣ ማወቅ አለማወቁን ለማወቅ ራሱን በራሱ የሚፈትንበት ብልሀት ነው፡፡ የራሱን ጠንካራና ደክማ ጎን ራሱ የሚፈትሽበት ቴክኒክ ነው (O'malley and Chamot (1990)::

### 2.6.2.2. ስሜታዊ ብልሀቶች

ተማሪዎች ፍርሀትንና ጭንቀትን ለመቆጣጠር የሚጠቀሙባቸው ብልሀቶች ናቸው፡፡ አብዘኛውን ጊዜ ከተማሪው ስሜትና መነቃቃት ጋር የተቆራኙ ሆነው ተማሪው በሰዋስው ትምህርት ሂደት የሚያጋጥመውን ፍርሀት የሚቆጣጠርበት ብልሀት ነው፡፡ ዝርዝር ብልሀቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ጭንቀትን መቀነስ - ተማሪው የሰዋስው ትምህርት ሂደት ከመጀመሩ በፊት የጭንቀት፣ የድካምና የድብርት ስሜት በመቀነስ አእምሮን የሚያዝናናበት ብልሀት ነው፡፡ ተማሪው ጭንቀቱን ሲቀንስ ለትምህርቱ ያለው አመለካከት አዎንታዊ ይሆናል፤ ጭንቀትን ለመቀነስ በረዥሙ መተንፈስ፣ ማሰላሰል፣ ሙዚቃ መጠቀም፣ ማዝናናት ወዘተ. አእምሮ የሚፈልገውን ነገር ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

- ራስን መሸለም - በሰዋስው ትምህርት ውጤታማ ሲሆኑ ራስን የማድነቅ ወይም የማሞገስ፤ የመሸለም ብልሀት ነው፡፡ ለምሳሌ፡- መጽሀፍ በመግዛት፣ በመዝናናት

- ራስን ማበረታታት - ሰውነታችን ወይም አእምሯችን የሚፈልገውን ነገር በመስጠት አካላችንን የማበረታታት ብልሀት ነው፡፡ በታላሚው ቋንቋ ሲናገሩ ለሚፈጠረው ሰዋስው ስህተት ሳይሸማቀቁ ለመናገር ራስን የማበረታታት ብልሀት ነው፡፡

- ሀላፊነትን መቀበል - በሰዋስው ትምህርት ሂደት የሚያጋጥሙ ማንኛውም ተግባራት ለማከናወን ሀላፊነት የመቀበል ብልሀት ነው፡፡ በትምህርቱ ሂደት ስህተት ቢፈጠርም ስሜትን በመቆጣጠር በንቃት በመሳተፍ ግደታን መወጣት፡፡ ለምሳሌ፡- በንግግር ፣ በጭውውት፣ በውይይት፣ በገለፃ ጊዜ ወዘተ…

- አዎንታዊ ገለፃ መስጠት - የሰዋስው ትምህርት ተግባራትን ማከናወን እችላለሁ፣ አደርጋለሁ ወዘተ. ብሎ አዎንታዊ የሆነ ሀሳብ ማሰብ፡፡ የ"ይቻላል" መርህ የመከተል ብልሀት ነው፡፡

- ስሜትን ማጋራት - በሰዋስው ትምህርት ሂደት የሚያድርባቸውን ስሜት ለሌሎች የማካፈል ብልሀት፣ ከሌሎች ሰዎች ጋር የመወያየት ብልሀት ነው፡፡ ለምሳሌ፡- ለመምህራን፣ ለክፍል ጓደኞች ወዘተ.

- የራስ አካል ማዳመጥ (መተኛት ከፈለገ መተኛት፣ መጫወት ከፈለገ መጫወት፣ ማጥናት ከፈለገ ማጥናት ወዘተ.(Oxford 1990)::

### 2.6.2.3. ማህበራዊ ብልሀቶች

ማህበራዊ ብልሀቶች ተማሪዎች ከክፍል ጓደኞቻቸው ጋር እየተደጋገፉና እርስ በርስ ሀሳባቸውን እየተለዋወጡ የሚያስቸግሯቸውን የሰዋስው ተግባራት መምህሮቻቸውን ወይም በቋንቋው ብቃት ያላቸውን ሰዎች እየጠየቁና ከታላሚው ቋንቋ ተናጋሪ ህብረተሰብ ጋር ማህበራዊ ግንኙነት እያደረጉ እንዲማሩ የሚያገለግሉ ብልሀቶች ናቸው፡፡ በዚህ ስር ተማሪዎች የሚያከናውኗቸው ዝርዝር ብልሀቶች፡-

- መተባበር - የሰዋስው ትምህርት ከክፍል ጓደኞቹ ጋር በጥንድ ወይም በቡድን ህብረት ፈጥሮ መስራት፣ መለማመድ

- ማብራሪያ መጠየቅ - መምህሩን ወይም በታላሚው ቋንቋ ዕውቀት ያላቸውን ሰዎች ገለፃዎችን፣ ማብራሪያዎችን፣ ምሳሌዎችን፣ ማስተካከያዎችን ወዘተ. የመጠየቅ ብልሀት ነው፡፡

- ባህልን ማዳበር - ስለታላሚው ቋንቋ ተናጋሪዎች ባህልና አኗኗር ያላቸውን ግንዛቤ የማዳበር ብልሀት ነው (Oxford 1990)::

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱ ቋንቋ ከመማር ብልሀቶች የመነጩ ሰዋስው የመማር ብልሀቶች ሲሆኑ የሰዋስው ዕውቀት ለማዳበር አስፈላጊዎች ናቸው፡፡

ቢሆንም ሁሉም ተማሪዎች ሁሉንም ሰዋስው የመማር ብልሀቶችን በአንድ ዓይነት መንገድ ይጠቀማሉ ለማለት አያስደፍርም፤ እንደየተማሪዎቹ ዕድሜና ፆታ፣ እንደየተማሪዎቹ ባህላዊ ዳራና የዕውቀት ደረጃ፤ የሚገለገሉባቸው ብልሀቶች አጠቃቀማቸውም ይለያያል፡፡ ይህንን ሀሳብ አስመልክቶ Richard (1994) ሲያብራሩ በተመሳሳይ አካባቢና በተመሳሳይ ማስተማሪያ ዘዴ ከተማሩ ተማሪዎች መካካል አንዳንዶቹ ውጤታማ ሲሆኑ አንዳንዶቹ ግን ውጤታማ አይደሉም፡፡ ለዚህ ምክንያቱ የተማሪዎቹ የመማር ብልሀት መለያየት ነው፡፡ በመሆኑም የታላሚው ቋንቋ ተማሪዎች የሰዋስው ችሎታቸውን ለማዳበር ሀላፊነትን ወስደው ሰዋስው የመማር ብልሀቶችን መሰረት አድርገው በራሳቸው ጥረት ታላሚውን ቋንቋ ሰዋስው እንዲማሩ ማለማመድ ይገባል፡፡

## 2.7 የቀደምት ጥናቶች ውጤት

የዚህ የቀደምት ጥናቶች የሚለዉ ክፍል ዓላማ ከዚህ ጥናት ጋር ግንኙነት ያላቸዉ የቀደምት የጥናት ሰራዎችን መቃኘት ነዉ፡፡ በዚህ ርዐስ ቀደምት ስራዎች ስፋትና ጥልቀት ባለዉ መንገድ ይዳሰሳሉ፡፡

ሰዋስው ከመማር ብልሀቶች ጥናት ጋር ዝምድና ባላቸው በሌሎች ቋንቋ ዘርፎች መማሪያ ዙሪያ የተሰሩ የተወሰኑ ጥናታዊ ፅሁፎችን ለመዳሰስ ተሞክሯል፡፡ ከነዚህም ውስጥ፡-

ሠፋ (1995) የጉመር ጉራግኛ አፍ ፈት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ሲናገሩ የሚጠቀሙባቸው ተግባቦታዊ ብልሀቶች ትንተና በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት በቋንቋዎች ጥናት ተቋም አማርኛ ማስተማር (TEAM) ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ ነው፡፡ የጥናቱ ዓላማ አማርኛን እንደሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ የጉመር ጉራግኛ አፈ ፈት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች፣ የቀሰሙትን የተወሰኑ የአማርኛ ቋንቋ ዕውቀት በመጠቀም ሀሳባቸውን በንግግር ለመግለፅ ሲሞክሩ፣ የሚያጋጥማቸውን የቋንቋ ችግር ለመፍታት(ለመቋቋም) የሚጠቀሙባቸውን ተግባቦታዊ ብልሀቶች መመርመር ነው፡፡

የዚህ ጥናት ግኝትም ተማሪዎች የሚጠቀሙባቸው ተግባቦዊ ብልሀቶች ዓይነቶችና ብዛት አብዘኛውን ጊዜ ተማሪዎቹ በሚያከናውኗቸው ተግባራት ባህሪያት እንዲሚወሰኑ ገልፀዋሉ፡፡ አያይዘውም የተግባሩ ዓይነት (ባህርይ) በብልሀት ምርጫ ላይ ጉልህ ተፅዕኖ እንዳለውም ገልፀዋሉ፡፡

ቀጥሎም ንጋቱ (2000) ቃላትን የመማር ብልሀቶች ምርመራ ለኤም ኤ ዲግሪ ማሟያነት ያቀረቡ ሲሆን ጥናቱ ያተኮረው በደቡብ ክልል በሲዳማ ዞን ውስጥ በሚገኙ ሁለት የመንግስት አጠቃላይ ከፍተኛ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አፋቸውን በሲዳሚኛ የፈቱ የአስራ አንደኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቃላትን ለመማር የሚገለገሉባቸው ቃላት የመማር ብልሀቶችን ለማጥናት የቀረበ ነው፡፡

የዚህ ጥናት ውጤት ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ቃላትን የሚማሩበት ወይም የሚለማመዱበት መንገድ ቃላትን የመማር ብልሀቶችን መሰረት ያላደረገ መሆኑን ገልፀዋሉ፡፡ ይህም ተማሪዎቹ ስለብዙ ብልሀቶች ያላቸው ዕውቀትና ልምድ የዳበረ አለመሆኑን አመልክተዋሉ፡፡

ተክላይ (2000) በትግርኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የስምንተኛና የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ንባብ ጊዜ የንባብ ብልሀት አጠቃቀም እና የመምህራን ግንዛቤ ተጣጥሞሽ ፍተሻ ሲሆን በአክሱም ከተማ አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መነሻነት ለአማርኛ /TEAM/ ኤም ኤ ዲግሪ ማሟያነት የተሰራ ጥናት ነው፡፡

የጥናቱ ውጤት የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች ከአስረኛ ክፍል ተማሪዎች በተወሰነ መልኩም ቢሆን የተሻለ የንባብ ብልሀት አጠቃቀም ያሳዩ መሆናቸውን ገልፀዋሉ፡፡ ይህም የሚያመለክተው በዝቅተኛ የክፍል ደረጃ የሚገኙና በቋንቋ ችሎታቸው በተለየ ደረጃ የሚገኙ ተማሪዎች ከፍ ባለ የክፍል ደረጃ ከሚገኙ ተማሪዎች ይልቅ በንባብ ብልሀት አጠቃቀማቸው የሚያሳዩት ልዩነት ከፍ እንደሚል ጠቁመዋሉ፡፡

ሰሎሞን (1991) የተማሪዎች የአማርኛ ድርሰት የመጻፍ ስትራቴጅና የመምህራን የማስተማር ዘዴ ተጣጥሞ በአዋሳ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት በቋንቋዎች ጥናት ተቋም አማርኛ ማስተማር (TEAM) ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ነው፡፡

የዚህ ጥናት ውጤት በመምህሩ ድርሰት በማስተማር ዘዴውና በተማሪዎች ድርሰት በመጻፍ ስትራቴጅ መካከል ክፍተት መኖሩን ወይም የማይጣጣሙ መሆናቸውን ጠቁመዋሉ፡፡

በተጨማሪም ይርጋ (1997) አፋቸውን በከፊኛ የፈቱ ጥሩ የቋንቋ ተማሪዎች አማርኛ ሲማሩ የሚገለገሉባቸው ቋንቋ የመማር ብልሀቶች እና የመምህራን ግንዛቤ አሰሳ በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት በቋንቋዎች ጥናት ተቋም አማርኛ ማስተማር (TEAM) ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ነው፡፡

በጥናቱ ያገኙት ውጤትም ጥሩ የቋንቋ ተማሪዎች ይገለገሉባቸዋል የተባሉ ስድስቱንም ዋና ዋና ቋንቋ የመማር ብልሀቶች ባመዛኙ በጥቅም ላይ የሚውሉ መሆኑንና የቋንቋ መምህራኑ በተማሪዎቻቸው ቋንቋ የመማር ብልሀት ዙሪያ ግንዛቤ የሌላቸው መሆኑን በመግለፅ፤ በተማሪዎቹ ቋንቋ የመማር ብልሀት እና በመምህራኑ ቋንቋ የማስተማር ሂደት መካከል መጣጣም የሌለ መሆኑን አመልክተዋሉ፡፡

ባጠቃላይ እነዚህ ከላይ የተጠቀሱትን ጨምሮ አጠቃላይ ቋንቋ የመማር ብልሀቶች ቢኖሩም ለትምህርትነት እንደሚሰጠው ንዑስ የቋንቋ ትምህርት ዓይነት ብልሀቶቹ ሊለያዩ ይችላሉ፡፡ ተማሪዎቹም ሁሉንም ብልሀቶች እኩል ላይጠቀሙ ይችላሉ፡፡ ስለዚህ በያንዳንዱ ቋንቋ ዘርፍ መሰራቱ በያንዳንዱ ቋንቋ ትምህርት ዘርፍ ለትምህርትነት በሚሰጥበት ጊዜ የሚዘወተሩትንና የበለጠ ውጤታማ የሆኑትን ብልሀቶች ነጥሎ ለመለየት ያስችላል፡፡ በመሆኑም ሰዋስው ሲማሩ ተማሪዎች የትኞቹን ብልሀቶች የበለጠ እንደሚጠቀሙባቸው የሚያሳይ ጥናት ባለማግኘቴ ጥናቱን ለማካሄድ ችያለሁ፡፡

# ምዕራፍ ሶስት
# የጥናቱ ዘዴ

## 3.1. የጥናቱ ንድፍ

በዚህ ንዑስ ስር የጥናቱ ምንነት፡ የመረጃ ምንጮች፡ የጥናቱ ናሙና አመራረጥ ዘዴ፡ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች አና የመረጃ መተንተኛ ዘዴዎች በቅደም ተከተል ቀርበዋል፡፡

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎችን የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስው የመማር ብልሀቶች መመርመር ነው፡፡ ይህን ዓላማ ማሳካት ይቻል ዘንድ አጥኚው ገላጭ የምርምር ዘዴን መርጧል፡፡ የተመረጠውን ዘዴ በመጠቀም ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስው የመማር ብልሀት አጠቃቀማቸው ምን እንደሚመስል፤ ከተማሪዎች ያገኛቸውን መረጃዎች መሰረት በማድረግ በገለፃ ስልት አቅርቧል፡፡

## 3.2. የመረጃ ምንጭ

የዚህ ጥናት ዓላማ የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስውን የመማር ብልሀት የሚፈትሽ ነው፡፡ ለጥናቱ መረጃ ምንጭ ሆነው የሚያገለግሉት ተማሪዎች ናቸው፡፡ የሚካሄደውም በደቡብ ክልል በወላይታ ዞን በባይራ ኮይሻ ወረዳ በቅሎ ሰኞ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ነው፡፡ ጥናቱ በሚካሄድበት ትምህርት ቤት ከዘጠነኛ እስከ አስራ ሁለተኛ ክፍል ድረስ ያሉ ተማሪዎች የሚገኙ ሲሆን የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በአማርኛ ቋንቋ በመማራቸው አማርኛ በትምህርት ዓይነትነት እየተሰጠ ይገኛል፡፡ ከቀሩት የክፍል ደረጃዎች ዘጠነኛ ክፍል የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት መጀመሪያ ስለሆነ ለሚቀጥለው የትምህርት ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስው የመማር ብልሀት መረጃ ያገኛሉ ብዬ ስላሰብኩ በዓላማ ናሙና ስልት ተመርጠዋል፡፡ በትምህርት ቤቱ ሰባት ዘጠነኛ ክፍሎች የሚገኙ ሲሆን ወንድ 190፣ ሴት 250፣ ባጠቃላይ 440 ተማሪዎች ናቸው፡፡ በያንዳንዱ ክፍል የሚገኙ ተማሪዎች የተለያየ ዳራ ያላቸው ናቸው፡፡ ተማሪዎች አፋቸውን የፈቱበት ቋንቋ አንድ ዓይነት ቢሆንም በዕድሜ፣ በፆታና በትምህርት ችሎታቸው የተለያዩ ናቸው፡፡ ስለዚህ ሁሉንም ዓይነት ተማሪዎች በማሰባጠር እያንዳንዳቸው የየራሳቸው ተወካይ እንዲኖራቸው በማድረግ ከ440 ተማሪዎች 40 ተማሪዎች በዓላማ ንሞና ዘዴ ተመርጠው እንዲካተቱ ተደረጓል፡፡ ከ40 ተማሪዎች ውስጥ ወንድ 17፣ ሴት 23፤ ዕድሜያቸው ከ17 በታች፣ ከ18-20 እና ከ20 ዓመት በላይ ዕድሜ ያላቸውን ተማሪዎች አንድ ላይ በማድረግ፤ በትምህርት ችሎታቸው ደግሞ ጎበዝ፣ መካከለኛና ደካማ ተማሪዎችን እኩል በማከፋፈል እንዲሳተፉ ተደርጓል፡፡

## 3.3. የናሙና አመራረጥ ዘዴ

### 3.3.1. የክልልና የወረዳ የናሙና አመራረጥ

አጥኚው ይህን ጥናት ለማካሄድ በደቡብ ክልል የሚገኘውን የባይራ ኮይሻ ወረዳን በአመቺ የናሙና ዘዴ መርጧል፡፡ ክልሉና ወረዳው የተመረጠበት ምክንያት አጥኚው የመማር ማስተማር ስራውን እያከናወነ የሚያጠናው በመሆኑና በዚሁ ክልል በማስተማር ስራ በመቆየቱ ተጠኚዎችን በቅርብ ማግኘት ስለሚችል ነው፡፡

### 3.3.2. የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ

በወረዳው ውስጥ ከሚገኙ ሁለት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል በቀላል የእጣ ንሞና የናሙና አመራረጥ ዘዴ የበቅሎ ሰኞ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተመርጧል፡፡ በትምህርት ቤቱ ሰባት ዘጠነኛ ክፍሎች የሚገኙ ሲሆን ወንድ 190 ሲሆኑ ሴት 230፤ ባጠቃላይ 440 ተማሪዎች ናቸው፡፡

### 3.3.3 የክፍል ደረጃ ናሙና አመራረጥ

በዚህ ጥናት በ2015 ኢ.ም በተመረጠዉ አንድ ትምህርት ቤት የዘጠነኛ ክፍል የተመረጠበት ምክንያት ይህ የክፍል ደረጃ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት መጀመሪያ እንደመሆኑ መጠን ለቀጣይ ክፍሎች መሰረት ለመጣል የሚያስችል የክፍል ደረጃ በመሆኑ ተማሪዎች እርስ በርስ የመረዳዳት የመተጋገዝ ባህልን እንዲያዳብሩ ከማሰብ አኮያ ተመራጭ ያደርገዋል፤፤

### 3.3.4. የተማሪዎች የናሙና አመራረጥ

ይህ ጥናት የሚያካልለው በደቡብ ክልላዊ መንግስት በወላይታ ዞን ውስጥ በሚገኙት ወረዳዎች አንዱ በሆነዉ በባይራ ኮይሻ ወረዳ በበቅሎ ሰኞ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚማሩ440 ተማሪዎችን ነዉ፡፡እነዚህን ተማሪዎችን ለማስተማር ትምህርት ቤቱ ሰባት የመማሪያ ክፍሎችን የሚጠቀሙ ስሆን ከነዚህ ውስጥ ለናሙናነት የሚመረጡ የመረጃ ምንጮች ከየክፍሉ ማለትም ከአምስት ክፍሎች ስድስት ስድስት ተማርዎች እና ከሁለት ክፍል አምስት አምስት ሆነው በድምሩ አርባ ተማሪዎች ይሆናሉ፡፡አርባ ተማሪዎች የተመረጡበት ምክንያት አጥኚዉ ካለዉ የጊዜና የገንዘብ አቅም አንጻር ከአርባ ተማሪዎች በቂ መረጃ ለመሰብሰብ ለአካላዩ ማጣቃያ መሰጣት ይቻላል ብሎ ስላመነ ነዉ፡፡ያለው(2006፣132) እንዳለው ዓላማ ተኮር የናሙና ዘዴን በተመለከተ “ተመራማሪው የጥናቱን ተሳታፊዎች የሚመርጠው ከአላማ አንፃር ነው፡፡ እነማንን ብመርጥ የሚፈለገው

መረጃ ኖሯቸው ሊሰጡኝ ይችላሉ? የትኞቹን የጥናቱ አካላይ አባላት በጥናቱ ቢሳተፉ አስፈላጊውን መረጃ ላገኝባቸው እችላለሁ? የሚሉ ጥያቄዎችን በማንሳት የጥቱን ዓላማ ለማሳካት ሰዎችን ወይም ሌሎች ነገሮችን ይመርጣል" ብለዋል፡፡ በዚሁ መሰረት ለዚህ ጥናት አጥኚው በትምህርት ቤቱ ከሚያስተምራቸው ሰባት የዘጠነኛ ክፍሎች መካከል በዓላማ ተኮር የናሙና ዘዴ ወንድ 190፣ ሴት 230፤ በድምሩ 440ተማሪዎችን መርጧል፡፡ ከ40 ተማሪዎች ውስጥ ዕድሜያቸው ከ17 በታች፣ ከ18-20 እና ከ20 ዓመት በላይ ዕድሜ ያላቸውን ተማሪዎች አንድ ላይ በማድረግ፤ በቋንቋ ትምህርት ችሎታቸው ደግሞ ከ85 በላይ ውጤት ያስመዘገቡትን በጎበዝ፣ ከ60 እስከ 84 ውጤት ያስመዘገቡትን በመካከለኛና ከ50 በታች ውጤት ያስመዘገቡትን ደግሞ በደካማ ጎራ በመመደብ እኩል በማከፋፈል በስብጥራዊ ናሙና ዘዴ ተመርጠው እንዲሳተፉ አድርጓል፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎቹ የተለያየ ዳራ ያላቸው በመሆኑ ሁሉም የየራሳቸው ተወካይ እንዲኖራቸው ለማድረግ ከዓላማ አንፃር ይህንን የናሙና አመራረጥ ዘዴ ተከትሏል፡፡ የተማሪዎቹን ስብጥር የሚያሳይ ሰንጠረዥ ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

**ሰንጠረዥ 1 በጥናቱ የተሳተፉ ተማሪዎች ስብጥር**

| በቋንቋ ትምህርት ችሎታቸው | ዕድሜያቸው | | | | | | ድምር | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ከ17 ዓመት በታች | | ከ18 - 20 | | ከ20 ዓመት በላይ | | | | |
| | ወ | ሴ | ወ | ሴ | ወ | ሴ | ወ | ሴ | ድ |
| ጎበዝ | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 | 3 | 8 | 9 | 17 |
| መካከለኛ | 2 | 3 | 2 | 2 | 2 | 2 | 6 | 7 | 13 |
| ደካማ | 2 | 2 | 1 | 2 | 1 | 2 | 4 | 6 | 10 |
| ድምር | 7 | 8 | 5 | 7 | 6 | 7 | 18 | 22 | 40 |

በስንጠረዥ አንድ ሴት ተማሪዎች ከ17 ዓመት በታች ዕድሜ ያላቸው በጎብዝና በደካማ ደረጃ ከወንዶች ጋር እኩል ችሎታ መኖር የሚገልጽ ሲሆን በመካከለኛ ዕድሜ ያላቸው ሴት ተማሪዎች ከወንዶች ለቋንቋ ትምህርት ችሎታቸው ተሽለው ተገኝቷል ። በመቀጠል ከ18-20 ዕድሜ ውስጥ የሚገኙ ሴት ተማሪዎች ለቋንቋ ችሎታቸው ከወንዶች ይልቅ በቁጥር ከፍ ብሎ ታይቷል ። ነገር ግን መካከለኛ ዕድሜ ያላቸው ተመሳሳይ ሆኖ አግኝቼያለሁ ። ለደካማ ችሎታ ያሳዩት ከወንዶች ይልቅ ሴቶች በቁጥር በልጠው ተገኝቷል ። በመጨረሻም ከ20 ዓመት በላይ የሆኑ ሴት ተማሪዎች በሁለቱም ማለትም በጎብዝና በመካከለኛ ተመሳሳይ ችሎታ ያላቸው ሲሆን በደካማ ችሎታ የሴቶች በልጠው ተገኝቷል ። በአጠቃላይ የሴቶች ችሎታቸው ከወንዶች አንሶ መገኘቱን ከሰጠረዡ ለመረዳት ችያለሁኝ ።

## 3.4. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ

### 3.4.1 የፅሁፍ መጠይቅ

ለዚህ ጥናት ተግባር ላይ የዋለውን መጠይቅ የሞሉት ተማሪዎች ሲሆን መጠይቁ ለተማሪዎቹ ከመድረሱ በፊት የተለያዩ ፍተሻዎችን በማድረግ የጥያቄዎቹን አስተማማኝነት ደረጃ ለማወቅ ጥረት ተደርጓል። ይህም የተዘጋጁት ጥያቄዎች ከሙያው ወይም ከትምህርቱ ጋር ቅርበት ባላቸው ባለሙያዎች፣ለስራ ባልደረባዎችና በጥናቱ አማካሪ ፍተሻ እንዲደረግባቸውና አስተያየት እንዲሰጥባቸው ተደርጎ በተሰጡት አስተያየቶች መሰረት ማሻሻያ ተደርጎባቸው ቀርበዋል።

የፅሁፍ መጠይቁ ስድስት ክፍሎች ሲኖሩት በመጠይቁ የመጀመሪያ ክፍል የማስታወስ ብልሃቶች የሚል መረጃዎችን የያዘ ሲሆን በክፍል ሁለት ደግሞ የአእምሮታዊ ብልሃቶች በክፍል ሶስት የማካካሻ ብልሃቶች በክፍል አራት ልዕለ አእምሮታዊ ብልሃቶች በክፍል አምስት ደግሞየስሜታዊ ብልሃቶች ሲሆን በክፍል ስድስት የማህበራዊ ብልሃቶች ለሁሉም አምስት አማራጮች ያሉት ሳላሳ ዝግ ጥያቄዎች ቀርበዋል።

የፅሁፍ መጠይቁ የቀረበላቸው ከሰባቱ መማሪያ ክፍሎች በናሙናነት ለተመረጡ አርባ ተማሪዎች ሲሆን ለእነዚህ ተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅ ማቅረቡ ከብዛታቸው አንጻር ከቃለ መጠይቅ በተሻለ የሚሰጡትን መረጃ በቀላሉ ለመተንተን ይረዳል ብሎ አጥኚው ስላመነበት ነው።ከዚህ ጋር በተያያዘ አለም(1994፣44) የፅሁፍ መጠይቅ በአንድ ጊዜ ለብዙ ሰዎች በማሰራጨት ከተለያየ አቅጣጫ መረጃ ለመሰብሰብ ስለሚረዳ ጠቃሚ እንደሆነ ይጠቁማል።

ለዚህ ጥናት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ሆኖ የተመረጠው የፅሁፍ መጠይቅ ነው፡፡ ምክንያቱም መላሾቹ በመጠይቁ ላይ ማንነታቸውን ስለማይገልፁ አስተማማኝ መረጃ እንዲሰጡ ስለሚያበረታታቸውና ለሁሉም ተጠኚዎች አንድ ዓይነት ጥያቄ ስለሚያቀርብላቸው ጠቀሜታው የጎላ ስለሆነ ነው፡፡ በመጠይቁ ባጠቃላይ 30 ዝግ የፅሁፍ ጥያቄዎች ተዘጋጅተዋሉ፡፡ መጠይቁ ሁለት መመሪያዎች ያሉት ሲሆን የመጀመሪያው መመሪያ የተማሪዎች አጠቃላይ መረጃ የሚሞላበት ነው፡፡ ሁለተኛው መመሪያ ደግሞ ጥያቄዎቹ የቀረቡበት ነው፡፡ በሁለተኛው መመሪያ ስር የሚገኘው መጠይቅ ሁለት ክፍሎች አሉት፡፡

የመጀመሪያው ክፍል ተማሪዎች የሚገለገሉበትን ቀጥተኛ የመማር ብልሀቶችን የሚጠይቅ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ኢቀጥተኛ የመማር ብልሀቶችን የሚጠይቅ ነው፡፡ የመጠይቁ ዐቢይ ትኩረት በቀጥተኛ የመማር ብልሀቶች (በማስታወስ፣ በአእምሮታዊ፣ በማካካሻ) እና በኢቀጥተኛ የመማር ብልሀቶች (በልዕለ አእምሮታዊ፣ በስሜታዊና በማህበራዊ ብልሀቶች) ስር ተማሪዎች በሰዋስው ትምህርታቸው ውጤታማ ይሆኑ ዘንድ ሰዋስውን ሲማሩ በሚገለገሉባቸው ዝርዝር ብልሀቶች ላይ ነው፡፡ ከሰላሳ ጥያቄዎች አስራ ሰባት ቀጥተኛ የመማር ብልሀቶችን የሚመለከቱ ሲሆን አስራ ሶስቱ ደግሞ ኢቀጥተኛ የመማር ብልሀቶችን የሚመለቱ ናቸው ፡፡

ቀጥተኛ የመማር ብልሀቶችን ከሚመለከቱ አስራ ሰባት ጥያቄዎች ውስጥ አምስቱ የማስታወስ አስር አእምሮታዊ፣ ሁለቱ የማካካሻ ብልሀቶችን የሚመለከቱ ሲሆን፣ ኢቀጥተኛ የመማር ብልሀቶችን ከሚመለከቱ አስራ ሶስቱ ጥያቄዎች ውስጥ አራቱ ልዕለ አእምሮታዊ፣ አምስቱ ስሜታዊ፣ አራቱ ማህበራዊ ብልሀቶችን የሚመለከቱ ናቸው፡፡ ጥያቄዎቹ ከዓላማ ጋር የሚዛመዱ ሆነው ሰዋስው የመማር ብልሀቶችን መሰረት አድርገው በአጥኚው የተዘጋጁ ናቸው፡፡ የተዘጋጁ ጥያቄዎች በአራት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ከተገመገሙና አስተያየት ከተሰጠ በኋላ በአማካሪ እንዲታዩ ተደርገዋል፡፡ ከዚያም ጥያቄዎቹ በአማርኛ ቋንቋ አስተማሪዎች አማካይነት በአማርኛ ክፍለ ጊዜ ለአርባ ተማሪዎችም የተሰራጨ ሲሆን፤ ጥያቄውን መስራት ከመጀመራቸው በፊት እንዴት መስራት እንዳለባቸው ከአጥኚው ማብራሪያ ቀርቦላቸዋል፡፡ ስድስቱንም የመማር ብልሀቶችን የሚጠይቀው መረጃ በሰንጠረዥ ቁልቁል ወይም ወደታች የሰፈረ ሲሆን፤ አግድም ወይም ወደጎን ደግሞ ተማሪዎች ሰዋስው የመማር ብልሀቶች አጠቃቀምና የድግግሞሽ መጠናቸውን ለመፈተሽ የሚገለገሉበት የLikert-scale ባለአምስት አማራጭ መልሶች 5 = ሁል ጊዜ፣ 4 = አብዛኛውን ጊዜ፣ 3 = አንዳንድ ጊዜ፣ 2 = አልፎ አልፎ 1 = ጭራሽ ድረስ ያሉት

መመዘኛዎች ሰፍረው ይገኛሉ፡፡ ተማሪዎች ከቀረቡ አማራጭ መልሶች መካከል እያንዳንዳቸው በየግላቸው መልስ ይሆናል ያሉትን አንዱን ብቻ መርጠው በያንዳንዱ ጥያቄ ትይዩ ባለው ባዶ ሳጥን ውስጥ የ"x" ምልክት በማድረግ አጠቃላይ ጥያቄዎቹን በአርባ ደቂቃ ውስጥ ሞልተው እንዲመልሱ ተደርጓል፡፡ ሁሉም ተማሪዎች በተሰጣቸው ደቂቃ ሁሉንም ጥያቄ ሰርተው መልሰዋሉ፡፡ ከዚህ በኂላ ሁሉንም ጥያቄዎች ምን ያህል ተማሪ በምን ያህል መጠን እያንዳንዱን ብልሀት እንደሚገለገልበት ተቆጥሮ አጠቃላይ ተማሪዎች ከሚጠቀሙባቸው ብልሀቶች አንፃር የትኛውን አዘውትረው እንደሚገለገሉበት በቁጥርና በመቶኛ ተሰልተው የተማሪዎች የብልሀት አጠቃቀማቸው ተመዝኗል፡፡

## 3.5. የመረጃ አተናተን ዘዴ

በዚህ ጥናት ውስጥ በፅሁፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ከአላማዎቹ አንፃር ማለትም ቀጥተኛ ብልሀቶችን የሚመለከቱ መረጃዎች በመጀመሪያ ላይ፤ ኢቀጥተኛ ብልሀቶችን የሚመለከቱ መረጃዎች ደግሞ ሁለተኛ ርዕስ ይዘው በምዕራፍ አራት ስር ተተንትነዋል፡፡ በሁለቱም ዐብይ ብልሀቶች ስር ስድስቱንም ብልሀቶች የሚመለከቱ ዝርዝር መረጃዎች ተቆጥረው የትኛው ብልሀት በምን ያህል ተማሪዎች እንደሚዘወተር በዓይነት በዓይነታቸው በሰንጠረዥ ተከፋፍለው እያንዳንዱን ጥያቄ የመለሱ ተማሪዎች ድምር ውጤት በቁጥርና እያንዳንዱን ጥያቄ የመለሱ ተማሪዎች ድምር ለአጠቃላይ ተማሪዎች ቁጥር በማካፈልና በመቶ በማባዛት ውጤቱ በመቶኛ ስሌት ቀርቧል፡፡ ከዚህ በኂላ በያንዳንዱ መረጃ ላይ የተማሪዎች የብልሀት አጠቃቀም የድግግሞሽ መጠንና አዘውትረው የሚጠቀሙባቸው ብልሀቶች አንድምታ ገላጭ ዘዴን በመጠቀም ትንተና ተደርጓል፡፡

# ምዕራፍ አራት

# የመረጃ ትንተናና ማብራሪያ

በዚህ የመረጃ ትንተና ክፍል በቅሎ ሰኞ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ሰዋስው የመማር ብልሀቶችን በሚመለከት በፅሁፍ መጠይቅ አማካይነት የተገኙ መረጃዎች ከዓላማዎቹ አንፃር ቀጥተኛ ብልሀቶችን የሚመለከቱ መረጃዎች መጀመሪያ ላይ፤ ቀጥሎ ደግሞ ኢቀጥተኛ ብልሀቶችን የሚመለከቱ መረጃዎች ቀርበዋል፡፡ በሁለቱ ዐብይ ብልሀቶች ስር ሶስት ሶስት ንዑሳን ብልሀቶች የሚገኙ ሲሆን፣ በያንዳንዳቸው ንዑሳን ብልሀቶች ስር በሚገኙ ዝርዝር ብልሀቶች መረጃ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስው የመማር ብልሀቶችን በምን ያህል መጠን እንደሚገለገሉ የሚያሳይ ትንተና ቀጥሎ በቅደም ተከተል ቀርበዋል፡፡

## 4.1. ቀጥተኛ የመማር ብልሀቶች መረጃ ትንተና ማብራሪያ

ሰዋስው ለመማር ተገቢ የሆኑ ቀጥተኛ የመማር ብልሀቶችም የማስታወስ፣ አእምሮታዊና ማካካሻ ብልሀቶች በሚባሉ ሶስት ንዑሳን ምድቦች የሚከፈሉ ሲሆን፤ ሶስቱም ብልሀቶች እያንዳንዳቸው በስራቸው ሌሎች ዝርዝር ብልሀቶችን ያካተቱ ናቸው፡፡ በመሆኑም በፅሁፍ መጠይቅ የተሰበሰበው መረጃ እንደሚያመለክተው የተማሪዎች ቀጥተኛ የመማር ብልሀት አጠቃቀማቸው ዝቅተኛ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በሶስቱ ንዑሳን ምድቦች ውስጥ የሚገኙ ዝርዝር ብልሀቶችን አዘውትረው እንደሚጠቀሙ መልስ እንዲሰጡ 17 ጥያቄዎች ለተማሪዎች በፅሁፍ መጠይቅ ቀርቦላቸዋል፡፡ በእያንዳንዱ አማራጭ ስር አምስት ቀጥተኛ የመማር ብልሀቶችን ጥያቄ የመለሱ ተማሪዎች ድምር በቁጥርና ምላሽ የሰጡ ተማሪዎች ድምር ለአጠቃላይ ተማሪዎች ድምር ተካፍሎ በመቶ በማባዛት በመቶኛ ተተንትኗል፡፡ በዚሁ መሰረት 81(8.1%) የሚያህሉ ተማሪዎች እነዚህን ብልሀቶች በጭራሽ እንደማይጠቀሙ ነው መልስ የሰጡት፡፡ ይሄ የተማሪዎች የቀጥተኛ ብልሀት አጠቃቀማቸው ዝቅተኛ መሆኑን ያሳያል፡፡ አንዳንድ ጊዜ እንጠቀማለን ያሉት ተማሪዎች ብዛት 246(24.6%) ሲሆን፣ 168(16.8%) የሚያህሉ ተማሪዎች አልፎ አልፎ እንደሚጠቀሙ ገልፀዋሉ፡፡ ይሄም ዝቅተኛነቱን የሚያመለክት ነው፡፡ 286(28.6%)የሚያህሉ ተማሪዎች ሁል ጊዜ እንደሚጠቀሙ ሲገልፁ 219(21.9%) የሚያህሉ ተማሪዎች ደግሞ አብዛኛውን ጊዜ የሚጠቀሙ ናቸው፡፡ ይሄም ደግሞ ሌላው ዝቅተኛ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

አጠቃላይ ቀጥተኛ ብልሀቶች አጠቃቀም በተመለከተ የመረጃ ትንተናና ማብራሪያ ቀጥሎ ባሉት ሰንጠረዦች ቀርቧል፡፡

## ሰንጠረዥ 2. የማስታወስ ብልሀቶች መረጃ

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | አማራጮች | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሁል ጊዜ | | አብዛኛውን ጊዜ | | አንዳንድ ጊዜ | | አልፎ አልፎ | | በጭራሽ | |
| | | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥ | በ% |
| 1 | ማቧደን<br>1.1 በምዕላድ ዓይነት | 9 | 22.5 | 10 | 25 | 16 | 40 | 5 | 12.5 | 0 | 0 |
| | 1.2 በቃል ክፍላቸው | 14 | 35 | 8 | 20 | 10 | 25 | 8 | 20 | 0 | 0 |
| | 1.3 በሀረግ ክፍላቸው | 7 | 17.5 | 11 | 27.5 | 12 | 30 | 10 | 25 | 0 | 0 |
| | 1.4 በዐረፍተ ነገር ዓይነት | 8 | 20 | 10 | 25 | 10 | 25 | 9 | 22.5 | 3 | 7.5 |
| 2 | ማያያዝ<br>2.1 ከመፅሀፉ ገፅ አንፃር | 10 | 25 | 9 | 22.5 | 6 | 15 | 10 | 25 | 2 | 12.5 |
| | 2.2 ከመምህሩ አንፃር | 13 | 32.5 | 9 | 22.5 | 10 | 25 | 6 | 15 | 2 | 5 |
| 3 | ምስል መፍጠር<br>3.1 ከተጨባጭ ጋር | 15 | 37.5 | 7 | 17.5 | 9 | 22 .5 | 6 | 15 | 3 | 7.5 |
| | 3.2 ከድምፆች ጋር | 10 | 25 | 15 | 37.5 | 6 | 15 | 4 | 10 | 5 | 12.5 |
| 4 | እንደገና መከለስ | 6 | 15 | 16 | 40 | 8 | 20 | 7 | 17.5 | 3 | 7.5 |
| 5 | እንቅስቃሴን መጠቀም | 12 | 30 | 6 | 15 | 12 | 30 | 6 | 15 | 4 | 10 |

ከላይ በሰንጠረዥ 2 በጥያቄ 1 ስር ከጥያቄ 1.1-1.4 ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስው ትምህርት በቀላሉ ለማስታወስ ተመሳሳይ ነገሮችን በአንድ ወገን ማለትም በምዕላድ ዓይነታቸው፣ በቃል ክፍላቸው፣ በሀረግ ክፍላቸውና በዐረፍተ ነገር ዓይነታቸው በመመደብ ይማሩ እንደሆን ለመመርመር የቀረበ ነበር። በመሆኑም ተማሪዎች ይህን ብልሀት የመጠቀማቸው ሁኔታ ዝቅተኛ ነው። በጥያቄ 1 አራቱን ዝርዝር ብልሀቶችን የመለሱ ተማሪዎች ድምር በቁጥርና ምላሽ የሰጡ ተማሪዎች ድምር ለአጠቃላይ ተማሪዎች ድምር ተካፍሎ በመቶ በማባዛት በመቶኛ ተተንትኗል።

### 4.1.1. የማስታወስ ብልሀቶች መረጃ ትንተናና ማብራሪያ

የተማሪዎች የማስታወስ ብልሀት አጠቃቀማቸው ባጠቃላይ ዝቅተኛ ሆኖ ተገኝቷል። በእያንዳንዱ አማራጭ ስር አስሩን የማስታወስ ብልሀቶች ጥያቄ የመለሱ ተማሪዎች ድምር በቁጥርና ምላሽ የሰጡ ተማሪዎች ድምር ለአጠቃላይ ተማሪዎች ድምር ተካፍሎ በመቶ በማባዛት በመቶኛ ተተንትኗል። በዚሁ መሰረት 104(26%) የሚያህሉ ተማሪዎች ሁል ጊዜ የሚጠቀሙ ሲሆን በአንፃሩ ደግሞ 71(17.75%) የሚያህሉ ተማሪዎች ደግሞ አልፎ አልፎ እንደሚጠቀሙ ገልፀዋሉ። 25(6.25%) የሚያህሉት ተማሪዎች በጭራሽ የማይጠቀሙ ናቸው። ይሄ ዝቅተኛነቱን ያሳያል። ሌላው ደግሞ ይህንን ብልሀት አብዛኛውን ጊዜ እንጠቀማለን ያሉት ተማሪዎች ብዛት 101(25.25%) ያህል ነው። እንዲሁም 99(24.75%) የሚያህሉ ተማሪዎች ደግሞ አንዳንድ ጊዜ የሚጠቀሙ ናቸው። ይሄም ደግሞ ሌላው ዝቅተኛ መሆኑን የሚያሳይ ነው።

ከማስታወስ ብልሀቶች ውስጥ ተማሪዎች የሰዋስው ትምህርትን ከዚህ በፊት ከሚያውቁት ነገር ጋር ማያያዝን፣ በቃል ክፍላቸው መቦደንን፣ ከተጨባጭ ነገሮች ጋር አገናኝቶ ምስል መፍጠርና እንቅስቃሴ መጠቀምን አዘውትረው የሚጠቀሙባቸው ብልሀቶች ናቸው። ተማሪዎች እነዚህን ብልሀቶች አዘውትረው መጠቀማቸው ሰዋስው ትምህርትን ቶሎ እንዲያስታውሱና በአእምሯቸው በቀላሉ እንዲቀርፁ እንዲሁም እንዳይረሱ ያግዟቸዋል። በአንፃሩ እነዚህን ብልሀቶች አዘውትረው መጠቀማቸው በሸምደዳ ላይ ብቻ እንዲያተኩሩ ያደርጓቸዋል። ተማሪዎች የዚህን ዝርዝር ብልሀቶችን በምን ያህል መጠን እንደሚደጋግሙ የሚመለከቱ ጥያቄዎች ቀጥሎ ባለው ሰንጠረዥ ከተራ ቁጥር 1-5 ቀርበው ተተንትነዋል።

በዚሁ መሰረት 48(30%) የሚያህሉ ተማሪዎች አንዳንድ ጊዜ የሚጠቀሙ ሲሆን 39(24.4%) የሚያህሉ ተማሪዎች ደግሞ አብዛኛዉ ጊዜ እንደሚጠቀሙ ገልፀዋሉ። ይህ

ከግማሽ በላይ ተማሪዎች ይህን ብልሀት አንዳንዴና አብዛኛዉ ጊዜ መጠቀማቸው ዝቅተኛነቱን ያሳያል፡፡

ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስው ትምህርት በቀላሉ ለማስታወስ በምዕላድ ዓይነቶች በማቧደን ይማሩ እንደሆን ተጠይቀው 16(40%) የምዕላድ ዓይነቶችን አንዳንድ ጊዜ በየወገኑ በመመደብ እንደሚማሩ ሲገልፁ 10(25%) ተማሪዎች ደግሞ ይህን ብልሀት አብዛኛውን ጊዜ እንደሚገለገሉ ገልፀዋሉ፡፡ እንዲሁም 5(12%) የሚሆኑ ተማሪዎች የሰዋስው ትምህርት በቀላሉ ለማስታወስ በምዕላድ ዓይነቶች መቦደንን አልፎ አልፎ እንደሚገለገሉ ሲገልፁ 9(22.5%) ተማሪዎች ደግሞ ብልሀቱን ሁል ጊዜ እንደሚገለገሉ ገልፀዋሉ፡፡ ይህን ብልሀት በጭራሽ የማይጠቀሙ ተማሪዎች እንደለሉ ከመረጃው ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ተጠኚዎች አዲሱን ሰዋስው ትምህርት በቀላሉ ለማስታወስ በቃል ክፍላቸው የመመደብ ብልሀት አጠቃቀማቸውን በተመለከተ 14(35%) የሚሆኑ ተጠኚዎች ሁል ጊዜ የሚጠቀሙ ሲሆን 10(25%) ተጠኚዎች ይህን ብልሀት አንዳንድ ጊዜ እንደሚጠቀሙ የሰጡት ምላሽ ያመለክታል፡፡ 8(20%) የሚያህሉ ተጠኚዎች ደግሞ ይህን ብልሀት አልፎ አልፎ እንደሚጠቀሙ ሲገልፁ 8(20%) ተጠኚዎች አብዛኛውን ጊዜ እንደሚጠቀሙ ገልፀዋሉ፡፡ ሌላው ደግሞ ይህን ብልሀት በጭራሽ የማይጠቀሙ ተጠኚዎች የሉም፡፡ ይህ ብልሀት ተማሪዎች በመቦደን ከሚያስታውሱት ብልሀቶች ውስጥ አዘውትረው የሚጠቀሙብት ብልሀት ነው፡፡ ይህን ብልሀት አዘውትረው መጠቀማቸው የሰዋስው ትምህርትን ቶሎ እንዲያስታውሱ ያስችሏቸዋል፡፡

ተማሪዎች የሰዋስው ትምህርት በቀላሉ ለማስታወስ ይረዳቸው ዘንድ በሀረግ ክፍላቸው የመመደብ ብልሀት አስመልክተው በሰጡት ምላሽ 12(30%) የሚደርሱ ተማሪዎች አንዳንድ ጊዜ የሚጠቀሙ ሲሆን 11(27.5%) ተማሪዎች አብዛኛውን ጊዜ የሚጠቀሙ መሆናቸውን ለመረዳት ተችሏል፡

10(25%) የሚሆኑ ተማሪዎች ደግሞ ብልሀቱን አልፎ አልፎ የሚጠቀሙ ሲሆን 7(17.5%) ተማሪዎች ሁል ጊዜ የሚጠቀሙ ናቸው፡፡ ይህን ብልሀት በጭራሽ የማይጠቀሙ ተማሪዎች የሌሉ መሆናቸውን መረጃው ያመለክታል፡፡

ተተኳሪዎች አዲሱን የሰዋስው ትምህርት በቀላሉ ለማስታወስ በዐረፍተ ነገር ዓይነታቸው ይቦድኑ እንደሆን ተጠይቀው 10(25%) የሚሆኑ ተተኳሪዎች ባብዛኛው የሚጠቀሙ መሆናቸውን ሲገልፁ 8(20%) ተተኳሪዎች ሁል ጊዜ የሚጠቀሙ መሆናቸውን ገልፀዋሉ፡፡

በቁጥር 10( 25%) የሚያህሉ ተተኳሪዎች ደግሞ ብልሀቱን አንዳንድ ጊዜ የሚጠቀሙ ሲሆን 9(22.5%) አልፎ አልፎ የሚጠቀሙ መሆናቸውን መረጃው ያመለክታል፡፡ 3(7.5%) ተተኳሪ ብልሀቱን በጭራሽ የማይጠቀም ነው፡፡

ባጠቃላይ ከጥያቄ 1.1-1.4 አዲሱን የሰዋስው ትምህርት በቀላሉ ለመማርና ለማስታወስ እንዲረዳቸው በቡድን በቡድን የመከፋፈል ብልሀት አጠቃቀማቸውን በተመለከተ 38(23.75%) ተማሪዎች ሁል ጊዜ፣ 39(24.5%) አብዘኛውን ጊዜ፣ 48(30%) አንዳንድ ጊዜ፣ 32(20%) አልፎ አልፎ ሲቦድኑ 3(1.87%) ተማሪ መቦደንን የማይጠቀም ነው፡፡

ተማሪዎች የሰዋስው ትምህርት በቀላሉ ለማስታወስ በቃል ክፍላቸውና በዐረፍተ ነገር ዓይነታቸው የማቧደን ብልሀት ትኩረት በመስጠት በስፋት የሚጠቀሙ ሲሆን በምዕላድና በሀረግ ክፍላቸው የማቧደን ብልሀት ብዙም ትኩረት ሰጥተው የማይጠቀሙ መሆናቸውን የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡ ባጠቃላይ የሰዋስው ትምህርት ለረዥም ጊዜ ለማስታወስ በየምድባቸው የማቧደን ብልሀት አጠቃቀማቸው ዝቅተኛ እንደሆነ ከጥናቱ ውጤት ለመረዳት ተችሏል፡፡

ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስው ትምህርት በአእምሯቸው ውስጥ መዝግበው ለረዥም ጊዜ ማስታወስ እንዲችሉ ከዚህ በፊት ከሚያውቁት ነገር ጋር ማያያዛቸውን በተመለከተ በ2.1 የሰዋስው ትምህርት በመፅሀፉ ውስጥ ከሚገኝበት ገፅ አንፃር በማያያዝ በቁጥር 10(25%) የሚሆኑ ተጠኚዎች ሁል ጊዜ የሚጠቀሙ መሆናቸውን ሲገልፁ 10(25%) ተጠኚዎች አልፎ አልፎ የሚጠቀሙ መሆናቸውን ገልፀዋሉ፡፡

በአንፃሩም 9(22.5%) የሚያህሉ ተጠኚዎች ይህን ብልሀት ባብዘኛው የሚገለገሉ ሲሆን 6(15%) የሚሆኑት ደግሞ አንዳንዴ የሚገለገሉ መሆናቸውን ገልፀዋሉ፡፡ በቁጥር 5(12.5%) የሚሆኑት ይህን ብልሀት በጭራሽ የማይጠቀሙ ናቸው፡፡

የሰዋስው ትምህርት በቀላሉ ለማስታወስ መምህሩ ክፍል ውስጥ ከነበረበት ሁኔታ አንፃር በማያያዝ በቁጥር 13(32.5%) የሚሆኑ ተጠኚዎች ሁል ጊዜ የሚጠቀሙ መሆናቸውን ሲገልፁ ሁል ጊዜ ከሚጠቀሙት ጋር እኩል መጠን ያላቸው ተጠኚዎች አንዳንድ ጊዜ የሚጠቀሙ መሆናቸውን ገልፀዋሉ፡፡ 6(15%) የሚሆኑ ተጠኚዎች ደግሞ ይህን ብልሀት አልፎ አልፎ የሚጠቀሙ ናቸው፡፡ 9(22.5%) የሚሆኑ ተጠኚዎች ደግሞ ይህን ብልሀት አብዘኛውን ጊዜ የሚጠቀሙ ሲሆን 2(5%) ተጠኚዎች በጭራሽ የማይጠቀሙ መሆናቸውን መረጃው ያመለክታል፡፡

የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስው ትምህርት በአእምሯቸው ውስጥ መዝግበው ለረዥም ጊዜ ለማስታወስ በመፅሀፉ ውስጥ ከሚገኝበት ገፅ አንፃር ይልቅ መምህሩ ክፍል ውስጥ ከነበረበት ሁኔታ አንፃር ማያያዛቸውን የበለጠ እንደሚጠቀሙ መረጃው ያመለክታል፡፡ ተማሪዎች ይህን ብልሀት ከዚህ በፊት በአእምሯቸው ውስጥ ለረዥም ጊዜ ካከማቹት ዕውቀት ጋር አያይዘው እንዲያስታውሱ ያስችሏቸዋል፡፡ ሆኖም ይህን ብልሀት አዘውትረው መጠቀማቸው በሽምደዳ ላይ እንዲያተኩሩ ያደርጋቸዋል፡፡

የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስው ትምህርት በአእምሯቸው ውስጥ ምስል በመፍጠር ለማስታወስ መሞከርን በተመለከተ በጥያቄ 3.1 ከተጨባጭ ነገሮች ጋር አገናኝተው ምስል የመፍጠር ብልሀት ይጠቀሙ እንደሆን ተጠይቀው 15(37.5%) የሚሆኑ ተጠኚዎች ሁል ጊዜ እንደሚጠቀሙ ሲገልፁ 6(15%) ተጠኚዎች አልፎ አልፎ የሚጠቀሙ መሆናቸውን ገልፀዋሉ፡፡ 9(22.5%) የሚሆኑት ተጠኚዎች ደግሞ ይህን ብልሀት አንዳንዴ የሚጠቀሙ ሲሆን 7(17.5%) የሚያህሉ ደግሞ ባብዛኛው የሚጠቀሙ ናቸው፡፡ ይህን ብልሀት በጭራሽ የማይጠቀሙት 3(7.5%) እንደሚደርሱም ከመረጃው ተረጋግጧል፡፡ ይህ ብልሀት ተማሪዎች አዘውትረው የሚጠቀሙት ብልሀት ሲሆን የሰዋስው ትምህርት ስዕላዊ መግለጫ በአእምሯቸው ውስጥ እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡

ከድምፆች ጋር አገናኝተው ምስል የመፍጠር ብልሀት ይጠቀሙ እንደሆን ለተጠየቁትም 6(15%) የሚሆኑ ተጠኚዎች አንዳንድ ጊዜ እንደሚጠቀሙ ምላሽ ሲሰጡ 15(37.5%) የሚሆኑ ተጠኚዎች አብዛኛውን ጊዜ እንደሚጠቀሙ ምላሽ ሰጥተዋሉ፡፡ 10(25%) የሚሆኑ ተጠኚዎች ደግሞ ይህን ብልሀት ሁል ጊዜ የሚጠቀሙ ሲሆን 4(10%) ተጠኚዎች አልፎ አልፎ የሚጠቀሙ መሆናቸውን መረጃው ያመለክታል፡፡ 5(12.5%) የሚደርሱ ተጠኚዎች ደግሞ ይህን ብልሀት በጭራሽ የማይጠቀሙ ናቸው፡፡

ባጠቃላይ የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስው ትምህርት በቀላሉ ለመማር በአእምሯቸው ውስጥ ከድምፆች ጋር አገናኝተው ምስል ከመፍጠር ብልሀት ይልቅ ከተጨባጭ ነገሮች ጋር አገናኝተው ምስል የመፍጠር ብልሀት በስፋት እንደሚጠቀሙ መረጃው ይጠቁማል፡፡

ተማሪዎች የተማሩትን የሰዋስው ትምህርት በተለያዩ ጊዜያት የሚከልሱ መሆናቸውን ተጠይቀው 16(40%) ተማሪዎች አብዛኛውን ጊዜ የሚከልሱ መሆናቸውን ሲገልፁ 8(20%) ተማሪዎች ደግሞ አንዳንድ ጊዜ የሚከልሱ መሆናቸውየሚሆኑን ገልፀዋሉ፡፡ 6(15%) ተማሪዎች ይህን ብልሀት ሁል ጊዜ የሚጠቀሙ ሲሆን 7 (17.5%) አልፎ አልፎ

የሚጠቀሙ መሆናቸውን ከምላሻቸው ለመረዳት ተችሏል፡፡ 3(7.5%) ተማሪዎች ይህን ብልሀት በጭራሽ የማይጠቀሙ ናቸው፡

የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስው ትምህርት በቀላሉ ለማስታወስ የተለያዩ አካላዊ እንቅስቃሴዎችን በመጠቀም ይማሩ እንደሆን ተጠይቀው 12(30%) ተጠኚዎች ሁል ጊዜ የሚጠቀሙ ሲሆን፣ ሁል ጊዜ ከሚጠቀሙት ጋር እኩል መጠን ያላቸው ተጠኚዎች ደግሞ አንዳንድ ጊዜ የሚጠቀሙ መሆናቸውን ከምላሻቸው ለመረዳት ተችሏል፡፡ ይህን ብልሀት 6(15%) የሚሆኑ ተጠኚዎች አልፎ አልፎ እንጠቀማለን ብለው ሲመልሱ በአንፃሩ 6(15%) ተጠኚዎች ይህን ብልሀት አብዘኛውን ጊዜ እንደሚጠቀሙ መልሰዋሉ፡፡ 4(10%) ተጠኚዎች ደግሞ ይህን ብልሀት በጭራሽ የማይጠቀሙ መሆናቸውን መረጃው ያመለክታል፡፡

ተማሪዎች ከላይ ከቀረቡት ከማስታወስ ብልሀቶች ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ከዚህ በፊት ከሚያውቀት ነገር ጋር ማያያዛቸውን፣ በአእምሯቸው ውስጥ ምስል በመፍጠር ማስታወስን፣ የተለያዩ አካላዊ እንቅስቃሴዎችን የመጠቀም ብልሀቶችን የሚያዘውትሩ ናቸው፡፡ ተማሪዎች እነዚህን ብልሀቶች አዘውትረው መጠቀማቸው ሰዋስው ትምህርትን ቶሎ እንዲያስታውሱና የጠለቀ እውቀት እንዲኖራቸው ያግዟቸዋል፡፡ በአእምሯቸው በቀላሉ እንዲቀርፁና በአጭሩ እንዲረዱ እንዲሁም እንዳይረሱ ይረዷቸዋል፡፡ በሌላ ጎኑ ደግሞ ሁል ጊዜ እነዚህን ብልሀቶች መጠቀማቸው በተወሰኑ ሰዋስው ትምህርቶች ላይ ብቻ እንዲያተኩሩ በማያውቁት ሰዋስው ትምህርት ላይ ሰፊ እውቀት እንዳይኖራቸውና እንዳይጨምሩ ያደርጓቸዋል፡፡ በሽምደዳ ላይ ብቻ እንዲያተኩሩም ያደርጓቸዋል፡፡

ባጠቃላይ ከላይ በሰንጠረዥ 1 ከተራ ቁጥር 1-5 ከቀረቡት መጠይቆች የተገኘው መረጃ ውጤት የሚያመለክተው በ4.1.1 ስር እንደተገለፀው አብዘኞቹ ማለትም 104(26%) የሚያህሉት ተማሪዎች የማስታወስ ብልሀቶችን ሁል ጊዜ የሚጠቀሙ መሆናቸውን ነው፡፡ ይህም ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስው ትምህርት ለረዥም ጊዜ በማስታወስ በቀላሉ ለመማር የመጠቀማቸው ሁኔታ ዝቅተኛ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ የዚህ መረጃ ውጤት በተዛማጅ ፅሁፍ ቅኝት ከተገለፀው ሀሳብ ጋር የሚጣጣም ነው፡፡ የታላሚው ቋንቋ ተማሪዎች ችግሮች አንዱ በአንድ ወቅት ከዚህ በፊት የተማሯቸውን የሰዋስው ትምህርትን በሌላ ጊዜ አስታወሰው መጠቀም አለመቻል ነው፡፡

## ሰንጠረዥ 3. የአእምሮታዊ ብልሀቶች መረጃ

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | አማራጮች | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሁል ጊዜ | | አብዘኛውን ጊዜ | | አንዳንድ ጊዜ | | አልፎ አልፎ | | በጭራሽ | |
| | | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% |
| 6 | ደጋግሞ መፃፍ | 15 | 37.5 | 7 | 17.5 | 11 | 27.5 | 5 | 12.5 | 2 | 5 |
| 7 | ደጋግሞ በአእምሮ ውስጥ ማመላለስ | 14 | 35 | 6 | 15 | 10 | 25 | 7 | 17.5 | 3 | 7.5 |
| 8 | መፃህፍትንመጠቀም | 11 | 27.5 | 9 | 22.5 | 13 | 32.5 | 5 | 12.5 | 2 | 5 |
| 9 | ሚዲያን መከታተል | 10 | 25 | 6 | 15 | 14 | 35 | 6 | 15 | 4 | 10 |
| 10 | ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር መተንተን | 12 | 30. | 9 | 22.5 | 9 | 22.5 | 8 | 20 | 2 | 5 |
| 11 | ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ መተንተን | 8 | 20 | 7 | 17.5 | 10 | 25 | 10 | 25 | 5 | 12.5 |
| 12 | ማስታውሻ መያዝ | 15 | 37.5 | 6 | 15 | 9 | 22.5 | 4 | 10 | 6 | 15 |
| 13 | ማነፃፀር | 16 | 40 | 9 | 22.5 | 10 | 25 | 4 | 10 | 1 | 2.5 |
| 14 | መተርጐም | 14 | 35 | 8 | 20 | 10 | 25 | 5 | 12.5 | 3 | 7.5 |
| 15 | ማድመቅ 15.1 በተለያየ ብዕር | 15 | 37.5 | 11 | 27.5 | 6 | 15 | 6 | 15 | 2 | 5 |
| | 15.2 ከስሩበማስመር | 18 | 45 | 9 | 22.5 | 6 | 15 | 4 | 10 | 3 | 7.5 |
| | 15.3 በማክበብ | 9 | 22.5 | 10 | 25 | 7 | 17.5 | 6 | 15 | 8 | 20 |

ከላይ በሰንጠረዥ 3 በጥያቄ 6 አዲሱን የሰዋስው ትምህርት ለመገንዘብ ህጎችን ደጋግመው በመፃፍ ይለማመዱ እንደሆን ተጠይቀው 15(37.5%) የሚሆኑ ተጠኚዎች ህጎችን ደጋግመው በመፃፍ ሁል ጊዜ እንደሚለማመዱ ሲገልፁ 11(27.5%) ተጠኚዎች አንዳንድ ጊዜ የሚለማመዱ መሆናቸውን ገልፀዋሉ፡፡

### 4.1.2 አእምሮታዊ ብልሀቶች መረጃ ትንተናና ማብራሪያ

አእምሮታዊ ብልሀቶች ተማሪው በሰዋስው ትምህርት ተግባራት ላይ በቀጥታ በሚሳተፍበት ጊዜ የሚገለገልባቸው ብልሀቶች ሆነው የመገንዘብ ሁኔታን ለማዳበር የሚደረጉ ብልሀቶች ናቸው፡፡ የተማሪዎች የአእምሮታዊ ብልሀቶች አጠቃቀም ከፍተኛ ነው ፡፡ ተማሪዎች የዚህን ዝርዝር ብልሀቶች አዘውትረው እንደሚጠቀሙ መልስ እንዲሰጡ ፅሁፍ መጠይቅ ቀርቦላቸው ነበር፡፡ በእያንዳንዱ አማራጭ ስር አስራ ሁለቱን አእምሮታዊ ብልሀቶች ጥያቄ የመለሱ ተማሪዎች ድምር በቁጥርና ምላሽ የሰጡ ተማሪዎች ድምር ለአጠቃላይ ተማሪዎች ድምር ተካፍሎ በመቶ በማባዛት በመቶኛ ተተንትኗል፡፡

በዚሁ መሰረት 157(32.7%) የሚያህሉ ተማሪዎች ሁል ጊዜ የሚጠቀሙ ቢሆንም 70(14.58%) የሚያህሉ ተማሪዎች አልፎ አልፎ የሚጠቀሙና 41(8.54%) የሚሆኑ ተማሪዎች ደግሞ በጭራሽ የማይጠቀሙ ናቸው፡፡ ይህ ከፍተኛ ነው ለማለት የማያስደፍር መሆኑን ያሳያል፡፡ ሌላው ደግሞ እነዚህን ብልሀቶች 97(20.20%) የሚያህሉ ተማሪዎች ባብዛኛው የሚጠቀሙ ሲሆን 115(23.96%) የሚያህሉ ተማሪዎች ደግሞ አንዳንድ ጊዜ እንደሚጠቀሙ ነው መልስ የሰጡት፡፡ ይሄም ከፍተኛ ነው ለማለት የማያስደፍር መሆኑን ያመለክታል፡፡ ከዚህ ብልሀት ውስጥ ተማሪዎች ህጎችን ደጋግሞ በአእምሮ ውስጥ ማመላለስና መናገርን፣ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር መማርን፣ ጠቃሚ ሀሳቦችን አጠር አድርጎ ማስታውሻ መያዝን፣ ከአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ጋር ማነፃፀርን፣ ወደ አፍ መፍቻ ቋንቋ መተርጐምንና በፅሁፍ ውስጥ ጠቃሚ የሆኑ ሰዋስዋዊ መረጃዎችን የተለያዩ ምልክቶችን በማድረግ መጠቀምን አዘውትረው የሚጠቀሙባቸው ብልሀቶች ናቸው፡፡ ተማሪዎች እነዚህን ብልሀቶች አዘውትረው መጠቀማቸው በሰዋስው ትምህርት የጠለቀ እውቀት እንዲኖራቸው ያግዟቸዋል፡፡ በአእምሯቸው በቀላሉ እንዲቀርፁና በአጭሩ እንዲረዱ እንዲሁም እንዳይረሱ ይረዷቸዋል፡፡ በተጨማሪም ዋና ዋና ነጥቦችን ቶሎ እንዲለዩና የረሱትን መልሰው እንዲያገናዝቡ ያስችሏቸዋል፡፡ ቀጥሎ በሰንጠረዥ ከተራ ቁጥር 6-17 የቀረቡ መረጃዎችም ተማሪዎች እነዚህን ዝርዝር ብልሀቶች ምን ያህል ጊዜ በተደጋጋሚ እንደሚገለገሉ የሚመለከቱ ናቸው፡፡ ትንተናም ተካሂዶባቸዋል፡፡

በአንፃሩም 5(12.5%) የሚሆኑ ተጠኚዎች ይህን ብልሀት አልፎ አልፎ የሚጠቀሙ ሲሆን 7(17.5%) ተጠኚዎች ባብዛኛው የሚጠቀሙ ናቸው፡፡ 2(5%) ተጠኚዎች ደግሞ ይህን ብልሀት በጭራሽ የማይጠቀሙ መሆናቸው ከምላሻቸው ተረጋግጧል፡፡ ይህ ብልሀት ተማሪዎች አዘውትረው የሚጠቀሙት ሲሆን የሰዋስው ትምህርት ህጎችን እንዲያገናዝቡና ጥልቅ እውቀት እንዲኖራቸው ያደርጓቸዋል፡፡ ሆኖም ተማሪዎች ይህን ብልሀት

ማዘውተራቸው ለሰዋስው ትምህርት ህግ ብቻ ተገዢ እንዲሆኑና በራሳቸው ፈጠራ እንዳይጠቀሙ ያደርጋቸዋል፡፡

የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስው ትምህርት ለመገንዘብ ህጎችን በአእምሯቸው ውስጥ በማመላለስ ይጠቀሙ እንደሆን ለተጠየቁት 6(15%) ተጠኚዎች ባብዛኛው እንደሚጠቀሙ ሲመልሱ 7(17.5%) ተጠኚዎች አልፎ አልፎ እንደሚጠቀሙ ምላሻቸው ያመለክታል፡፡ 14(35%) ተጠኚዎች ደግሞ ይህን ብልሀት ሁል ጊዜ ሲጠቀሙ 10(25%) ተጠኚዎች አንዳንዴ የሚጠቀሙ ናቸው፡፡ 3(7.5%) ተጠኚዎች ይህን ብልሀት በጭራሽ እንደማይጠቀሙ ምላሻቸውን ሰጥተዋሉ፡፡

ተማሪዎች የተማሯቸውን የሰዋስው ትምህርት ሲያጠኑ ማጣቀሻ መፃህፍትን(ሰዋስው መፅሀፍ፣ መዝገበ ቃላት ወዘተ.) መጠቀም አለመጠቀማቸውን ለመመርመር ለቀረበው ጥያቄ 13(32.5%) የሚሆኑ ተማሪዎች አንዳንድ ጊዜ መጠቀማቸውን ሲገልፁ 11(27.5%) የሚያህሉት ሁል ጊዜ እንደሚጠቀሙ ገልፀዋሉ፡፡ 9(22.5%) ተማሪዎች ደግሞ ይህን ብልሀት ባብዛኛው የሚጠቀሙ ሲሆን 5(12.5%) የሚሆኑት አልፎ አልፎ የሚጠቀሙ ናቸው፡፡ ይህን ብልሀት 2(5%) የሚሆኑ ተማሪዎች በጭራሽ እንደማይጠቀሙ ምላሻቸውን ሰጥተዋሉ፡፡

ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስው ዕውቀት ለማዳበር የተለያዩ ሚዲያዎችን(ሬዲዮ፣ ቴሌቭዥን ወዘተ.) መከታተል አለመከታተላቸውን መረጃ ለማግኘት የቀረበ ነበር፡፡ ከላይ በሰንጠረዥ 3 እንደሚታየው 14(35%) ተማሪዎች ይህን ብልሀት አንዳንዴ እንደሚጠቀሙ ሲገልፁ 10(25%) ተማሪዎች ደግሞ ሁል ጊዜ እንደሚከታተሉ ገልፀዋሉ፡፡ 6(15%) ተማሪዎች ደግሞ ይህን ብልሀት ባብዛኛው ሲጠቀሙ 6(15%) ተማሪዎች አልፎ አልፎ የሚጠቀሙ ናቸው፡፡ በጭራሽ ይህን ብልሀት የማይጠቀሙት 4(10%) እንደሚደርሱም የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡

ተጠኚዎች አዲሱን የሰዋስው ትምህርት ተግባራት ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር በሆነ መንገድ መማርን መጠቀም አለመጠቀማቸውን ለማወቅ ለቀረበው ጥያቄ 12(30%) የሚሆኑ ተጠኚዎች ሁል ጊዜ እንደሚጠቀሙ ሲመልሱ 9(22.5%) የሚሆኑ ተጠኚዎች ደግሞ አብዛኛውን ጊዜ እንደሚጠቀሙ ምላሽ ሰጥተዋሉ፡፡ ይህን ብልሀት አብዛኛውን ጊዜ ከሚጠቀሙት ጋር እኩል መጠን ያላቸው ተጠኚዎች አንዳንድ ጊዜ እንደሚጠቀሙ ከምላሻቸው ለመረዳት ተችሏል፡፡አልፎ አልፎ 8(20%)የሚሆኑ ተጥኝዎች ደግሞ እንደሚጠቀሙ ምላሽ ሰቱዋል፡፡ 2(5%) የሚሆኑ ተጠኚዎች ደግሞ ይህን ብልሀት በጭራሽ

የማይጠቀሙ መሆናቸውን አመልክተዋሉ። ይህን ብልሀት ሁል ጊዜ መጠቀማቸው የሰዋስውን ትምህርት በአጭር ጊዜ እንዲረዱ ይጠቅሟቸዋል።

ተጠኚዎች አዲሱን የሰዋስው ትምህርት ተግባራት ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ በሆነ መንገድ መማርን መጠቀም አለመጠቀማቸውን ለማወቅ ለቀረበው ጥያቄ 10(25%) የሚሆኑ ተጠኚዎች አንዳንድ ጊዜና ከነዚህ ጋር እኩል መጠን ያላቸው ተማሪዎች አልፎ አልፎ መጠቀማቸውን ሲገልፁ 8(20%) የሚሆኑት ሁል ጊዜ እንደሚጠቀሙ ገልፀዋሉ። በአንፃሩም 7(17.5.%) የሚያህሉ ተጠኚዎች ደግሞ ይህን ብልሀት ባብዘኛው የሚጠቀሙ ሲሆን 5(12.5%) የሚሆኑ ተጠኚዎች በጭራሽ የማይጠቀሙ መሆናቸው ከመረጃው ለማረጋገጥ ተችሏል።

ተማሪዎች የታላሚውን ቋንቋ ሰዋስው ለመማር ከሚያግዟቸው አእምሮታዊ ብልሀቶች አንዱ ቀደም ሲል የተማሩትን የሌላ ቋንቋ ሰዋስው ዕውቀት ለአዲሱ ቋንቋ ሰዋስው ትምህርት ዕውቀት በማሸጋገር መጠቀም ነው፡

በዚህ ክፍል ያለው ጥያቄ ተጠኚዎች ጠቃሚ ናቸው የሚሏቸውን የሰዋስው ፅንሰ ሀሳቦችንና አጠቃቀሞችን አጠር አድርገው በማስታውሻ ደብተራቸው የመያዝ ብልሀት አጠቃቀማቸውን ለማወቅ የቀረበ ነበር። ይህን ብልሀት 15(37.5%) የሚሆኑ ተጠኚዎች ሁል ጊዜ ሲጠቀሙ 9(22.5%) የሚሆኑ ተጠኚዎች ደግሞ አንዳንድ ጊዜ የሚጠቀሙ ናቸው። 6(15%) ተጠኚዎች ይህን ብልሀት ባብዘኛው እንደሚጠቀሙ ሲገልፁ በጭራሽ የማይጠቀሙት 6(15%) እንደሚደርሱ መረጃው ያመለክታል።

4(10%) ተጠኚዎች ደግሞ አልፎ አልፎ የሚጠቀሙ ናቸው። ማስታውሻ መያዝ ከተለያዩ ምንጮች(ከገለፃ፣ ከመፅሀፍ ወዘተ.) መረጃ መሰብሰብ ሲሆን ይህን ብልሀት አዘውትረው መጠቀማቸው የረሱትን መልሰው እንዲያገናዝቡ ይጠቅሟቸዋል።

ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስው አጠቃቀም ከአፍ መፍቻ ቋንቋ ሰዋስው አጠቃቀም ጋር እያነፃፀሩ መጠቀም አለመጠቀማቸውን ተጠይቀው 16(40%) የሚሆኑ ተተኳሪዎች ሁል ጊዜ መጠቀማቸውን ሲገልፁ 10(25%) የሚሆኑ ተተኳሪዎች ደግሞ አንዳንዴ እንደሚጠቀሙ ምላሻቸውን ሰጥተዋሉ። በአንፃሩም 9(22.5%) ተተኳሪዎች ይህን ብልሀት ባብዘኛው የሚጠቀሙ ሲሆን 4(10%) የሚያህሉት አልፎ አልፎ እንደሚጠቀሙ አመልክተዋሉ። 1(2.5%) ተተኳሪ ይህን ብልሀት በጭራሽ የማይጠቀም ነው።

ተጠኚዎች የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስው አጠቃቀም በቀላሉ ለመማር ወደአፍ መፍቻ ቋንቋ ሰዋስው አጠቃቀም የመተርጐም ብልሀት ይጠቀሙ እንደሆን ለመፈተሽ የቀረበ ነበር፡፡ በዚህም መሰረት ይህን ብልሀት 14(35%) የሚሆኑ ተጠኚዎች ሁል ጊዜ የሚጠቀሙ ሲሆን 10(25%) የሚያህሉት ደግሞ አንዳንዴ የሚጠቀሙ ናቸው፡፡ በአንፃሩም 8(20%) የሚሆኑ ተጠኚዎች ይህን ብልሀት ባብዛኛው የሚጠቀሙ ሲሆን 5(12.5%) የሚሆኑት ደግሞ አልፎ አልፎ እንደሚጠቀሙ መረጃው ያመለክታል፡፡ 3(7.5%) የሚሆኑ ተጠኚዎች ደግሞ ይህን ብልሀት በጭራሽ የማይጠቀሙ ናቸው፡፡ ይህ ብልሀት ተማሪዎች አዘውትረው ከሚጠቀሙት ብልሀት አንዱ ሲሆን ታላሚውን ቋንቋ ውስብስብ መዋቅሮችን በፍጥነትና በቅልጥፍና እንዲተነትኑና መረዳት እንዲችሉ ያስችሏቸዋል፡፡ ሁል ጊዜ መተርጐማቸው ደግሞ የባህል ልዩነት ወይም ፅንሰ ሀሳቡን የሚወክል ነገር ባጡ ጊዜ ወደስህተት ሊያመራቸው ይችላል፡፡

የታላሚው ቋንቋ ተማሪዎች በፅሁፍ ውስጥ ጠቃሚ የሆኑ ሰዋስዋዊ መረጃዎችን የተለያዩ ምልክቶችን በማድረግ መጠቀም አለመጠቀማቸውን ለመለየት የቀረበ ነበር፡፡ ይህን ብልሀት በተመለከተ በሰንጠረዥ 3 በተራ ቁጥር 15.1 ተማሪዎች በፅሁፍ ውስጥ የሚያጋጥሙ ጠቃሚ መረጃዎችን የተለያየ ቀለም ያለው ብዕር ይጠቀሙ እንደሆን ለመፈተሽ ለቀረበላቸው ጥያቄ

15(37.5%) የሚሆኑ ተማሪዎች ሁል ጊዜ እንደሚጠቀሙ ሲገልፁ 11(27.5%) የሚሆኑ ተማሪዎች ደግሞ አብዛኛውን ጊዜ እንደሚጠቀሙ የተገኘው መረጃ ይጠቁማል፡፡ በአንፃሩ 6(15%) ተማሪዎች አንዳንድ ጊዜና በእኩል መጠን  አልፎ አልፎ የሚጠቀሙ ናቸው፡፡ 2(5%) ተማሪዎች ደግሞ ይህን ብልሀት በጭራሽ የማይጠቀሙ መሆናቸውን አመልክተዋሉ፡፡

በጥያቄ 15.2 ተማሪዎች ጠቃሚ መረጃዎችን ከስራቸው በማስመር ይጠቀሙ እንደሆን ተጠይቀው 18(45%) ተማሪዎች ሁል ጊዜ እንደሚጠቀሙ ሲገልፁ 9(22.5%) ተማሪዎች ባብዛኛው የሚጠቀሙ ናቸው፡፡ በአንፃሩም 6(15%) የሚሆኑ ተማሪዎች ደግሞ ይህን ብልሀት አንዳንዴ ሲጠቀሙ 4(10%) ተማሪዎች አልፎ አልፎ የሚጠቀሙ ናቸው፡፡ በቁጥር 3(7.5%) የሚሆኑ ተማሪዎች ደግሞ ይህን ብልሀት በጭራሽ የማይጠቀሙ መሆናቸውን አመልክተዋሉ፡፡

ጥያቄ 15.3 ተማሪዎች በፅሁፍ ውስጥ የሚያጋጥሟቸውን ሰዋስዋዊ መረጃዎችን በማክበብ ይጠቀሙ እንደሆን ለመፈተሽ የቀረበ ነበር፡፡ ይህን ብልሀት 10(25%) የሚሆኑ ተማሪዎች

ባብዘኛው የሚጠቀሙ ሲሆን 9(22.5%) የሚሆኑ ተማሪዎች ሁል ጊዜ የሚጠቀሙ ናቸው። 7(17.5%) የሚሆኑ ተማሪዎች ይህን ብልሀት አንዳንዴ የሚጠቀሙ ሲሆን 8(20%)የሚሆኑተማሪዎች በጭራሽ የማይጠቀሙ ናቸው። 6(15%) የሚሆኑ ተማሪዎች ደግሞ ይህን ብልሀት አልፎ አልፎ የሚጠቀሙ መሆናቸውን ከመረጃው ለማረጋገጥ ተችሏል።

አብዘኞቹ ተማሪዎች በፅሁፍ ውስጥ የሚያጋጥሟቸውን ሰዋስው መረጃዎችን የተለያየ ቀለም ባለው ብዕር ከመፃፍና ከማክበብ ይልቅ ከስሩ የማስመር ብልሀቶችን በበለጠ እንደሚጠቀሙ ከመረጃው መረዳት ተችሏል። ተማሪዎች ይህን ብልሀት አዘውትረው መጠቀማቸው ዋና ዋና ነጥቦችን ቶሎ እንዲለዩ ይጠቅሟቸዋል።

በምዕራፍ ሁለት ለመግለፅ እንደተሞከረው አእምሮታዊ ብልሀቶች በቋንቋ ተማሪዎች በስፋት የሚተገበሩ ሆነው ተማሪው የቋንቋ ትምህርት ተግባራትን መረዳትና መገንዘብ እንዲችል እገዛ የሚያደርጉ ብልሀቶች ናቸው። የዚህ ጥናት ውጤትም ከዚህ ሀሳብ ጋር የሚስማማ ነው። ይኸውም ከተሰበሰበው መረጃ ትንተና ውጤት መረዳት እንደተቻለው ህጎችን ደጋግሞ መፃፍና መናገርን፣

ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር መማርን፣ ጠቃሚ ሀሳቦችን አጠር አድርጎ ማስታወሻ መያዝን፣ ከአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ጋር ማነፃፀርን፣ ወደ አፍ መፍቻ ቋንቋ መተርጎምንና በፅሁፍ ውስጥ ጠቃሚ የሆኑ ሰዋስዋዊ መረጃዎችን የተለያዩ ምልክቶችን በማድረግ የመጠቀም ብልሀቶችን አዘውትረው እንደሚገለገሉ የተገኘው ውጤት ያመለክታል።

ባጠቃላይ በ4.1.2 ስር ለመግለፅ እንደተሞከረው ይህን ብልሀት 157(39.25%) ተጠኚዎች ሁል ጊዜ 97(24.25%) ተጠኚዎች አብዘኛውን ጊዜ፣ 115(28.75%) ተጠኚዎች ደግሞ አንዳንድ ጊዜ፣ 70(17.5%) ተጠኚዎች አልፎ አልፎ የሚጠቀሙ ሲሆን፣ 41(10.2%) የሚሆኑ ተጠኚዎች ደግሞ በጭራሽ የማይጠቀሙ ናቸው። ይህ አብላጫ (ከፍተኛ) ቁጥር ያላቸው ተጠኚዎች ብልሀቱን ሁል ጊዜ መጠቀማቸው የተማሪዎች የዚህ ብልሀት አጠቃቀማቸው ከፍተኛ መሆኑን ያረጋግጣል።

## ሰንጠረዥ 4. የማካካሻ ብልሀቶች መረጃ

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | አማራጮች | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሁል ጊዜ | | አብዘኛውን ጊዜ | | አንዳንድ ጊዜ | | አልፎ አልፎ | | በጭራሽ | |
| | | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% |
| 16 | ምልክት መጠቀም<br>16.1 በአንገት እንቅስቃሴ | 6 | 15 | 4 | 10 | 10 | 25 | 12 | 30 | 8 | 20 |
| | 16.2 በእጅ እንቅስቃሴ | 12 | 30 | 6 | 15 | 10 | 25 | 7 | 17.5 | 5 | 12.5 |
| 17 | መገመት | 7 | 17.5 | 11 | 27.5 | 12 | 30 | 8 | 20 | 2 | 5 |

### 4.1.3 የማካካሻ ብልሀቶች መረጃ ትንተናና ማብራሪያ

የማካካሻ ብልሀቶች ተማሪዎች በቋንቋ አጠቃቀም ወቅት በሰዋስው ዕውቀት እጥረት የተነሳ የሚያጋጥሟቸውን ችግሮችን ለማለፍ ወይም ጉድለቱን ለመሙላት የሚገለገሉባቸው ብልሀቶች ናቸው፡፡ የተማሪዎች የዚህን ብልሀት አጠቃቀማቸውን በሚመለከት በፅሁፍ መጠይቅ በተሰበሰበው መረጃ መሰረት ዝቅተኛ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በእያንዳንዱ አማራጭ ስር ሰስቱን የማካካሻ ብልሀቶች ጥያቄ የመለሱ ተማሪዎች ድምር በቁጥርና ምላሽ የሰጡ ተማሪዎች ድምር ለአጠቃላይ ተማሪዎች ድምር ተካፍሎ በመቶ በማባዛት በመቶኛ ተተንትኗል፡፡ በዚሁ መሰረት ይህንን ብልሀት ሁል ጊዜ እንጠቀማለን ያሉት ተማሪዎች 25(20%) ሲሆን 27(22.5%) የሚሆኑት ተማሪዎች አልፎ አልፎ የሚጠቀሙና 15(12.5%) የሚያህሉ ተማሪዎች በጭራሽ የማይጠቀሙ ናቸው፡፡ ይህ ዝቅተኛነቱን ያሳያል፡፡ 21(17.5.%) የሚያህሉ ተማሪዎች አብዘኛውን ጊዜ እንጠቀማለን ያሉት ሲሆን 32(26.6% አንዳንድ ጊዜ እንደሚጠቀሙ ገልፀዋሉ፡፡ ይሄም ደግሞ ሌላው ዝቅተኛ መሆኑን

የሚያሳይ ነው፡፡ ቀጥሎ የዚህን ዝርዝር ብልሀቶችን የሚመለከቱ መረጃዎች ከተራ ቁጥር 16-17 ድረስ በሰንጠረዥ ቀርበው ተተንትነዋል፡፡

በጥያቄ 16.1ተማሪዎች የሚያጋጥሟቸውን የሰዋስው ጉድለት ለመሙላት የአንገት እንቅስቃሴን ይጠቀሙ እንደሆን ለተጠየቁት 12(30%) የሚሆኑ ተማሪዎች አልፎ አልፎ እንደሚጠቀሙ ሲመልሱ 10(25%) የሚሆኑ ተማሪዎች ደግሞ አንዳንዴ እንደሚጠቀሙ መልሰዋሉ፡፡ በአንፃሩም 8(20%) ተማሪዎች ይህን ብልሀት በጭራሽ የማይጠቀሙ መሆናቸውን አረጋግጠዋሉ፡፡ 6(15%) የሚደርሱ ተማሪዎች ደግሞ ይህን ብልሀት ሁል ጊዜ የሚጠቀሙ ሲሆን 4(10%) ተማሪዎች ባብዛኛው የሚጠቀሙ መሆናቸውን ከምላሻቸው ለመረዳት ተችሏል፡፡

ተማሪዎች በተግባቦት ሂደት የሚያጋጥሟቸውን የሰዋስው ክፍተት ለመሙላት የተለያዩ አካላዊ ምልክቶችን ይጠቀሙ እንደሆን ለመፈተሸ የቀረበ ነበር፡፡ በጥያቄ 16.2 የሰዋስው ትምህርት የእጅ እንቅስቃሴን በመጠቀም ይማሩ እንደሆን ተጠይቀው በቁጥር 12(30%) የሚሆኑ ተተኳሪዎች ሁል ጊዜ እንደሚጠቀሙ ሲገልፁ 10(25%) የሚሆኑት ደግሞ አንዳንድ ጊዜ የሚጠቀሙ መሆናቸውን ገልፀዋሉ፡፡ በአንፃሩም 5(12.5%) የሚሆኑ ተተኳሪዎች ደግሞ ይህን ብልሀት በጭራሽ የማይጠቀሙ ናቸው፡፡ የሚደርሱ ተተኳሪዎች ደግሞ ይህን ብልሀት በእኩል መጠን 6(15%)ባብዛኛውና7(17.5%) አልፎ አልፎ የሚጠቀሙ መሆናቸውን አመልክተዋሉ፡፡ ይህ ብልሀት ተማሪዎች አዘውትረው የሚጠቀሙት ሲሆን በንግግር ሂደት የሰዋስው እጥረት ሲያጋጥሟቸው ማሟያ በመሆን ይጠቅሟቸዋል፡፡

ተጠኚዎች የታላሚውን ቋንቋ በመማር ሂደት የሚያጋጥሟቸውን እንግዳ የሆኑ መዋቅሮችን ከአውዱ የመገመት ብልሀት አጠቃቀማቸውን ለመመርመር ተጠይቀዋሉ፡፡ በዚሁ መሰረት 12(30%) የሚሆኑ ተጠኚዎች ይህን ብልሀት አንዳንድ ጊዜ የሚጠቀሙ ሲሆን 11(27.5%) የሚሆኑ ተጠኚዎች ባብዛኛው እንደሚጠቀሙ ገልፀዋሉ፡፡ 8(20%) የሚያህሉ ተጠኚዎች ደግሞ ይህን ብልሀት አልፎ አልፎ እንደሚጠቀሙ ሲገልፁ 7(17.5%) የሚያህሉት ደግሞ ሁል ጊዜ የሚጠቀሙ መሆናቸውን ገልዋሉ፡፡ 2(5%) ተጠኚዎች ይህን ብልሀት በጭራሽ የማይጠቀሙ መሆናቸውን መረጃው ያረጋግጣል፡፡

ከላይ በሠንጠረዥ 4 እንደሚታየው ተማሪዎች በሰዋስው ትምህርት ሂደት የሚያጋጥሙ ሰዋስው ጉድለቶችን ለመሙላት ብልሀቶቹን አብዛኞቹ ተማሪዎች አንዳንድ ጊዜ እንደሚጠቀሙ የመረጃ ትንተና ውጤት ያሳያል፡፡ ይህም ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ

ሰዋስው ትምህርት ሂደት ሰዋስው ጉድለቶችን በመሙላት የመጠቀማቸው ሁኔታ ዝቅተኛ መሆኑን ያመለክታል፡፡ የዚህ መረጃ ውጤት በተዛማጅ ፅሁፍ ቅኝት ከተገለፀው ሀሳብ ጋር የሚቃረን ነው፡፡ የማካካሻ ብልሀቶች ተማሪዎች ሰዋስው ብቃት እንዲያዳብሩ በጣም አጋዥ ሆኖ ሳለ አንዳንድ ጊዜ መጠቀማቸው የማይጣጣም መሆኑን ያመለክታል፡፡

ባጠቃላይ በ4.1 ስር እንደተገለጸው ቀጥተኛ የመማር ብልሀቶችን 283(28.4%) ተጠኚዎች ሁል ጊዜ፣ 219(21.96%) ተጠኚዎች አብዘኛውን ጊዜ፣ 246(24.7%) ተጠኚዎች አንዳንድ ጊዜ፣ 168(16.85%) ተጠኚዎች ደግሞ አልፎ አልፎ የሚጠቀሙ ሲሆን 81(8.12%) ተጠኚዎች በጭራሽ የማይጠቀሙ መሆናቸውን የተሰበሰበው መረጃ ትንተና ውጤት ያመለክታል፡፡ ይህ በርካታ ቁጥር ያላቸው ተጠኚዎች በርካታ ብልሀቶችን አንዳንድ ጊዜ መጠቀማቸው የተማሪዎች ቀጥተኛ ሰዋስው የመማር ብልሀት አጠቃቀማቸው ዝቅተኛ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

## 4.2. ኢቀጥተኛ የመማር ብልሀቶች ትንተና ማብራሪያ

በኢቀጥተኛ ብልሀቶች ስር ሶስት ንዑሳን ብልሀቶች ይካተታሉ፡፡ እነሱም፡- ልዕለ አእምሮታዊ፣ ስሜታዊና ማህበራዊ ብልሀቶች ናቸው፡፡ የኢቀጥተኛ ብልሀቶች አጠቃቀማቸው ከቀጥተኛ ብልሀቶች አጠቃቀማቸው የተሻለ ቢሆንም በጣም ከፍተኛ ሆኖ አልተገኘም፡፡

በሶስቱ ንዑሳን ምድቦች ውስጥ የሚገኙ ዝርዝር ብልሀቶችን አዘውትረው እንደሚጠቀሙ መልስ እንዲሰጡ 16 ጥያቄዎች ለተማሪዎች በፅሁፍ መጠይቅ ቀርቦላቸው ነበር፡፡ በእያንዳንዱ አማራጭ ስር አስራ ኢ ቀጥተኛ ሰስቱን የመማር ብልሀቶችን ጥያቄ የመለሱ ተማሪዎች ድምር በቁጥርና ምላሽ የሰጡ ተማሪዎች ድምር ለአጠቃላይ ተማሪዎች ድምር ተካፍሎ በመቶ በማባዛት በመቶኛ ተተንትኗል፡፡ በዚሁ መሰረት 29(5.17%) የሚያህሉ ተማሪዎች እነዚህን ብልሀቶች ፍፁም እንደማይጠቀሙ ነው ምላሽ የሰጡት፡፡ ይሄ የተማሪዎች የኢቀጥተኛ ብልሀት አጠቃቀማቸው ዝቅተኛ መሆኑን ያሳያል፡፡ አንዳንድ ጊዜ እንጠቀማለን ያሉት ተማሪዎች ብዛት 144(25.71%) ሲሆን 87(15.53%) የሚያህሉ ተማሪዎች አልፎ አልፎ እንደሚጠቀሙ ገልፀዋሉ፡፡ ይሄም ዝቅተኛነቱን የሚያመለክት ነው፡፡ 180(32.14%) የሚያህሉ ተማሪዎች ሁል ጊዜ እንደሚጠቀሙ ሲገልፁ 120(21.42%) የሚያህሉ ተማሪዎች ደግሞ አብዘኛውን ጊዜ እንደሚጠቀሙ የገለፁ ናቸው፡፡ ይሄም ደግሞ ሌላው ከፍተኛ ያለመሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ አጠቃላይ ኢቀጥተኛ ብልሀቶች አጠቃቀም በተመለከተ የመረጃ ትንተናና ውጤት ቀጥሎ ባሉት ሰንጠረዦች ቀርቧል፡፡

## ሰንጠረዥ 5. የልዕለ አእምሮታዊ ብልሀቶች መረጃ

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | አማራጮች | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሁል ጊዜ | | አብዛኛውን ጊዜ | | አንዳንድጊዜ | | አልፎ አልፎ | | በጭራሽ | |
| | | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% |
| 18 | ማቀድ | 15 | 37.5 | 8 | 20 | 9 | 22.5 | 5 | 12.5 | 3 | 7.5 |
| 19 | ትኩረት መስጠት | 15 | 37.5 | 9 | 22.5 | 9 | 22.5 | 5 | 12.5 | 2 | 5 |
| 20 | ማደራጀት | 16 | 40 | 7 | 17.5 | 9 | 22.5 | 7 | 17.5 | 1 | 2.5 |
| 21 | ራስን መቆጣጠር | 9 | 22.5 | 8 | 20 | 14 | 35 | 7 | 17.5 | 2 | 5 |

### 4.2.1 የልዕለ አእምሮታዊ ብልሀቶች መረጃ ትንተናና ማብራሪያ

የተማሪዎች የልዕለ አእምሮታዊ ብልሀት አጠቃቀማቸው ከፍተኛ ነው፡፡ ተማሪዎች ይህንን ብልሀት አዘውትረው እንደሚጠቀሙ ምላሽ እንዲሰጡ ፅሁፍ መጠይቅ ቀርቦላቸው ነበር፡፡ በእያንዳንዱ አማራጭ ስር አምስቱን ልዕለ አእምሮታዊ ብልሀቶች ጥያቄ የመለሱ ተማሪዎች ድምር በቁጥርና ምላሽ የሰጡ ተማሪዎች ድምር ለአጠቃላይ ተማሪዎች ድምር ተካፍሎ በመቶ በማባዛት በመቶኛ ተተንትኗል፡፡ በዚሁ መሰረት 55(43.37%) የሚያህሉ ተማሪዎች ሁል ጊዜ ሲጠቀሙ 24(15 %) የሚሆኑ ተማሪዎች አልፎ አልፎ የሚጠቀሙና 8(5%) የሚያህሉ ተማሪዎች ደግሞ በጭራሽ እንደማይጠቀሙ ገልፀዋሉ፡፡ ይሄ የተማሪዎች የብልሀት አጠቃቀማቸው የማያኮራ መሆኑን ያሳያል፡፡ ሌላው ደግሞ ይህንን ብልሀት አብዛኛውን ጊዜ እንጠቀማለን ያሉት ተማሪዎች ብዛት 32(20%) ያህል ሲሆን 41(25.6%) የሚያህሉ ተማሪዎች ደግሞ አንዳንድ ጊዜ እንደሚጠቀሙ ነው ምላሽ የሰጡት፡፡ ይሄም የሚያኮራ ያለመሆኑን ያመለክታል፡፡ አብዛኞቹ ተማሪዎች የሰዋስው ትምህርት ሂደት ምቹ እንዲሆን ለማድረግ ከልዕለ አእምሮታዊ ብልሀቶች ውስጥ ማቀድን፣ ትኩረት መስጠትን፣ ማደራጀትንና ራስን መገምገምን አዘውትረው የሚጠቀሙባቸው ብልሀቶች ናቸው፡፡

ተማሪዎች እነዚህን ብልሀቶች አዘውትረው መጠቀማቸው የሰዋስው ትምህርትን ቅደም ተከተልን

ጠብቀው እንዲጓዙና ወደፊት ከሰዋስው ትምህርት የሚጠብቁትን ነገሮች ቀድመው ለይተው እንዲይዙ ያግዟቸዋል፡፡ የሰዋስው ትምህርት ምን ያክል እንዳወቁና በትምህርታቸው ወደኋላ እንዳይቀሩ ይረዷቸዋል፡፡ ሆኖም እነዚህን ብልሀቶች ሁል ጊዜ መጠቀማቸው ዋና ዋና ሀሳቦች ላይ ብቻ እንጂ በጥቃቅን ጉዳዮች ላይ እንዳያተኩሩ ያደርጓቸዋል፡፡ እነዚህን ዝርዝር ብልሀቶችን የሚመለከቱ ከተራ ቁጥር 18-21 ድረስ ያሉት ጥያቄዎች ቀጥሎ ባለው ሰንጠረዥ ቀርበው ተተንትነዋል፡፡

ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስውን ለምን እንደሚማሩ፣ ከትምህርቱ በኋላ ምን እንደሚጠብቁ ዓላማ ይነድፉ እንደሆን ለመመርመር የቀረበ ነበር፡፡ ከላይ በሰንጠረዥ 5 እንደሚታየው 15(37.5%) የሚሆኑ ተማሪዎች ሰዋስውን ለመማር ሁል ጊዜ ዓላማ የሚነድፉ ሲሆን 9(22.5%) የሚያህሉት አንዳንዴ የሚነድፉ ናቸው፡፡ 8(20%) የሚሆኑ ተማሪዎች ደግሞ ይህን ብልሀት ባብዛኛው የሚጠቀሙ ሲሆን 5(12.5%) የሚሆኑት አልፎ አልፎ እንደሚጠቀሙ መረጃው ይጠቁማል፡፡ 3(7.5%) የሚሆኑት ደግሞ ይህን ብልሀት በጭራሽ የማይጠቀሙ ናቸው፡፡ ይህ ብልሀት ተማሪዎች አዘውትረው ከሚጠቀሙባቸው ብልሀቶች አንዱ ሲሆን የሰዋስውን ትምህርት ቅደም ተከተልን ጠብቀው እንዲማሩና ወደፊት ከሰዋስው ትምህርት የሚጠብቁትን ነገሮች ቀድመው ለይተው እንዲይዙ ያግዟቸዋል፡፡ ሆኖም ይህን ብልሀት ሁል ጊዜ መጠቀማቸው ዋና ዋና ሀሳቦች ላይ ብቻ እንጂ በዝርዝር ጉዳዮች ላይ እንዳያተኩሩ ያደርጓቸዋል፡፡

ተጠኚዎች ለታላሚው ቋንቋ ሰዋስው ትምህርት በራሳቸው ተነሳሽነት በጣም አስፈላጊ ናቸው ለሚሏቸው ተግባራት ቅድሚያ መስጠት አለመስጠታቸውን ተጠይቀው 15(37.5%) የሚሆኑ ሁልጊዜ ተጠኚዎች በጣም አስፈላጊዎችን መርጠው ትኩረት እንደሚሰጡ ሲገልፁ 9(22.5%) የሚሆኑት ደግሞ በእኩል መጠን አብዛኛውን ጊዜና አንዳንድ ጊዜ መርጠው ትኩረት እንደሚያደርጉ ገልፀዋሉ፡፡ 5(12.5%) የሚያህሉት ተጠኚዎች ደግሞ ይህን ብልሀት አልፎ አልፎ ሲገለገሉ 2(5%) ተጠኚዎች በጭራሽ የማይገለገሉ መሆናቸውን ከምላሻቸው ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ይህ ብልሀት ተማሪዎች አዘውትረው የሚጠቀሙት ሲሆን የሰዋስውን ትምህርት እንዲመራመሩና በሰዋስው ትምህርት ጥልቅ እውቀት እንዲኖራቸው ያደርጋቸዋል፡፡ ተማሪዎች ከልዕለ አእምሮታዊ ብልሀቶች ውስጥ ትኩረት የመስጠት ብልሀትን በይበልጥ እንደሚጠቀሙ (Temesgen 2013) ይገልፃሉ፡፡

ተተኳሪዎች የሰዋስውን ትምህርት ለመማር ተግባራትን በማቀድ፣ የጥናትና የልምምድ ፕሮግራም በማዘጋጀት ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር የሚያደርጉትን ጥረት ለመመርመር ቀርቧል፡፡ በዚህም 16(40%) የሚሆኑት ተተኳሪዎች ለትምህርታቸው ምቹ ሁኔታን የመፍጠር ብልሀት ሁል ጊዜ እንደሚጠቀሙ ሲገልፁ 9(25.5%) ተተኳሪዎች አንዳንድ ጊዜ እንደሚጠቀሙ ገልፀዋሉ፡፡ በአንፃሩም 7(17.5 %) የሚያህሉት ተተኳሪዎች በእኩል መጠን አብዘኛውን ጊዜና አልፎ አልፎ እንደሚጠቀሙ ገልፀዋሉ፡፡ 1(2.5%) ተተኳሪዎች ደግሞ ይህን ብልሀት በጭራሽ የማይጠቀሙ መሆናቸውን መረጃው ያመለክታል፡፡

ተማሪዎች በሰዋስው ትምህርት ሂደት የሚፈጠረውን ስህተት የሌላው አካል ጣልቃ ገብነት ሳይኖር የራሳቸውን የሰዋስው አጠቃቀም ስህተት በራሳቸው የመለየት ብልሀት መጠቀም አለመጠቀማቸውን ተጠይቀው 14(35%) ተማሪዎች ይህን ብልሀት አንዳንድ ጊዜ የሚጠቀሙ መሆናቸውን ሲገልፁ 7(17.5%) የሚሆኑ ተማሪዎች ደግሞ አልፎ አልፎ እንደሚጠቀሙ ገልፀዋሉ፡፡ በአንፃሩም 9(22.5%) የሚያህሉ ተማሪዎች ደግሞ ይህን ብልሀት ሁል ጊዜ ሲጠቀሙ 8(20%) ተማሪዎች ባብዘኛው እንደሚጠቀሙ አመልክተዋሉ፡፡ ይህን ብልሀት በጭራሽ የማይጠቀሙት በቁጥር 2(5%) እንደሚደርሱም ከምላሻቸው ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ባጠቃላይ በ4.2.1 ስር ለማየት እንደተሞከረው ይህን ብልሀት 55(34.37%) ተጠኚዎች ሁል ጊዜ፣ 24(15%) ተጠኚዎች አልፎ አልፎ፣ 32(20%) ተጠኚዎች አብዘኛውን ጊዜ፣ 41(25.6%) ተጠኚዎች አንዳንድ ጊዜ የሚጠቀሙ ናቸው፡፡ ሌላው ደግሞ ይህንን ብልሀት 8(5%)ተጠኚዎች ደግሞ በጭራሽ የማይጠቀሙ ናቸው፡፡ ይህ 55(34.37%) ተጠኚዎች ሁል ጊዜ መጠቀማቸው የተማሪዎች ልዕለ አእምሮታዊ ብልሀት አጠቃቀማቸው ከፍተኛ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

በምዕራፍ ሁለት እንደተገለፀው ልዕለ አእምሮታዊ ብልሀቶች በቋንቋ ተማሪዎች በስፋት የሚተገበሩ ሆነው ተማሪዎች የትምህርታቸውን ሂደት ለማመቻቸት የሚገለገሉባቸው ብልሀቶች ናቸው፡፡ በመሆኑም የዚህ ጥናት ውጤትም ከዚህ ሀሳብ ጋር የሚስማማ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

### ሰንጠረዥ 6. የስሜታዊ ብልሀቶች መረጃ

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | አማራጮች | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሁል ጊዜ | | አብዘኛውን ጊዜ | | አንዳንድ ጊዜ | | አልፎ አልፎ | | በጭራሽ | |
| | | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% |
| 22 | ጭንቀትን መቀነስ | 14 | 35 | 7 | 17.5 | 11 | 27.5 | 6 | 15 | 2 | 5 |
| 23 | ራስን ማበረታታት | 11 | 27.5 | 10 | 25 | 8 | 20 | 8 | 20 | 3 | 7.5 |
| 24 | ስሜትን ማጋራት<br>24.1 ለክፍልጓደኞቼ | 12 | 30 | 9 | 22.5 | 14 | 35 | 2 | 5 | 3 | 7.5 |
| | 24.2 ለመምህሮቼ | 8 | 20 | 6 | 15 | 13 | 32.5 | 11 | 27.5 | 2 | 5 |
| 25 | አዎንታዊ ገለፃ መስጠት | 13 | 32.5 | 8 | 20 | 7 | 17.5 | 8 | 20 | 4 | 10 |
| 26 | ሀላፊነትን መቀበል | 14 | 35 | 10 | 25 | 8 | 20 | 6 | 15 | 2 | 5 |

### 4.2.2. የስሜታዊ ብልሀቶች መረጃ ትንተናና ማብራሪያ

የተማሪዎች ስሜታዊ ብልሀቶች አጠቃቀማቸው ከፍተኛ ነው፡፡ በእያንዳንዱ አማራጭ ስር ሰባቱን ስሜታዊ ብልሀቶች ጥያቄ የመለሱ ተማሪዎች ድምር በቁጥርና ምላሽ የሰጡ ተማሪዎች ድምር ለአጠቃላይ ተማሪዎች ድምር ተካፍሎ በመቶ በማባዛት በመቶኛ ተተንትኗል፡፡ በዚሁ መሰረት 72(30%) የሚያህሉ ተማሪዎች ሁል ጊዜ የሚጠቀሙ ሲሆን በአንፃሩም 61(25.41%) የሚያህሉ ተማሪዎች አንዳንድ ጊዜ የሚጠቀሙና 41(9.8%) የሚያህሉ ተማሪዎች ደግሞ አልፎ አልፎ የሚጠቀሙ ናቸው፡፡ ይሄ ከፍተኛ ያለመሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ በተጨማሪም 50(20.8%) የሚያህሉ ተማሪዎች አብዘኛውን ጊዜ የሚጠቀሙ ሲሆን 16(6.6%) የሚያህሉ ተማሪዎች ደግሞ በጭራሽ እንደማይጠቀሙ ነው የገለፁት፡፡ ይሄ ደግሞ ሌላው ዝቅተኛ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ ከስሜታዊ ብልሀቶች ውስጥ ጭንቀት መቀነስን፣ ራስን ማበረታታትን፣ አዎንታዊ ገለፃ መስጠትንና ሀላፊነት መቀበልን አዘውትረው የሚጠቀሙባቸው ብልሀቶች ሲሆኑ እነዚህን ብልሀቶች አዘውትረው መጠቀማቸው በሰዋስው ትምህርት ሂደት በራስ የመተማመንን ስሜት በማዳበር፣

ያለፍርሀት በንቃት እንዲሳተፉና በሰዋስው ትምህርታቸው ውጤታማ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል፡፡

ቀጥሎ የዚህን ዝርዝር ብልሀቶችን የሚመለከቱ መረጃዎች ከተራ ቁጥር 22-26 ድረስ ትንተና ተካሂዶባቸዋል፡፡

ተማሪዎች ከሰዋስው ትምህርት በፊት የድካምና የመጫጫን ስሜት ለመቀነስ አካላቸውንና አእምሯቸውን የሚያዝናኑ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የቀረበ ነበር፡፡ በዚሁ መሰረት 14(35%) የሚሆኑ ተማሪዎች ከሰዋስው ትምህርት በፊት አካላቸውንና አእምሯቸውን የማዝናናት ብልሀት ሁል ጊዜ የሚጠቀሙ ሲሆን 11(27.5%) የሚሆኑት ደግሞ አንዳንድ ጊዜ እንደሚጠቀሙ አረጋግጠዋሉ፡፡ 7(17.5%) ተማሪዎች ይህን ብልሀት ባብዘኛው የሚጠቀሙ ሲሆን 6(15%) ያላቸው ተማሪዎች አልፎ አልፎ የሚጠቀሙ ናቸው፡፡ ይህን ብልሀት በጭራሽ የማይጠቀሙት ደግሞ 2(5%) የሚደርሱ መሆናቸው ከምላሻቸው ተረጋግጧል፡፡ ይህ ብልሀት ተማሪዎች አዘውትረው የሚጠቀሙት ሲሆን ለቋንቋ ትምህርት ውጤታማነት አስፈላጊ ብልሀት መሆኑን አንዳንድ ምሁራን ይገልፃሉ፡፡ ተማሪዎች በከፍተኛ መነቃቃት በአነስተኛ ጭንቀት ቋንቋ መማርን ያፋጥናሉ፡፡

ተማሪዎች አዲሱን የሰዋስው ትምህርት ለመማር ሰውነታቸው የሚፈልገውን ነገር(የሚበላ፣ የሚጠጣ ወዘተ.) በመስጠት የማበረታታት ብልሀት መጠቀም አለመጠቀማቸውን

ለመፈተሽ ቀርቦ 11(27.5%) የሚሆኑ ተተኳሪዎች ሁል ጊዜ የሚጠቀሙ መሆናቸውን ሲገልፁ 10(25%) ተተኳሪዎች ባብዘኛው የሚጠቀሙ መሆናቸውን ገልፀዋሉ፡፡ በአንፃሩም 8(20%) የሚሆኑ ተተኳሪዎች ደግሞ ይህን ብልሀት አልፎ አልፎ ሲጠቀሙ 8(20%) የሚያህሉ ተተኳሪዎች አንዳንድ ጊዜ የሚጠቀሙ ናቸው፡፡ 3(7.5%) የሚደርሱ ተተኳሪዎች ደግሞ ይህን ብልሀት በጭራሽ የማይጠቀሙ መሆናቸውን ከመረጃው ለመረዳት ተችሏል፡፡

ከላይ በሰንጠረዥ 6 በጥያቄ 24 ስር ተማሪዎች በሰዋስው ትምህርት ሂደት የሚያድርባቸውን ውስጣዊ ስሜት ለሌሎች በማካፈል ይማሩ እንደሆን ተጠይቀዋሉ፡፡ በዚህ መሰረት በጥያቄ 24.1 ተጠኚዎች በሰዋስው ትምህርት ሂደት የሚያድርባቸውን ውስጣዊ ስሜት ለክፍል ጓደኞቻቸው የማካፈል ብልሀት መጠቀም አለመጠቀማቸውን ተጠይቀው 14(35%) የሚሆኑ ተጠኚዎች አንዳንድ ጊዜ መጠቀማቸውን ሲገልፁ 12(30%) የሚያህሉ ተጠኚዎች ደግሞ ሁል ጊዜ የሚጠቀሙ መሆናቸውን ገልፀዋሉ፡፡ 9(22.5%) ተጠኚዎች ደግሞ ይህን ብልሀት ባብዘኛው የሚጠቀሙ ሲሆን 3(7.5%) ተጠኚዎች በጭራሽ

የማይጠቀሙ ናቸው። ይህን ብልሀት አልፎ አልፎ የሚጠቀሙት 2(5%) እንደሚደርሱም መረጃው ያመለክታል።

እንደዚሁም በጥያቄ 24.2 ተጠኚዎች በሰዋስው ትምህርት ሂደት የሚያድርባቸውን ውስጣዊ ስሜት ለመምህሮቻቸው የማካፈል ብልሀት መጠቀም አለመጠቀማቸውን ተጠይቀው 13(32.5%) የሚያህሉ ተጠኚዎች አንዳንዴ እንደሚጠቀሙ ሲገልፁ 11(27.5%) የሚሆኑ ተጠኚዎች አልፎ አልፎ እንደሚጠቀሙ ገልፀዋሉ። በአንፃሩም 8(20%) የሚደርሱ ተጠኚዎች ይህን ብልሀት ሁል ጊዜ የሚጠቀሙ ሲሆን 6(15%) ተጠኚዎች ባብዛኛው የሚጠቀሙ ናቸው። ይህን ብልሀት በጭራሽ የማይጠቀሙት ተጠኚዎች 2(5%) እንደሚደርሱም ምላሻቸው ያስረዳል።

ባጠቃላይ ተማሪዎች በሰዋስው ትምህርት ሂደት የሚያጋጥማቸውን ውስጣዊ ስሜት ከመምህሮቻቸው ይልቅ ለክፍል ጓደኞቻቸው የሚያካፍሉ ቢሆንም ብልሀቱን አንዳንድ ጊዜ እንደሚጠቀሙ ከመረጃው ለመረዳት ተችሏል።

ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ተግባራትን ለማከናወን የሚችሉ ጎበዞች አድርገው ራሳቸውን የሚቆጥሩ መሆናቸውን ለመፈተሽ የቀረበ ነበር። 13(32.5%) የሚሆኑ ተጠኚዎች ሁል ጊዜ ራሳቸውን እንደጎበዝ ተማሪዎች አድርገው የሚቆጥሩ ሲሆን 8(20%) የሚሆኑት ደግሞ አብዛኛውን ጊዜ ይህን ብልሀት የሚጠቀሙ ናቸው። በአንፃሩም 7(17.5%) የሚያህሉ ተጠኚዎች ደግሞ ይህን ብልሀት አንዳንዴ የሚጠቀሙ ሲሆኑ 8(20%) የሚሆኑ ተጠኚዎች አልፎ አልፎ የሚጠቀሙ ናቸው። 4(10%) የሚሆኑ ተጠኚዎች ደግሞ በጭራሽ ራሳቸውን እንደጎበዝ ተማሪ አድርገው የማይቆጥሩ መሆናቸውን መረጃው ያመለክታል። ተማሪዎች ይህን ብልሀት አዘውትረው መጠቀማቸው በራስ የመተማመንን ስሜት በማዳበር በሰዋስው ትምህርታቸው ውጤታማ እንዲሆኑ ያደርጓቸዋል።

ተማሪዎች በሰዋስው ትምህርት ሂደት ስህተት ቢፈጥሩም መሳሳት ያለመሆኑን በመረዳት ሃላፊነትን ይወስዱ እንደሆን ተጠይቀዋሉ። በዚህ መሰረት 14(35%) የሚሆኑ ተጠኚዎች ይህን ብልሀት ሁል ጊዜ እንደሚጠቀሙ ሲመልሱ 10(25%) የሚሆኑ ተጠኚዎች ደግሞ ባብዛኛው እንደሚጠቀሙ መልሰዋሉ። በአንፃሩ 8(20%) ተጠኚዎች ይህን ብልሀት አንዳንዴ የሚጠቀሙ ሲሆኑ 6(15%) የሚያህሉ ተጠኚዎች ደግሞ አልፎ አልፎ የሚጠቀሙ መሆናቸውን መልሰዋሉ። 2(5%) የሚሆኑት ይህን ብልሀት በጭራሽ የማይጠቀሙ ናቸው። ተማሪዎች ይህን ብልሀት አዘውትረው መጠቀማቸው በሰዋስው ትምህርት ሂደት ሳይፈሩ በንቃት እንዲሳተፉ ያደርጓቸዋል።

ከላይ የመረጃ ትንተና ውጤት እንደሚያመለክተው ተማሪዎች ስሜታዊ ብልሀቶችንም አዘወትረው እንደሚጠቀሙ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

## ሰንጠረዥ 7. የማህበራዊ ብልሀቶች መረጃ

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | አማራጮች | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሁል ጊዜ | | አብዘኛውን ጊዜ | | አንዳንድ ጊዜ | | አልፎ አልፎ | | በጭራሽ | |
| | | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% |
| 27 | መተባበርመደጋገፍ | 16 | 40 | 8 | 20 | 10 | 25 | 5 | 12.5 | 1 | 2.5 |
| 28 | ችሎታ ያላቸውን ማብራሪያ መጠየቅ | 10 | 25 | 9 | 22.5 | 13 | 32.5 | 7 | 17.5 | 1 | 2.5 |
| 29 | ለአስተማሪዉ ጥያቄ ማቅረብ | 13 | 32.5 | 11 | 27.5 | 10 | 25 | 4 | 10 | 2 | 5 |
| 30 | ባህላዊ ግንዛቤ ማዳበር | 14 | 35 | 10 | 25 | 9 | 22.5 | 6 | 15 | 1 | 2.5 |

### 4.2.3. የማህበራዊ ብልሀቶች መረጃ ትንተናና ማብራሪያ

በዚህ ብልሀት ስር የሚካተቱት ብልሀቶች ከክፍል ጓደኞቹ ጋር ተባብሮ መስራት፣ በታላሚው ቋንቋ ዕውቀት ያላቸውን ሰዎች ማብራሪያ መጠየቅ፣ ያልገባቸውን ነገር መምህሮቻቸውን መጠየቅ፣ ከህብረተሰቡ ጋር ተግባቦታዊ ግንኙነት በማድረግ ባህላዊ ግንዛቤን ማዳበር የሚሉት ናቸው፡፡ የተማሪዎች የማህበራዊ ብልሀቶች አጠቃቀማቸው በጣም ከፍተኛ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ተማሪዎች ይህንን ብልሀት አዘውትረው መጠቀማቸውን ለማረጋገጥ ፅሁፍ መጠይቅ ቀርቦላቸው ነበር፡፡ በእያንዳንዱ አማራጭ ስር አራቱን የማህበራዊ ብልሀቶች ጥያቄ የመለሱ ተማሪዎች ድምር በቁጥርና ምላሽ የሰጡ ተማሪዎች ድምር ለአጠቃላይ ተማሪዎች ድምር ተካፍሎ በመቶ በማባዛት በመቶኛ ተተንትኗል፡፡ በዚሁ መሰረት 53(33.12%) የሚያህሉ ተማሪዎች ሁል ጊዜ እንደሚጠቀሙ ቢገልፁም 5(3.12%) የሚያህሉ ተማሪዎች በጭራሽ እንደማይጠቀሙ ገልፀዋሉ፡፡ ይሄ የተማሪዎች የማህበራዊ ብልሀት አጠቃቀማቸው ከፍተኛ ያለመሆኑን ያመለክታል፡፡ በተጨማሪም 38(23.8%) የሚያህሉ ተማሪዎች አብዘኛውን ጊዜ እንደሚጠቀሙ ሲገልፁ ተማሪዎች 42(26.3%)አንዳንድ ጊዜ የሚጠቀሙ ናቸው፡፡

22(13.8%) የሚያህሉ ተማሪዎች ደግሞ አልፎ አልፎ እንደሚጠቀሙ ገልፀዋሉ፡፡ ይሄ ደግሞ ሌላው ከፍተኛ ያለመሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ አብዘኞቹ ተማሪዎች የሰዋስው ትምህርት ሂደት ምቹ እንዲሆን ከክፍል ተማሪዎች ጋር መተባበርን፣ መምህሩን መጠየቅንና ማህበራዊ ግንዛቤ ማዳበርን አዘውትረው የሚጠቀሙባቸው ብልሀቶች ናቸው፡፡ ተማሪዎች እነዚህን ብልሀቶች አዘውትረው መጠቀማቸው ማህበረ ስነ ልሳናዊ ብቃት ደረጃ ላይ እንዲደርሱ ያግዟቸዋል፡፡ በአንፃሩ እነዚህን ብልሀቶች አዘውትረው መማራቸው ጥገኛ ያደርጓቸዋል፤ ጠባቂነትን ያለማምዳቸዋል፤ በራስ መተማመንን ይቀንስባቸዋል፡፡ እነዚህን ዝርዝር ብልሀቶችን የሚመለከቱ መረጃዎች ቀጥሎ ባለው ሰንጠረዥ ቀርበው ተተንትነዋል፡፡

ተተኳሪዎች አዲሱን የሰዋስው ትምህርት በክፍል ውስጥ ህብረት በመፍጠር የመስራት ብልሀት መጠቀም አለመጠቀማቸውን ለመመርመር የቀረበ ነበር፡፡ ይህን ብልሀት 16(40%) የሚሆኑ ተተኳሪዎች ሁል ጊዜ የሚጠቀሙ መሆናቸውን ሲገለፁ 8(20%) ተተኳሪዎች ባብዘኛው የሚጠቀሙ መሆናቸውን ገልፀዋሉ፡፡ በአንፃሩም 10(25%) የሚያህሉ ተተኳሪዎች ደግሞ ይህን ብልሀት አንዳንዴ የሚጠቀሙ ሲሆን 5(12.5%) ተተኳሪዎች አልፎ አልፎ የሚጠቀሙ ናቸው፡፡ ይህን ብልሀት በጭራሽ የማይጠቀሙት 1(2.5%) እንደሚደርሱ ከመረጃው ተረጋግጧል፡፡ ተማሪዎች ይህን ብልሀት አዘውትረው መጠቀማቸው እርስ በርሳቸው የተለያዩ የሰዋስው እውቀቶችን እንዲካፈሉ ይረዷቸዋል፡፡ ሆኖም ይህን ብልሀት አዘውትረው መጠቀማቸው በራስ መተማመንን ይቀንስና ጥገኛ እንዲሆኑ ሊያደርጋቸው ይችላል፡፡ ጠባቂነትንም ያስተምራል፡፡

ተማሪዎች ያልገባቸውን የሰዋስው ትምህርት በአማርኛ ቋንቋ ዕውቀት ያላቸውን ሰዎች ማብራሪያ እንዲያደርጉላቸው የመጠየቅ ብልሀት በተመለከተ 13(32.5%) የሚሆኑ ተማሪዎች አንዳንዴ የሚጠቀሙ ሲሆን 10(25%) ተማሪዎች ሁል ጊዜ ሲጠቀሙ ተመሳሳይ መጠን ያላቸው ተማሪዎች ባብዘኛው የሚጠቀሙ ናቸው፡፡ 7(17.5%) የሚሆኑ ተማሪዎች ደግሞ ይህን ብልሀት አልፎ አልፎ የሚጠቀሙ ሲሆን 1(2.5%) ተማሪ በጭራሽ የማይጠቀም ነው፡፡

በጥያቄ 29ተማሪዎች እርግጠኛ ያልሆኑበትን የሰዋስው ትምህርት መምህሮቻቸውን የመጠየቅ ብልሀት መጠቀም አለመጠቀማቸውን ተጠይቀው 13(32.5%) የሚሆኑ ተጠኚዎች ሁል ጊዜ እንደሚጠቀሙ ሲገልፁ 11(27.5%) የሚያህሉ ደግሞ ባብዘኛው እንደሚጠቀሙ ገልፀዋሉ፡፡ በአንፃሩም 10(25%) የሚሆኑ ተጠኚዎች ይህን ብልሀት አንዳንዴ እንደሚጠቀሙ ሲገልፁ 4(10%) ተጠኚዎች ደግሞ አልፎ አልፎ እንደሚጠቀሙ ገልፀዋሉ፡፡ ይህን ብልሀት በጭራሽ የማይጠቀሙት 2(5%) እንደሚደርሱም ከምላሻቸው

ለመረዳት ተችሏል፡፡ ይህ ብልሀት ተማሪዎች አዘውትረው ከሚጠቀሙባቸው ብልሀቶች አንዱ ሲሆን አዘውትረው መጠቀማቸው ግልፅ ያልሆኑ ነገሮችን እንዲረዱ እድል ይሰጧቸዋል፡፡ ጥርጣሬን አስወግደው እርግጠኛ እንዲሆኑ ያደርጓቸዋል፡፡ ይሁን እንጂ ሁል ጊዜ ይህን ብልሀት መጠቀማቸው ጠባቂ እንዲሆኑ ሊያደርጓቸው ይችላል፡፡

ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ባህልና የአኗኗር ስርዓት ግንዛቤን ከህብረተሰቡ ጋር ማበራዊ ተራክቦ በማድረግ የማዳበር ብልሀት ይጠቀሙ እንደሆን ለመመርመር የቀረበ ነበር፡፡

በዚሁ መሰረት ብልሀቱን 14(35%) ተማሪዎች ሁል ጊዜ የሚጠቀሙ ሲሆን 9(22.5%) ተማሪዎች ደግሞ አንዳንዴ የሚጠቀሙ ናቸው፡፡ መረጃው እንደሚያመለክተው ይህን ብልሀት 10(25%) የሚሆኑት ተማሪዎች ባብዛኛው የሚጠቀሙ ሲሆን 6(15%) ተማሪዎች ደግሞ አልፎ አልፎ የሚጠቀሙ ናቸው፡፡ 1(2.5%) የሚሆኑ ተማሪዎች ደግሞ ይህን ብልሀት በጭራሽ የማይጠቀሙ ናቸው፡፡ ይህ ብልሀት ተማሪዎች አዘውትረው ከሚጠቀሙባቸው ብልሀቶች አንዱ ሲሆን አዘውትረው መጠቀማቸው ማህበረ ስነ ልሳናዊ ብቃት ደረጃ ላይ እንዲደርሱ ያደርጓቸዋል፡፡

ከላይ በ4.2.3 ስር እንደተገለፀው 22(13.8%) ተጠኚዎች አልፎ አልፎ የሚጠቀሙና 5(3.12%) ተጠኚዎች በጭራሽ የማይጠቀሙ ቢሆንም በርካታ ቁጥር ያላቸው 53(33.12%) ተጠኚዎች ሁል ጊዜ መጠቀማቸው የተማሪዎች ማህበራዊ ብልሀቶች አጠቃቀማቸው የተሻለ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

ከላይ በ4.2 ስር እንደተመለከተው በርካታ ቁጥር ያላቸው 180(32.14%) የሚሆኑ ተጠኚዎች በርካታ ኢቀጥተኛ ሰዋስው የመማር ብልሀቶቹን አዘውትረው የሚጠቀሙ መሆናቸውን የተሰበሰበው መረጃ ትንተና ውጤት ያመለክታል፡፡ ይህ የተማሪዎች ኢቀጥተኛ ሰዋስው የመማር ብልሀቶች አጠቃቀማቸው የተሻለ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

ባጠቃላይ የተማሪዎች ኢቀጥተኛ ሰዋስው የመማር ብልሀቶች(ልዕለ አእምሮታዊ፣ ስሜታዊና ማህበራዊ) አጠቀም ከቀጥተኛ ሰዋስው የመማር ብልሀቶች(ከማስታወስ፣ ከአእምሮታዊና ከማካካሻ) ብልሀቶች አጠቃቀም የተሻለ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ተጠኚዎች ማህበራዊ ብልሀቶችን ከሌሎች ብልሀቶች ይልቅ በይበልጥ የሚተገብሩት ሲሆን፤ የማካካሻ ብልሀትን ደግሞ ከሌሎች ብልሀቶች ሁሉ ባነሰ ደረጃ ይተገብሩታል፡፡ በርካታ ተማሪዎች በቀጥታ ለሰዋስው ትምህርት እገዛ ከሚያደርጉ ብልሀቶች ይልቅ ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ ለሰዋስው ዕውቀት መዳበር እገዛ የሚያደርጉ በርካታ ብልሀቶችን አዘውትረው

እንደሚጠቀሙ የመረጃ ውጤት ያመለክታል፡፡ የዚህ ጥናት ውጤትም Yalcin (2005) ጥናት ጋር የሚጣጣም ሲሆን፤ ከYemeserach (2015) ጥናት ጋር የሚቃረን ሆኖ ተገኝቷል፡፡

## ቀጥተኛና ኢ-ቀጥተኛ የመማር ብልሀቶች አንፃር

ቀጥተኛ የመማር ብልሀቶች አጠቃቀም ዝቅተኛ ሲሆን ኢቀጥተኛ ብልሀቶች አጠቃቀም የተሻለ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ተማሪዎች ከቀጥተኛ መማር ብልሀቶች ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ከዚህ በፊት ከሚያውቀት ነገር ጋር ማያያዝን፣ በአእምሯቸው ውስጥ ምስል በመፍጠር ማስታወስን፣ የተለያዩ አካላዊ እንቅስቃሴዎች መጠቀምን፣ ህጎችን ደጋግሞ መፃፍና መናገርን፣ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር መማርን፣ ጠቃሚ ሀሳቦችን አጠር አድርጎ ማስታውሻ መያዝን፣ ከአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ጋር ማነፃፀርን፣ ወደ አፍ መፍቻ ቋንቋ መተርጎምንና በፅሁፍ ውስጥ ጠቃሚ የሆኑ ሰዋስዋዊ መረጃዎችን የተለያዩ ምልክቶችን በማድረግ የመጠቀም ብልሀቶችን፤ ከኢቀጥተኛ መማር ብልሀቶች ውስጥ ደግሞ ዓላማ ማዘጋጀትን፣ ትኩረት መስጠትን፣ ማቀድን፣ጭንቀት መቀነስን፣ ራስን ማበረታታትን፣ አዎንታዊ ገለፃ መስጠትን፣ ሀላፊነት መውሰድን፣ ከክፍል ተማሪዎች ጋር መተባበርን፣ መምህሩን መጠየቅንና ማህበራዊ ግንዛቤ ማዳበርን አዘውትረው እንደሚጠቀሙ ለመረዳት ተችሏል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

# ማጠቃለያና የመፍትሄ ሀሳቦች

## 5.1 ማጠቃለያ

በየምዕራፉ እንደተጠቀሰው የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በደቡብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በወላይታ ዞን በባይራ ኮይሻ ወረዳ ስር የሚገኘዉ በቅሎ ሰኞ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስው የመማር ብልሀቶችን መፈተሽ ነው። በዚህ ዋና ዓላማ ላይ በመመርኮዝ ጥናቱ የሚከተሉትን ዝርዝር ዓላማዎችን ያካተተ ነው።

1. በተመረጠዉ በቅሎ ሰኞ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስው ለመማር አዘውትረው የሚጠቀሙባቸው ቀጥተኛ ሰዋስው የመማር ብልሀቶች የትኞቹ እንደሆኑ መፈተሽ።

2. በተመረጠዉ በቅሎ ሰኞ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስው ለመማር አዘውትረው የሚገለገሉባቸው ኢቀጥተኛ ሰዋስው የመማር ብልሀቶች የትኞቹ እንደሆኑ መለየት።

እነዚህን ዓላማዎችን ለማሳካት በሰባት ዘጠነኛ ክፍል ካሉት ከ440 ተማሪዎች መካከል 40 ተማሪዎች በዓላማ ተኮር ናሙና ዘዴ ተመርጣዋል ። የጥናቱን ዓላማ ለማሳካት ለተማሪዎች 17 ቀጥተኛ የመማር ብልሀቶችን የሚመለከቱና 13 ኢቀጥተኛ የመማር ብልሀቶችን የሚመለከቱ ባጠቃላይ 30 ዝግ የፅሁፍ መጠይቆች የቀረቡ ሲሆን ለያንዳንዱ ጥያቄ ባለአምስት ነጥብ የLikert Scale መመዘኛዎችን በመጠቀም እንዲመልሱ በማድረግ መረጃ ተሰብስቧል። የተሰበሰቡ መረጃዎችንም በሁለት ዋና ዋና ብልሀቶች በመክፈል ቀጥተኛ የመማር ብልሀቶች (የማስታወስ፣ አእምሮታዊና የማካካሻ) እና ኢቀጥተኛ ብልሀቶች (ልዕለ አእምሮታዊ፤ ስሜታዊና ማህበራዊ) መሰረት አዘውትረው የሚጠቀሙባቸውንም በመለየት በገላጭ ዘዴ ከተተነተኑ በኋላ የተገኙትን ውጤቶች መሰረት በማድረግ ማጠቃለያዎችና የመፍትሄ ሀሰቦች ተሰጥተዋል።

የጥናቱ ውጤት እንደሚያመለክተው ተማሪዎች ስድስቱንም ሰዋስው የመማር ብልሀቶችን ከሞላ ጎደል የሚጠቀሙ ሲሆን ማህበራዊ ብልሀቶችን በይበልጥ ይጠቀሙብታል፤ በአንፃሩ ግን ከሁሉም ባነሰ መልኩ የሚተገብሩት የማካካሻ ብልሀትን ነው። በተጨማሪም ኢቀጥተኛ ሰዋስው የመማር ብልሀቶችን ከቀጥተኛ ሰዋስው ከመማር ብልሀቶች በተሻለ ሁኔታ እንደሚጠቀሙ የመረጃ ውጤት ያሳያል።

ቀጥተኛ የመማር ብልሀቶችን በተመለከተ አብዘኞቹ ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋ ሰዋስው የመማር ብልሀቶች አጠቃቀም ዝቅተኛ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ አብዘኞቹ ተጠኚዎች አንዳንዴ እንደሚጠቀሙባቸው የጥናቱ ውጤት ያሳያል፡፡ ይህም ብዙ ተማሪዎች ለበርካታ ቀጥተኛ ብልሀቶች አጠቃቀም ዕውቀትና ልምድ የሌላቸው መሆኑን ያመለክታል፡፡

ከቀጥተኛ ብልሀቶች ውስጥ ተማሪዎች የሰዋስው ትምህርት ከዚህ በፊት ከሚያውቀት ነገር ጋር ማያያዛቸውን፣ በአእምሯቸው ውስጥ ምስል በመፍጠር ማስታወስን፣ የተለያዩ አካላዊ እንቅስቃሴዎች መጠቀምን ፣ መደጋገምን (ህጎችን በአእምሮ ውስጥ ማመላለስና መናገርን)፣ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር መማርን፣ ጠቃሚ ሀሳቦችን አጠር አድርጎ ማስታውሻ መያዝን፣ ከአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ጋር ማነፃፀርን፣ ወደ አፍ መፍቻ ቋንቋ መተርጐምንና በፅሁፍ ውስጥ ጠቃሚ የሆኑ ሰዋስዋዊ መረጃዎችን የተለያዩ ምልክቶችን በማድረግ የመጠቀም ብልሀቶችን የሚያዘውትሩ ናቸው፡፡ ተማሪዎች እነዚህን ብልሀቶች አዘውትረው መጠቀማቸው ሰዋስው ትምህርትን ቶሎ እንዲያስታውሱና የጠለቀ እውቀት እንዲኖራቸው ያግዟቸዋል፡፡ በአእምሯቸው በቀላሉ እንዲቀርፁና በአጭሩ እንዲረዱ እንዲሁም እንዳይረሱ ይረዷቸዋል፡፡ ባጠቃላይ ተማሪዎች እነዚህን ብልሀቶች ማዘውተራቸው አይረሴ እንዲሆኑና የመገንዘብ ሁኔታ እንዲያዳብሩ ይረዷቸዋል፡፡ ሆኖም ሁል ጊዜ እነዚህ ብልሀቶች አጋዥ ላይሆኑ ይችላሉ፡፡ ሁል ጊዜ መደጋገም አሰልቺ ሊሆን ይችላል፡፡ ተማሪዎች ሁል ጊዜ ከአጠቃላይ ወደዝርዝር ብቻ መማርም እንዲሁ አሰልቺ ይሆናል፡፡ አንዳንዴ ጊዜ የሚወስድ ቢሆንም ከዝርዝር ወደአጠቃላይ በሆነ መንገድ ቢማሩ የተሻለ ይሆናል፡፡ አዘውትረው በመተርጐም ብቻ መማር ደግሞ ወደ ስህተት ሊያመራ ይችላል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ውስን ተማሪዎች እነዚህንና ሌሎች ቀጥተኛ የመማር ብልሀቶችን በጭራሽ የማይጠቀሙ አሉ፡፡ ይህ ደግሞ ተማሪዎች በሰዋስው ትምህርታቸው ውጤታማ እንዳይሆኑ ያደርጋቸዋል፡፡ ስለዚህ አብዘኞቹ ተማሪዎች አዘውትረው የሚጠቀሙባቸው ብልሀቶች እነዚህ ስለሆኑ መምህራን እነዚህን ብልሀቶች ተከትለው የሚመጡ ችግሮች እንዳይፈጠሩ ነቅተው መጠበቅ አለባቸው፡፡

ባጠቃላይ ተማሪዎች የታላሚውን ቋንቋ ተግባራት እየሰሩና በትምህርቱ ሂደት እየተሳተፉ እንዲማሩ በቀጥታ እገዛ ከሚያደርጉ ብልሀቶች ውስጥ በርካታ ቁጥር ያላቸው ተማሪዎች የማስታወስ ብልሀቶችንና የማካካሻ ብልሀቶችን አንዳንድ ጊዜ፤ አእምሮታዊ ብልሀቶችን ደግሞ ሁል ጊዜ የሚጠቀሙ መሆናቸውን የጥናቱ ውጤት ያመለክታል፡፡

ኢቀጥተኛ ብልሀቶች ተማሪዎች በትምህርቱ ሂደት በቀጥታ እየተሳተፉ ሳይሆን ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ ለሰዋስው ዕውቀት መዳበር እገዛ የሚያደርጉ ናቸው። እነዚህ ብልሀቶች ተማሪዎች የትምህርታቸውን ሂደት ለማመቻቸት የሚገለገሉባቸው ብልሀቶች ናቸው። በመሆኑም ኢቀጥተኛ የመማር ብልሀቶችን በተመለከተ የተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስው የመማር ብልሀቶች አጠቃቀማቸው ከፍተኛ መሆኑን የጥናቱ ውጤት ያመለክታል።

ከኢቀጥተኛ ብልሀቶች ውስጥ ተማሪዎች ዓላማ ማዘጋጀትን፣ ትኩረት መስጠትን፣ ማቀድን፣ ጭንቀት መቀነስን፣ ራስን ማበረታታትን፣ አዎንታዊ ገለፃ መስጠትን፣ ሀላፊነት መውሰድን፣ ከክፍል ተማሪዎች ጋር መተባበርን፣ መምህሩን መጠየቅንና ባህላዊ ግንዛቤ ማዳበርን አዘውትረው የሚጠቀሙባቸው ብልሀቶች ናቸው። እነዚህ ብልሀቶች ተማሪዎች የሰዋስው ትምህርት ለምን እንደሚማሩ፣ ከየት ተነስተው ወዴት እንደሚጓዙ፣ የራሳቸውን ጠንካራና ደካማ ጎን እንዲለዩ ያስችሏቸዋል። እንዲሁም ተማሪዎች ማህበረ ስነ ልሳናዊ ብቃት እንዲኖራቸው ያግዟቸዋል። በሌላ በኩል እነዚህ ብልሀቶች ሁል ጊዜ አጋዥ ላይሆኑ ይችላሉ። ተማሪዎች ሁል ጊዜ የሌላ ወገን እገዛ መሻት በራሳቸው እንዳይተማመኑና ጥገኛ እንዲሆኑ ያደርጓቸዋል። በመሆኑም አብዛኞቹ ተማሪዎች አዘውትረው የሚጠቀሙባቸው ብልሀቶች እነዚህ ስለሆኑ መምህራን እነዚህን ብልሀቶች ተከትለው የሚመጡ ችግሮችን መከላከል አለባቸው።

ከላይ ካጠቃላይ መረጃ ትንተና ውጤት እንደምንረዳው ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ሰዋስው ትምህርት ውጤታማነት ቀጥተኛ የመማር ብልሀቶቹን አብዛኞቹ ተማሪዎች አንዳንዴ የሚጠቀሙ ሲሆን ኢቀጥተኛ የመማር ብልሀቶቹን ግን ሁል ጊዜ የሚጠቀሙ ቢሆንም በርካታ ተማሪዎች አንዳንዴና አልፎ አልፎ የሚጠቀሙ እንዲሁም በጭራሽ የማይጠቀሙ መኖራቸውን የጥናቱ ውጤት ያመለክታል። ባጠቃላይ ይህ የተማሪዎች ሰዋስው የመማር ብልሀት አጠቃቀማቸው ዝቅተኛ መሆኑ ብዙ ተማሪዎች ለበርካታ ብልሀቶች አጠቃቀም ግንዛቤ የሌላቸው መሆኑን ያመለክታል።

## 5.2. የመፍትሄ ሀሳቦች

አጥኚው የጥናት ውጤቶችን መሰረት በማድረግ የሚከተሉትን የመፍትሄ ሀሳቦችን አስቀምጧል።

- ❖ መምህራን የተማሪዎቹን የመማር ብልሀት ምርጫ ተረድተው መረጃ በመስጠት ተማሪዎች የተለያዩ ሰዋስው የመማር ብልሀቶች ዕውቀትና ልምድ እንዲያዳብሩ ግንዛቤ ቢያስጨብጡ፡፡

- ❖ ተማሪዎች ቀጥተኛ ሰዋስው የመማር ብልሀቶችን የመጠቀም ፍላጎታቸው ዝቅተኛ ነው ፡፡ በተለይ የማስታወስና የማካካሻ፤ በመሆኑም የቋንቋ መምህራን ተማሪዎች እነዚህን ብልሀቶች በክፍል ውስጥ እንዲጠቀሙ ሁኔታዎችን ቢያመቻቹ፡፡

- ❖ አንዳንድ ተማሪዎች ለመምህሩ ጥያቄ ማቅረብን፣እንቅስቃሴ መጠቀምን፣ ማድመቅን (ማክበብን)ናብልሀቶችን በጭራሽ የማይጠቀሙ ናቸው፡፡ ስለዚህ መምህራን ለሰዋስው ትምህርት ውጤታማነት እነዚህን ብልሀቶች አልፎ አልፎ ቢሆንም እንዲጠቀሙ ቢያበረታቱ፡፡

- ❖ አብዘኞቹ ተማሪዎች የሰዋስው ትምህርትን ከዚህ በፊት ከሚያውቀት ነገር ጋር ማያያዝን፣ የተለያዩ አካላዊ እንቅስቃሴዎች መጠቀምን ፣ ህጎችን ደጋግሞ በአእምሮ ውስጥ ማሰላሰልንና መናገርን፣ ወደ አፍ መፍቻ ቋንቋ መተርጎምን፣ ከስሩ ማስመርን፣ ማቀድን፣ ጭንቀት መቀነስን፣ መተባበርንና መምህሩን መጠየቅን አዘውትረው የሚጠቀሙባቸው ብልሀቶች ስለሆኑ፤ መምህራኑ እነዚህን ብልሀቶች ተከትለው የሚመጡ ችግሮች እንዳይፈጠሩ ለተማሪዎች ቢያስገነዝቡ፡፡

- ❖ መርሃ ትምህርት አዘጋጆች የተማሪዎችን የተለያዩ ሰዋስው የመማር ብልሀቶችን ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ከአንዳንድ ብልሀቶች የሚመነጩ ችግሮች ማስተማሪያ መሳሪያዎች ላይ የጎላ ችግር እንዳይፈጥሩ አድርገው መርሀ ትምህርት ቢቀርፁ፡፡

እነዚህን ከላይ የተዘረዘሩ የመፍትሄ ሃሳቦችን ተማሪዎች፣ መምህራን፣ መርሀ ትምህርት ቀራጮች፣ መማሪያና ማስተማሪያ መፅሀፍ አዘጋጆች የሚመለከታቸውን ሃሳቦች ተግባራዊ የሚያደርጉ ከሆነ ተማሪዎቹ ሰዋስው የመማር ብልሀቶች አጠቃቀም ዕውቀትና ልምድ በማዳበር በሰዋስው ትምህርታቸው ውጤታማ ይሆናሉ የሚል ግምት አለኝ፡፡

## ዋቢ ፅሁፎች

ሠፋ መካ። (1995)። “የጉመር ጉራግኛ አፊ- ፊት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ሲናገሩ የሚጠቀሙባቸው ተግባቦታዊ ብልሀቶች (Communication strategies) ትንተና”። በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት በቋንቋዎች ጥናት ተቋም አማርኛ ማስተማር (TEAM) ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ ፣አዲስ አበባ። (ያልታተመ)።

ሰለሞን ዮሀንስ። (1991)። “የተማሪዎች የአማርኛ ድርሰት የመፃፍ ስትራቴጅና የመምህራን የማስተማር ዘዴ ተጣጥሞ (በአንድ መምህር ላይ የተካሄደ ጥናት)”። በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት በቋንቋዎች ጥናት ተቋም አማርኛ ማስተማር (TEAM) ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ ፣አዲስ አበባ።(ያልታተመ)።

በላይነህ ሀይሌ። (2003) ዓ.ም ። የሰዋሰወ ትምህርት አተገባበር ፊተሻ (በሀድያ ዞን በተመረጡ ሶስት የ8ኛ ክፍል ትምህርት ቤቶች ናሙናነት። በአድስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት ለአማርኛ ማስተማር (TeAm) ኤም.ኤ ድግሪ በከፍል ማሟያነት የቀረበ ጥናት ፡አዲስ አበበ ። (ያልታተመ)።

በላይነሽ ደነቀ። (2002) ። “በኦሮሚያ ክልል በኢሉባቦር ዞን በመቱ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አፋቸውን በኦሮምኛ ቋንቋ የፈቱ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቃላትን ለመማር የሚገለገሉባቸውን የመማር ብልሀቶች ፍተሻ”። በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት በቋንቋዎች ጥናት ተቋም አማርኛ ማስተማር (TEAM) ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ ፣አዲስ አበባ። (ያልታተመ)።

ተክላይ ትእዛዙ። (2000)። “በትግርኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የስምንተኛ እና የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ንባብ ጊዜ የንባብ ብልሀቶች አጠቃቀምና የመምህራን ግንዛቤ ተጣጥሞ ፍተሻ በአክሱም ከተማ አንደኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መነሻነት”። በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቋንቋዎች ጥናት ተቋም ድህረ ምረቃ መርሀ ግብር ለአማርኛ ማስተማር(TEAM) ኤም. ኤ ዲግሪ በከፊል ማሟያነት የተሰናዳ ጥናት፣ አዲስ አበባ። (ያልታተመ)።

ንጋቱ አሰፋ። (2000)። “በሲዳምኛ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች የአማርኛን ቃላት ሲማሩ የሚጠቀሙባቸው ቃላትን የመማር ብልሀት ምርመራ”። በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቋንቋዎች ጥናት ተቋም ድህረ ምረቃ መርሀ ግብር ለአማርኛ ማስተማር (TEAM) ኤም.ኤ ዲግሪ በከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት፣ አዲስ አበባ። (ያልታተመ)።

ከበደ አየለ። (1999)። “የሰዋሰው ትምህርትን በክፍል ውስጥ የማስተማሪያ ብልሀቶች አጠቃቀምና አተገባበር ፍተሻ በኦሮሚያ ክልል በአርሲ ዞን በሚገኙ አራት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በዘጠነኛ ክፍል ናሙናነት። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለድህረ ምረቃ የቀረበ ጥናት፣ ለአማርኛ ማስተማር (TeAm) ኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣ አዲስ አበባ። (ያልታተመ)።

ያለው እንዳወቀ። (2006)። ***የምርምር መሰረታዊ መርሆዎችና አተገባበር።*** ንግድ ማተሚያ ድርጅት። ባህረ ዳር።

ይርጋ አለም። (1997)። “አፋቸውን በከፊኛ የፈቱ ጥሩ የቋንቋ ተማሪዎች አማርኛ ሲማሩ የሚገለገሉባቸው ቋንቋ የመማር ብልሀቶች እና የመምህራን ግንዛቤ አሰሳ በደቡብ ክልል በከፋ ዞን በቦንጋ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና ጊንቦ መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ናሙናነት። በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት በቋንቋዎች ጥናት ተቋም አማርኛ ማስተማር (TEAM) ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፣ አዲስ አበባ። (ያልታተመ)።

Anderson, N. (2005). “L2 Learning Strategies”. In E. Hinkel (Ed.), *Handbook of Research in Second Language Teaching and Learning.* Mahwah, NJ: Lawrence Erlbaum Associates.

Bialystok, E. (1978). A Theoretical Model of Second Language Learning. *Language Learning.* 28, 69-83.

Brown, HD. (1994). *Principles of Language Learning and Teaching* (3rd ed.) Englewood Cliffs, NJ: Prentice Hall Regents.

Canale, M., & Swain, M. (1980). "Theoretical Bases of Communicative Approaches to Second Language Teaching and Testing". *Applied Linguistics,* 1(1), 1-47.

Chamot, A. U. (1987). "The Learning Strategies of ESL Students." in Wenden, A. and Rubin, J. (1987) *Learner Strategies in Language Learning.* Cambridge: Cambridge University press.

Chamot, A. U. (2004). "Issues in Language Learning Strategy Research and Teaching". *Electronic Journal of foreign Language Teaching,* 1(1):14-26.

Cohen, A. (1996). "Second Language Learning and Use Strategies: Clarifying the Issues". *Center for Advanced Research on Language Acquisition,*1-26

Cohen, A.D. (1998). *Strategies for Learning and Using a Second Language.* Essex, U.K.: Longman.

Ellis, R. (1994). *The Study of Second Language Acquisition*. New York: Oxford University Press.

Green, J. M., and Oxford, R. L. (1995). "A Closer Look at Learning Strategies, L2 Proficiency, and Gender".*TESOL Quarterly,* 29(2), 261-297.

Griffiths, C. & Judy, M. Parr. (2001). "Language-Learning Strategies": *Theory and Perception*, *ELT Journal,* 55/3, 247-254.

Griffiths, C. (2003). Patterns of Language Learning Strategy Use. *System;* 31: 367-383.

Halliday, M. (1994). *An Introduction to Functional Grammar* (2nd ed). New York: Oxford University Press Inc.

Haregewain Abate. (2008). "The Effect of Communicative Grammar on the Grammatical Accuracy of Students Academic Writing: An Integrated Approach to TEFL". Unpublished PhD Dissertation, Addis Ababa: Addis Ababa University.

Hutimen, I. (1996). "Learning to Learn an Overview LANGUAGE TEACHING": An International Abstracting Journal for Language Teacher Educators, and Researchers. Cambridge: Cambridge University press. Vol.29. No.5:2-4 pp 86-98.

Littlemore, J. (2001). "An Empirical Study of The Relationship Between Cognitive Style and The Use of Communication Strategies". *Applied Linguistics*. 22/2: 241-265

O'Malley, J. M., Chamot, A. U., Stewner-Manzanares, G., Russo, R. P., and Kupper, L. (1985) "Learning Strategy Applications with Students of English as a second Language". *TESOL Quarterly,*19(3), 557-584.

O'Malley, J. M. and Chamot, A. U. (1990). *Learning Strategies in Second Language Acquisition*. Cambridge: Cambridge University Press.

Oxford, R. L. (1989). "Use of Language Learning Ltrategies": a Synthesis of Studies with Implications for Strategy Training, *System,* 17/2, 235-247

Oxford, R. L. (1990). *Language Learning Strategies*: *What Every Teacher Should Know*. New York: Heinle and Heinle publishers.

Oxford, R. L. (1994). "Gender Differences in Strategies and Styles for L2 Learning: What is the Significance? Should we Pay Attention"? In J.E.

Alatis (ed.), *Theory and Practice of Strategies in Second Language Acquisition,* 541-557. Washington, DC: Georgetown University Press.

Oxford. R. L., Rang Lee, K. and Park, G. (2007). “L2 Grammar Strategies: the Second Cinderella and Beyond”. In Cohen, A. D. and Macaro, E. (eds). 2007. 117-139.

Richard, J. C. (1994). *Reflective Teaching in Second Language Classroom*. New York: Cambridge University Press.

Rubin, J. (1975). What the ``good language learner`` can teach us. *TESOL Quarterly,* 9(1), 41-51.

Rubin, J. (1981). Study of Cognitive Processes in Second Language Learning. *Applied Linguistics*, 11, 117-131.

Rubin, J. (1987). Learner Strategies: Theoretical Assumptions, Research History and Typology. In A.Wenden and J. Rubin (Eds.), *Lernear Strategies in Language Learning* (pp.15-30). Englewood, NJ: Prentice/Hall International.

Stern, H. (1983). *Fundamental Concepts of Language Teaching.* Oxford: Oxford University Press.

Temesgen Mereba. (2013). “Expioring English Grammar Skills Learning Strategies Used by University EFL Students, Jimma University in Focus. Addis Abeba University of Graduate Studies”. PHD Desertation. (Unpublished)

Wallace, G. (1992). *Reading*. Oxford; Oxford University press.

Wenden, A. (1987). ‘Conceptual Back ground and utility’, in Wenden, A and Rubin, J. (Eds) *Learner Strategies Language Learning*. New York; Prentice Hall.

Wenden, A. (1991). *Learner Strategies for Learner Autonomy*. New York: Prentice Hall.

Wenden, A. and Rubin, J. (1987). *Learner Strategies in Language Learning*. Englewood Cliffs, New York; Prentice Hall.

Wharton, G. (2000). Language Learning Strategy Use of Bilingual Foreign Language Learners in Singapore. *Language Learning.* vol. 50. no. 2.

Williams, M. and Burden R. L. (1997). *Psychology for Language Teachers*: *A Social Constractive Approach*. Cambriidge: CUP.

Yalcin, F. (2005). "An Analysis of the Relationship between the Use of Grammar Learning Strategies and Student Achievement at English Preparatory Classes". *Journal of Language and Linguistic Studies,* 1(2), 155-169.

Yemeserach Bayou. (2015). Grammer Learning Strategies Use of Grade11 Students at Medhanelem Preparatory School, Gender in Focus. Addis Abeba University of Graduate Studies. MA Thesis. (Unpublished)

# አባሪ 1

## በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ ስነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

## የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

### በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የሚሞላ የፅሁፍ መጠይቅ

*ውድ ተማሪዎች በመጀመሪያ መጠይቁን ለመሙላት ፈቃደኛ በመሆናችሁ አመሰግናለሁ:: የዚህ መጠይቅ ዓላማ በትምህርት ቤታችሁ ውስጥ የአማርኛ ቋንቋ ሰዋሰው የመማር ብልሀት ምን እንደሚመስል መረጃ መሰብሰብ ነው:: በመጠይቁ ላይ ከመመሪያ ውጭ ሌላ ነገር መጻፍ አያስፈልግም::*

*መመሪያ* 1 *አጠቃላይ መረጃ፡-* *ፆታ*------

*ዕድሜ*-----

*መመሪያ* 2 *ከዚህ ቀጥሎ በሰንጠረዥ ውስጥ የአማርኛ ቋንቋ ሰዋሰው የመማር ብልሀት የሚመለከቱ ጥያቄዎች ቀርበዋል:: በመሆኑም እያንዳንዱን ጥያቄ በደንብ ካነበብክ/ሽ በኋላ የተጠቀሰውን ብልሀት አጠቃቀምህን/ሽን አስመልክቶ ከቀረቡት ሁል ጊዜ፣ አብዘኛውን ጊዜ፣ አንዳንድ ጊዜ፣ አልፎ አልፎ እና በጭራሽ ከሚሉት አማራጭ መልሶች መካከል አንዱን ብቻ መርጠህ/ሽ ከጥያቄው ፊት ለፊት ወይም ከአማራጮቹ ስር በሚገኘው ሳጥን ውስጥ የ "X" ምልክት በማድረግ መልስ/ሽ፡፡ ለእያንዳንዱ ጥያቄ ትክክለኛው መልስ እያንዳንዳችሁ በታማኝነት የምትመልሱት መልስ ነው፡፡ በሰንጠረዥ ውስጥ ያሉት ምርጫዎች የሚወክሉት፡-*

5 = *ሁል ጊዜ*

4 = *አብዘኛውን ጊዜ*

3 = *አንዳንድ ጊዜ*

2 = *አልፎ አልፎ*

1 = *በጭራሽ ናቸው*

| ተ/ቁ | ጥያቄዎች | አማራጮች | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ቀጥተኛ ብልሀቶችን የሚመለከቱ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| | **ክፍል አንድ፡- የማስታወስ ብልሀቶች** | | | | | |
| 1 | አዲሱን የሰዋስው ትምህርት በቀላሉ ለማስታወስ ተመሳሳይ ነገሮችን በአንድ ወገን በመመደብ እማራለሁ፡፡<br>1.1 በምዕላድ ዓይነታቸው | | | | | |
| | 1.2 በቃል ክፍላቸው | | | | | |
| | 1.3 በሀረግ ክፍላቸው | | | | | |
| | 1.4 በዐረፍተ ነገር ዓይነታቸው | | | | | |
| 2 | የሰዋስው ትምህርት ከዚህ በፊት ከማውቀው ነገር ጋር አያይዤ አስታውሳለሁ፡፡<br>2.1 የሰዋስው ትምህርት በመፅሀፉ ውስጥ ከሚገኝበት ገፅ አንፃር | | | | | |
| | 2.2 መምህሩ ክፍል ውስጥ ሲያስተምር ከነበረበት ሁኔታ አንፃር | | | | | |
| 3 | የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስው ትምህርት በአእምሮዬ ውስጥ ምስል በመፍጠር ለማስታወስ እሞክራለሁ፡፡<br>3.1 ከተጨባጭ ነገሮች ጋር | | | | | |
| | 3.2 ከድምፆችጋር | | | | | |
| 4 | የተማርኳቸውን የሰዋስው ትምህርት በተለያየ ጊዜያት ውስጥ እከልሳቸዋለሁ፡፡ | | | | | |
| 5 | የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስው ትምህርት የተለያዩ አካላዊ እንቅስቃሴዎችን በመጠቀም እማራለሁ፡፡ ለምሳሌ፡- በመቀመጥ፣ በመቆም፣ በመራመድ ወዘተ. | | | | | |
| | **ክፍል ሁለት፡- የአእምሮታዊ ብልሀቶች** | | | | | |
| 6 | የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስው ትምህርት ህጎችን ደጋግሜ በመፃፍ እለማመዳለሁ፡፡ | | | | | |
| 7 | አዲሱን የሰዋስው ትምህርት ህጎችን በአእምሮዬ ውስጥ ደጋግሜ በማመላለስ አጠናለሁ፡፡ | | | | | |
| 8 | የተማርኳቸውን የሰዋስው ትምህርት ማጣቀሻ መፃህፍትን በመጠቀም | | | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | አጠናለሁ፡፡ ለምሳሌ፡- ሰዋስው መፃህፍት፣ መዝገበ ቃላት ወዘተ. | | | | | |
| 9 | የአዲሱን ቋንቋ ሰዋስው ዕውቀት ለማዳበር የተለያዩ ሚዲያዎችን (ሬድዮ፣ ቴሌቭዥን፣ ወዘተ.) እከታተላለሁ፡፡ | | | | | |
| 10 | የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስው ትምህርት ተግባራት ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር በሆነ መንገድ እማራለሁ፡፡ | | | | | |
| 11 | የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስው ትምህርት ተግባራት ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ በሆነ መንገድ እማራለሁ፡፡ | | | | | |
| 12 | ጠቃሚ ናቸው ብዬ የምገምታቸውን የሰዋስው ፅንሰ ሀሳቦችንና አጠቃቀሞችን አጠር አድርጌ ማስታውሻ እይዛለሁ፡፡ | | | | | |
| 13 | የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስው ከአፍ መፍቻ ቋንቋ ሰዋስው አጠቃቀም ጋር እያነፃፀርኩ እጠቀማለሁ፡፡ | | | | | |
| 14 | የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስው አጠቃቀም ወደ አፍ መፍቻ ቋንቋ ሰዋስው አጠቃቀም በመተርጐም እማራለሁ፡፡ ለምሳሌ፡- ዲቻ ወደ ትምህርት ቤት ሄደ፡፡ የሚለውን ዲቺ ትምህርቴ ከታ ቢስ፡፡ ብሎ መተርጎም | | | | | |
| 15 | በፅሁፍ ውስጥ ጠቃሚ የሆኑ ሰዋስዋዊ መረጃዎችን የተለያዩ ምልክቶችን በማድረግ አጠናለሁ፡፡<br>15.1 የተለያየ ቀለም ባለው ብዕር በመፃፍ | | | | | |
| | 15.2 ከስሩ በማስመር | | | | | |
| | 15.3 በመክበብ | | | | | |
| | **ክፍል ሶስት፡- የማካካሻ ብልሀቶች** | | | | | |
| 16 | አዲሱን የሰዋስው ትምህርት የተለያዩ አካላዊ ምልክቶችን በመጠቀም እማራለሁ፡፡<br>16.1በአንገት እንቅስቃሴ | | | | | |
| | 16.2 በእጅ እንቅስቃሴ | | | | | |
| 17 | እንግዳ የሆኑ ሰዋስዋዊ ተግባራት ሲያጋጥሙኝ ከአውዱ በመገመት እማራለሁ፡፡ | | | | | |
| | **ኢቀጥተኛ ብልሀቶችን የሚመለከቱ** | | | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | **ክፍል አራት፡- ልዕለ አእምሮታዊ ብልሀቶች** | | | | | |
| 18 | አዲሱን የሰዋስው ትምህርት የምማርበትን የራሴን ዓላማ አዘጋጃለሁ፡፡ | | | | | |
| 19 | የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስው ትምህርት ቅድሚያ ለሚፈልጉ ተግባራት ቅድሚያ በመስጠት እማራለሁ፡፡ | | | | | |
| 20 | የሰዋስውን ትምህርት ለመማር በትምህርቱ ሂደት የማከናውናቸውን ተግባራት በማቀድ የጥናትና የልምምድ ፕሮግራም አዘጋጅቼ ሁኔታዎችን አመቻቻለሁ፡፡ | | | | | |
| 21 | በሰዋስው ትምህርት ካለፈው የበለጠ ለውጥ ማምጣት አለማምጣቴን ራሴን<br>እፈትናለሁ፡፡ | | | | | |
| | **ክፍል አምስት፡- የስሜታዊ ብልሀቶች** | | | | | |
| 22 | ከአዲሱ የሰዋስው ትምህርት በፊት አካልና አእምሮዬን በማዝናናት የድካምና የድብርት ስሜት እቀንሳለሁ፡፡ | | | | | |
| 23 | አዲሱን የሰዋስው ትምህርት ለመማር ሰውነቴ የሚፈልገውን ነገር በማድረግ ራሴን አበረታታለሁ፡፡ | | | | | |
| 24 | በሰዋስው ትምህርት ሂደት ያደረብኝን ውስጣዊ ስሜት ለሌሎች አካፍላለሁ፡፡<br>24.1 ለክፍል ጓደኞቼ | | | | | |
| | 24.2 ለመምህሮቼ | | | | | |
| 25 | የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስው ትምህርት ተግባራትን ለማከናወን የምችል ጎበዝ ተማሪ አድርጌ ራሴን እቆጥራለሁ | | | | | |
| 26 | የሰዋስውን ትምህርት ስማር ስህተት ብፈጥርም መሳሳት ያለ በመሆኑ ያለፍርሃት በንቃት እሳተፋለሁ፡፡ | | | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | **ክፍል ስድስት፦ የማህበራዊ ብልሀቶች** | | | | | |
| 27 | አዲሱን የሰዋስው ትምህርት ከክፍል ጓደኞቼ ጋር በህብረት(በጥንድ፣በቡድን) እሰራለሁ፡፡ | | | | | |
| 28 | ያልገባኝን የሰዋስው ትምህርት የአማርኛ ቋንቋ ዕውቀት ያላቸው ሰዎች ማብራሪያ እንዲያደርጉልኝ እጠይቃለሁ፡፡ | | | | | |
| 29 | እርግጠኛ ያልሆንኩበትን የሰዋስው ትምህርት መምህሬን ጠይቄ እረዳለሁ፡፡ | | | | | |
| 30 | የአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ባህልና የአኗኗር ስርዓት ግንዛቤን ከህብረተሰቡ ጋር ማህበራዊ ተራክቦ በማድረግ አዳብራለሁ፡፡ | | | | | |

የሰዋስው ዕውቀት ለማዳበር ከላይ ከተዘረዘሩ ብልሀቶች በተጨማሪ የሚትገለገሉባቸው ብልሀቶች ካሉ ይዘርዝሩ፡፡

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

__________

መረጃ በመስጠት ስለተባበራችሁኝ አመሰግናለሁ!